# ነፃነታችን የሆነው የእግዚአብሄር ይቅርታ

ጃኪይ አስክ

## ዘፍጥረት 37-50

ትምህርት 1፡ ያዳላለት - *አባታቸው ከሁሉም አስበልጦ ይወደው ነበር*

ትምህርት 2፡ የተሳካለት - *ጌታ እግዚአብሄር ከዮሴፍ ጋር ነበር*

ትምህርት 3፡ ተርጓሚው - *ትርጉሙ ለእግዚአብሄር ነው*

ትምህርት 4፡ ገዢው - *ትንሹን ወንድማችሁን ወደ እኔ አምጡት*

ትምህርት 5፡ ወንድም - *እኔ ዮሴፍ ነኝ!*

ትምህርት 6፡ ልጅ- *አባቴን እዚህ አምጡት*

"...ቃልህን በልቤ ሰወርኩ..."

*መዝ* 119፡11

ዝግጅት

በቴንት ፓወር ፐብሊሺንግ

# መቅድም

ቀሪውን ህይወታችሁን ቅርፅ የሚያስይዘውን ጉዞ እየተጓዛችሁ ነው፡፡ ይህ ጉዞ ልዩ ነው፡፡ ለመማር ያላችሁ ጠንካራ ፍላጎት እና በሙሉ ልባችሁ የመከታተላችሁ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ የሚባለውን መጽሐፍ በመረዳት ለማደግ የምታደርጉት ጥረት በከፊል ይወስነዋል፡፡ ይህንን መጽሐፍ ተሰጥታችሁ ማጥናታችሁ ህይወታችሁን የሚያበለጽግ እና እግዚአብሄር በቃሉ ውስጥ ለእናንተ የመናገሩ ተስፋ አለው፡፡

ይህን ጥናት ስታጠኑ የሚከተሉትን ነገሮች መያዝ ይኖርባችኂል

1. የዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ምዕራፍ፡ *ነፃነታችን የሆነው የእግዚአብሄር ይቅርታ*
2. አዲሱን መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ

    በተጨማሪም

    ሀ. የህዳግ ማጣቀሻ ያለው መሆን አለበት

    ለ. የቃል ማውጫ

    ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ ካርታዎች ያሉት ይሁን
3. እርሳስ ወይንም እስኪብርቶ
4. 3 በ 5 ወይንም 4 በ 6 መጠን ያለው ካርድ

በቁጥር ሁለት ላይ የተዘረዘሩት መርጃ መሳሪያዎች ይህንን ጥናት በተሳካ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስን ለመቃኘት የሚረዷቸሁ መሳሪዎች ናቸው፡፡ይህ የመጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁ ከሆን *መጽሐፍ ቅዱስን መቃኘት* ከሚለው ጥናት መጀመር ይኖርባችኂል፡፡ ይህ ጥናት መጽሐፍ ቅዱስን በአግባቡ እና በብቃት ማጥናት የሚያስቸሏችሁ የቅኝት መሳሪያዎች አዘጋጅቶላችኂል፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ ምልክት ማድረግ አትርሱ ፡፡የእናንተ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በመሆኑ እላዩላይ አስምሩበት ፣ በሀይላይት ማርከር ምልክት አድርጉበት ፣አክብቡበት ፣በቀስት ምልክት አድርጉበት ማስታወሻ ደብተር ወይንም ትምህርቱን ቀድታችሁ ለመጠቀም፣ሀሳቦችን ፣ጥያቄዎችን ለመያዝ፣ ታብሌት ካላችሁ መጠቀም በመምረጥ እና ጥናታችሁን ልትቀጥሉ ትችላላችሁ፡፡

ይህ ጥናት ብቻችሁን ማጥናት እንድትችሉ ተደርጎ ነው የተዘጋጀው ፡፡ ያለምንም ወይንም መጠነኛ ችግር ጥናቱን ማጠቃለል ይኖርባችኂል፡፡በተጨማሪም ደግሞ አዲስ መረጃ ልታገኙ ትችላላችሁ ፣አዳዲስ መረዳቶችን ልታገኙ ትችላላችሁ፣መልስ የሚሹ ጥያቄዎቻችን ጠይቁ፡፡ አሁንም ሌሎች ጓደኞቻችሁን እንድትጋብዙ እናበረታታችኂለን፡፡

ጥናታችሁን በደስታ እንድታጠኑ እንመኛለን፡፡እግዚአብሄር በቃሉ ውስጥ ሲናገራችሁ ልባችሁ ይሰማ እና ይቀበል ዘንድ እንመኛለን፡፡በመጽሐፍ ቅዱስ ውስት የተፃፉት ታሪኮች በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል የተደረገላችሁን እውነት ያረጋግጡላችሁ፡፡

# ትምህርት አንድ

# አባታቸው ከሁሉም አስበልጦ ይወደው ነበር

## ዘፍጥረት 37- ያደላለት

---

### የትምህርት አንድ ቅኝት

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 1፡ ዘፍጥረት 37

- ዮሴፍ እና ህልሙ
- ቅናት በወንድሞች መካከል
- ዮሴፍ ተሸጠ
- ያዕቆብ ተታለለ
- የያዕቆብ ሀዘን

## *መግቢያ*

ዘፍጥረት ምዕራፍ 37 የያዕቆብ ልጅ በሆነው በዮሴፍ ታሪክ ይጀምራል፡፡በዚህ ቤት ውስጥ በተደጋጋሚ በተሰራው ኃጢአት ምክንያት ይህን ቤተሰብ በቀጣይነት የሚጎዳ ነገር ነበር የተፈጠረው፡፡ታሪኩን እያነበባችሁት ስትሄዱ አባት በሚወደው ልጁ ምክንያት የተፈጠረበትን የስሜት መጎዳት ተመልከቱ፡፡

የዚህን ቤተሰብ አባላት ጥፋት ለመለየት እና በራሳችን ጥፋት ለመታወር በጣም ቀላል ነው፡፡ በግንኙነት መካከል በመጠኑ ጥሩ ለሆነልን ሰው እኛም ምርጥ ለመሆን ከመፈለጋችን የተነሳ በዚህ ምክንያት የሚፈጠረውን ጥፋት ለመመልከት ይሳነናል፡፡ ስለዮሴፍ እና ስለወንድሞቹ የሚተርከውን ክፍል ስታጠኑ የጌታ መንፈስ ወደውስጣችሁ ያመጣው ሰው ይኖር ይሆን? እነማንን ይሆን  በሰላም እና በፍቅር አብራችኋቸው ለመኖር ስትታገሉ አእምሮአችሁን  የሚጎዳ እና ወደተሳሳተ አቅጣጫ የሚመራ ሀሳብ ተሞልቶባችሁ የምታገኙት ?

በእርግጥ ዮሴፍ ወንድሞቹ በእርሱ ላይ ያደረጉትበት ነገር ይገባው ነበር?የወንድሞቹ የቅናት ስር መነሻ ምን ነበር? የአባታቸውን መልካምነት እና በሰላም ለመኖር ያለውን ጥረት መመልከት የተሳናቸው ለምን ይሆን?እግዚአብሄር በዮሴፍ ህይወት ሚያስተምራችሁን ትምህርት በመከታተል ትምህርታችሁን ቀጥሉ፡፡

## *አባታቸው ከሁሉም አስበልጦ ይወደው ነበር*

**ክፍል 1**

***መግቢያ***፡ *መድረኩ ተዘጋጅቷል ያዕቆብና ልጆቹ በከነአን ምድር ኬብሮን በምትባለው ከተማ ውስጥ ከመላው ቤተሰቡ ጋር ይኖሩ ነበር ። የእግዚአብሄርን ታማኝነት፤ እርሱም ተስፋችን እግዚአብሄር ያዕቆብን በብዙ ሀብትና እና ንብረት ባረከው። በተጨማሪም እግዚአብሄር ያዕቆብን ከሁለቱ ሚስቶቹ ራሔል እና ልያ እንዲሁም ከባሪያዎቹ የተወለዱ በአስራ ሁለት ወንድ ልጆች በመስጠት ባረከው።*

*የያዕቆብን ታሪክ እያጠናን ስንሄድ ትኩረታችን በአንደኛው ለጁ በዮሴፍ ላይ ይሆናል። ታሪኩንም በዘፍጥረት* 37 *ላይ እናገኘዋለን። ዮሴፍ ገና አስራ ሰባት አመቱ ነበር። ከታላቅ ወንድሞቹ ጋር በመሆን መንጋ ይጠብቅ ነበር። እስቲ እናንተም ይህንን ሁኔታ ለመተግበር የአስራ ሰባት አመት ወጣት የነበራችሁበትን ጊዜ አስታውሱ። በዚያን ወቅት በህይወታችሁ ይካሄድ የነበረው ነገር ምን ነበር? ምን አይነት ጥበብ ወይንም ሀሳብ ውስጣችሁ እንደነበር ታስባላችሁ? ምንስ ይጎድላችሁ ነበር? ከአስራ ሰባት አመት በታች ከሆናችሁ ደግሞ ይህ እድሜ ምን እንደሚመስል ተመልከቱ። ወደ አስራ ሰባት አመታችሁ ስትጠጉ የእድገት እና የብስለት ምሳሌ አድርጋችሁ ልታስቀምጧቸው የምትመርጧቸው ነገሮች ምንድናቸው?*

**የቤት ስራ**፡ ዘፍጥረት 37፡1-11 አንብቡ

***መልመጃ፡***

1. *በቁጥር* 2 *መሰረት ዮሴፍ ወደአባቱ ይዞ የመጣው ምን ነበር?* ________________________
   *ለተነገሩን ገፀ ባህሪያት የሰጠነው ስያሜ ምንድነው* (*ማን ብለን እንጠራቸዋለን*)?__________
   ____________________________________________________________

2. *ዘፍጥረት* 3 *ለአመታት የዳበረውን ግንኙነት እድንረዳው ያደርገናል*____________________
   *ያዕቆብ ለአድልዎ ማሳያ ያደረገው ምን ነበር* (*ቁጥር* 3)?
   ____________________________________________________________

*ማስታወሻ ዘፍጥረት 32፡27-28 ተመልከቱ*

3. ግልፅ ለሆነው የያዕቆብ አድልዎ የወንድሞቹ ስሜት ምን ነበር?_____________________

_____________________________________________________________________

**ትምህርት** ፡ ኦ አምላኬ! ውጥረቱን ተመለከታችሁ? የያዕቆብ ለዮሴፍ ያደረገው አድልዎ በታላላቅ በወንድሞቹ ውስጥ ጥላቻን አሳደረበት ። ለወንድማቸው ያላቸው ጥላቻ ውስጥ ውስጡን ይበላቸው ጀመር ስለእሱም ምንም ጥሩ ነገር ሊናገሩ አልቻሉም። ምንም ርህራሄ ሊያሳዩት አልቻሉም። ያዕቆብ የሚያደላለት ልጅ ቢኖረው ይደንቀን ይሆን? ያዕቆብ የተነሳበትን ሁኔታ አስታውሱ (ዘፍጥረት 25፡28) ። ዘፍጥረት 29፡30 ራሄልን ከልያ አስበልጦ ይወዳት እንደነበር ይነግረናል። ስለዚህ የአድልዎ፣ቅናት፣በያዕቆብ ቤት ውስጥ ገብቷል፤ ስለዚህም በታላላቆቹ ወንዱሞቹ እና በታናሻቸው መካከል ጥላቻ ገባ።

**መልመጃ**: ዮሴፍ ህልም ነበረው (ዘፍጥረት 37፡5)

1. በቁጥር 5 ላይ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ህልሙን ሲነግራቸው የወንድሞቹ ምላሽ ምን ነበር?_____________________________________________________________
2. የዮሴፍን ህልም በራሳችሁ ቃል ግለፁት( ቁጥር ________________________________

_____________________________________________________________________

3. ወንድሞቹ እንዲህ ብለው ጠየቁት "በእኛ ላይ____________ይሆን? ወይስ__________ይሆን? አሉት። ለእነርሱ የህልሙ ትርጓሜ ይህ ነበር።
4. እንደገና በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለሶስተኛ ጊዜ እነዚህ ወንድሞቹ_____________የሚለውን አንረሳውም። ህልሙም ሆነ የእርሱ ንግግር አስቆጥቷቸዋል። ሶስቱንም ጊዜ ጠሉት የሚሉትን ቃላቶች አስምሩባቸው።
5. አንዳንዴ ማንም ምንም ማድረግ አይችልም ዮሴፍ ይህ ካልገባው ግን የሚገርም ነው በቁጥር 9 ላይ ምን ተፈጠረ? ______________________________________________
6. ህልሙ በዚህን ጊዜ ምን ማለት ነው?________________________________________
7. ለዚህ የዮሴፍ ህልም የያዕቆብ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 10)? ______________________
8. በቁጥር 11 ላይ ለህልሙ የወንድሞቹ ምላሽ ምን ነበር? ____________________________
   የአባቱስ ምላሽ ምን ነበር?____________________________________________
9. አድልዎ ወደ ጥላቻ ፣ጥላቻ ደግሞ ቅናትን አነሳሳ። አባትየው ነገሩን በልቡ አሰላሰለ።አባታቸው

ከሁሉ አስበልጦ ይወደዋል፡፡ጥላቻ እና ቅናታቸው የተመሰረተው በአባታቸው አድልዎ ላይ ነው፡፡ ዮሴፍን ከወንድሞቹ ሁሉ አብልጦ ይወደው ነበር____________ (ዘፍጥረት 37፡4)

**ክፍል 2**

**ትምህርት፤** ቅናት አዲስ ቃል አይደለም ፡፡ ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ራሄል መካን በመሆኗ ልጅ በምትወልደው እህቷ ልያ ትቀናባት ነበር፡፡ ራሄል ያዕቆብ ከልያ ልጆችን በመውለዱ ምክንያት ከልቡ እንደሚያወጣት አስባ ትፈራ ነበር፡፡ ቅናት በሁለት ተቃራኒ ቡድኖች መካከል የጠላትነትን አመለካከትን ይፈጥራል፡፡ በቅናት ውስጥ ምንም እግዚአብሄራዊ ወይንም መንፈሳዊ ስሜት ሊኖር አይችልም፡፡ በሁለቱ መካከል የነበረው ሁኔታ የእግዚአብሄርን የፍቅር እና የመልካምነት ባህሪይ የሚያንፀባርቅ አልነበረም ነገር ግን ለአንዳንዶች የማይገባቸው ነገር ሆኖባቸዋል፡፡ ቅናት የአንዱ የሆነውን ነገር ለራስ የመውሰድ ስግብግብነት ነው፡፡ ተስፋችን የሆነው የእግዚአብሄር ታማኝነት በሚለው በትምህርት 5 ክፍል 5 ጥናት ውስጥ የራሄል እና የልያ የቅናት ችግር ተገልጿል ፡፡ በእነዚህ እህትማማቾች መካከል የነበረው ኃጢአት ወደ ወንድማማቾቹም ተላለፈ፡፡

**ጥልቅ ምልከታ፤** ዘፍጥረት 37፡11 እንዲህ ይላል "ወንድሞቹ ቀኑበት" እስቲ በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ የተጠቀሱትን የዚህን ክፍል ማጣቀሻዎች ተመልከቱ የሐዋሪያት ስራ 7፡9 ፡፡የዚህ ክፍል የአዲስ ኪዳን ማጣቀሻ ቀጥሎ ምን ተፈጠረ ይለናል? ቅናታቸው ወደምን አመጣቸው ይላል?______________________________________________________________

______________________________________________________________

**የቤት ስራ፡** ወደ ዘፍጥረት 37 ተመልሳችሁ ከቁጥር 12-25 ያለውን ክፍል አንብቡት፡፡

**መልመጃ፡**

1. በቁጥር 12 መሰረት መቼ ነበር ወንድሞቹ የሄዱት?________________________________
   በዚያ ምን ያደርጉ ነበር?________________________________________________

በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ጀርባ ላይ ባለው ካርታ ላይ ሴኬምን ተመልከቱ ፡፡ ከካርታዎቹ በአንደኛው ላይ ሴኬምን ከእየሩሳሌም በስተሰሜን እና ከቤቴል በስተሰሜን ጠቁሙ፡፡ በሴኬም እና በእየሩሳሌም መካክል ያለውን ርቀት ገምቱ______________________________________

2. ቁጥር 13 እስራኤል (የዕቆብ) ዮሴፍ ምን ነገረው? ________________________________

3. ቁጥር 14 የዮሴፍ መመሪያ ምን ነበር? ________________________________________

ዮሴፍ ከዝርዝር መረጃ ጋር ሲመለስ በመጨረሻ ወቅት ምን እንደተፈጠረ አስታውሱ (ቀጥር 2)

___________________________________________________________________________

4. ዮሴፍ ረጅም መንገድ ነው የተጓዘው፤ እዚያም በደረሰ ጊዜ ወንድሞቹን ያሉበትን ለማወቅ ተቸገረ። በቁጥር 15-17 ባለው ክፍል ምን አገኘ? ____________________________________

___________________________________________________________________

ዶታይን ከኬብሮን በግምት ከ16 እስከ 24 ኪሎ ሜትር ሰሜን እና ሰሜን ምእራብ ርቀት ላይ ትገኛለች። ይህ እርቀት አስፓልት ቢሆንና በመኪና ቢኬድ ይህን ያህል ከባድ ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን ዮሴፍ በእግሩ በጣም አስቸጋሪ የሆነውን የከነአንን ድንጋያማ መንገድ በእግሩ እደተጓዘ ስናስብ እይታችን ሌላ ይሆናል ።

5. ዮሴፍ ወንድሞቹን በዶታይን አገኛቸው ነገር ግን ቁጥር 18 ምን ይነግረናል?

___________________________________________________________________________

6. ጥላቻ እና ቅናት ወንድማቸውን ለመግደል ተዘጋጅተው እንዲጠብቁት አደረጋቸው።ምናልባት ይህ ብዙም ላይገርመን ይችላል፤ ምክንያቱም በዘፍጥረት 4 ላይ የቃየን ጥላቻ እና ቅናት ወንድሙን እንዲገድል እንዳደረገው እናስታውሳለን።

7. ታዲያ ወንድሞቹ ከርቀት ወደ እነርሱ ሲመጣ ሲያዩት ማን መጣ ነበር ያሉት?__________

8. በቁጥር 20 ላይ ምን ለማድረግ አቀዱ? ________________________________________

9. በታሪኩ መሰረት ምን አይነት ምክር መከሩበት?_________________________________

የዮሴፍ ህልም ያበቃለት ይመስል ነበር። እነዚህ ወንድማማቾች ለዚህ ባለህልም ምን እንደሚገባው ሊያሳዩት ቆርጠዋል።

10. የትኛው ወንድሙ ነበር ሊያድነው የሞከረው? __________________በዘፍጥረት 29፡32 ስለእርሱ ምን እንማራለን? _____________________________________________

11. ሮቤል እንደ አማራጭ ያቀረበው ሀሳብ ምን ነበር?______________________________

12. ምን ማድረግ ነበረበት?_____________________________________________________

13. በቁጥር 23-24 ወንድሞቹ እንዳሰቡት አደረጉበት። ባለብዙ ቀለሚን ቀሚሱን ገፈፉት በምድረ በዳው በሚገኘው ጉድጓድ ውስጥም ጣሉት፤ ውሀ የሌለበት ጥልቅ ጉድጓድ ነበር።

14. ምግብ እየበሉ ሳለ ምን ተመለከቱ ቁጥር 25 ላይ?_____________________________

15. እስማኤላውያን ነጋዴዎች መጡ፤ ለመሆኑ እዚህ እስማኤላውያን ነጋዴዎች እነማን ናቸው (ዘፍጥረት 16፡11)? ____________________________________________________

## ክፍል 3

***መግቢያ፡*** *እስማኤላውያን የሚመጡት ከገለአድ ነበር፡፡ ስለዚህ ገለአድን በካርታችሁ ላይ ለመመልከት አንዲትን ከተማ ሳይሆን አንድን ክልል ነው መመልከት ያለባችሁ፡፡ ካርታችሁ ገለአድን የማያመለክት ከሆነ ገለአድ የምትገኘው ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ ነው፡፡ሰሜናዊው ክፍል እስከ ገሊላ ባህር ይደርሳል፡፡ የደቡቡ ክፍል እስከ ሙት ባህር (ጨው ባህር ድረስ ይደርሳል፡፡*

**የቤት ስራ፡** ዘፍጥረት 37፡ 24-36 አንብቡ፡፡

***መልመጃ፡***

1. *ነጋዴዎቹ ከገለአድ ወደግብፅ ነበር የሚጓዙት ለመሆኑ እነዚህ ነጋዴዎች የጫኑት ምንድነበር?*____________________________________________________
2. በቁጥር 26-27 ላይ ይሁዳ ለወንድሞቹ ያቀረበው ሀሳብ ምንድነበር? ____________________

______________________________________________________________________

3. ወንድሞቹስ በምን መልኩ ምላሽ ሰጡ?__________________________________________

**ትምህርት** ፡እዚህ ስፍራ ላይ እንድታስታውሷቸው ጥቂት ቃላቶችን ደግመን እንመለከታልን፡፡

- እስማኤላውያን የአብርሐም ልጅ የእስማኤል ልጆች ናቸው (ዘፍትረት 61፡16)
- ምድያማውያን የአብርሐም ሚስት የኬጡራ ልጆች ናቸው(ዘፍጥረት 25፡1-4)
- ምድያም እሩቅ ደቡብ እና ሙት ባህር ደቡብ ምስራቅ አካባቢ ያለው ክልል እንዲሁም ከኤዶም ደቡብ ነው፡፡እነዚህ የንግድ ጭነቶች ጉዞአቸውን የሚጀምሩት ከምድያም ሲሆን በሰሜን ወደ ገለአድ በመጓዝ ከነአንን አቋርጠው የዮሴፍ ወንድሞች ባገኙበት ስፍራ በዶታን አድርገው ይጓዛሉ፡፡

*ማስታወሻ ፡እነዚህ ቃላቶች ለትምህርታችን ብዙም አስፈላጊ ላይሆኑ ይችላሉ ነገር ግን እንዚህን ነገሮች በደንብ ማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን ይበልጥ ለመረዳት ያግዙናል ፡፡በርግጥ ስለዚህ ጥንታዊ ዓለም እና ጥንታዊ ባህል ከዚህ በፊት የትም አጥንታችሁ እንደማታውቁ አስባለሁ፡፡በጣም ጥሩ እያደረጋችሁ ነው ጥናታችሁን ቀጥሉ፡፡*

4. ምድያማውያን ነጋዴዎች ሲመጡ ወንድሞቹ ምን አደረጉ?____________________________

_____________________________________________________________*ነጋዴዎቹ*

ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወሰዱት፡፡

5. ጥቂት ቆይቶ የተደረገውን ነገር በሙሉ ያላየው ከዛበኋላ ነገሩን የተረዳው ማነው?______

________________________________________________________________

6. ቁጥር 30 ላይ ሮቤል ዮሴፍን ለማዳን ያደረገው ሙከራ አልተሳካለትም ፡፡ጉድጓዱ ውሃ የሌለበት ባዶ ነበር ዮሴፍም ተወስዶ ስለነበር በስፍራው አለተገኘም ነበር፡፡ማድረግ የፈለገውን ማድረግ አልቻለም ነበር፡፡በዚህ ግዜ ምን አለ? ______________________________________

________________________________________________________________________

7. ታላቁ እቅድ በ ቁጥር 31 ላይ ወንድሞቹ ምን ነበር ያደረጉት? ____________________

________________________________________________________________________

8. በቁጥር 32 ላይ ወንድሞቹ ለአባታቸው ምን ነገሩት? ____________________________

__________________________________________________________________

**ክፍል 4**

***ትምህርት፡*** *ይህ ታሪክ የመጀመሪያው ስውር ታሪክ አይደለም፡፡ የመጀመሪያውን አስታውሱ የተከናወነው በኤደን ገነት በዘፍጥረት3፡7 ለይ ነበር፡፡አንድ ስህተት ስንሰራ የመጀመሪያው እርምጃችን መደበቅ ነው፡፡አዳም እና ሄዋን የበለስ ቅጠል ሰፍተው በመልበስ በዛፍ መካከል ተደበቁ፡፡በፈፀሙት ድርጊት ምክንያት በሰላም ወደ ቤት መመለስ አልቻሉም፡፡ ዮሴፍን ለመግደል የነበራቸው እቅድ ከሽፏል ፡፡የክፉ እቅዳቸው እስረኛ ሆነዋል ፡፡ከሚጠሉት ሰው ላይ የገፈፉትን ልብስ ደም ነክረው ለአባትየው ሊሰጡት ይዘውታል፡፡ አባትየውም በጣም ለሚወደው እና ለሚያደላለት ልጁ የሰራውን በደም የተነከረውን ውብ ባለህብረቀለም ልብስ ልጁ እንደሞተ አምኖ ተቀምጧል፡፡*

***ገለፃ*** *፡ የገዛ ወንድሙን ለመግደል ማቀድ ምን ይመስል ይሆን? አንድን ሰው ለመግደል ማሰብ ምንኛ መጥፎ ነገር ነው? እነዚህ ወንደማማቾች ላለፉት 17 አመታት በወንድማቸው ዮሴፍ ላይ ቅናት ሲያቃጥላቸው ነበር፡፡በሰው ህይወት ውስጥ ሰይታወቅ እያደገ የሚመጣ ኃጢአት መጨረሻው ሞት ነው የሚሆነው፡፡*

1. ቅዱስ ጳውሎስ በ ገላቲያ 5፡19-21 የፃፈውን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እዚያ ላይ የዘረዘራቸው የኃጢአተኛ ሰው ድርጊቶች ምን ይመስላሉ? ____________________________

________________________________________________________________________

2. እነዚህን ድርጊቶች በተመለከተ የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ ምን ነበር?__________________

3. ምሳሌ 16፡25 ለሰው ቅን የምትመለስል መንገድ ፍፃሜዋ ምንድነው ይላል? ____________

4. በሮሜ 8፡10-14 የሚጠበቅብንን ግዴታ እና የክርስቶስን በውስጣችን መኖር ይነግረናል፡ ቁጥር 13 በኃጢአት መኖር ከቀጠልን ምን ይሆንብናል ይለናል? ____________________
________________________________________________________________________

5. በመንፈስ የምንኖር ከሆነስ ምን እንሆናለን?________________________________________
________________________________________________________________________

**የምናሰላስለው ቃል፡** ሮሜ 8፡ 10-14 ኃይለኛ ቃል ነው፡፡

1. ይህንን ክፍል ደግማችሁ በጥንቃቄ አንብቡ በውስጡ ያለውንም እግዚአብሄር ለናንተ ያለውን ፍቅር እና እንዴት በተትረፈረፈ ህይወት ውስጥ እንድትኖሩ እንደሚገልግ ለመረዳት ሞክሩ፡፡
2. ባዘጋጃችሁት ካርድ ላይ ቀጥር 13 አና 14 ፃፏቸው፡፡
3. እዚህን ቁጥሮች በዚህ ሳምንት ስታሰላስሏቸው ቀጥሎ ተዘረዘሩትን ተግባራዊ መመሪያዎች እራሳችሁን ጠይቁ፡፡
   ሀ. ለኃጢአት ተገዝቶት ያገኙሁት የህይወቴ ክፍል የትኛው ነው? (ገላተያ 5፡19-20)
   ለ. እግዚአብሄር በህይወቴ እየሰራበት ያለው እና በመንፈስ እየተመራሁበት ያለው የህይወቴ ክፍልስ የትኛው ነው? (ገላትያ 5፡22-23)
4. በካርዳችሁ ጀርባ ላይ የነእዚህን ጥያቄዎች መልስ ፃፉባቸው፡፡ይህን ክፍል ለማሰላሰል ካርዱን በዚህ ሳምንት በአግባቡ ተጠቀሙበት፡፡

<u>**ክፍል 5**</u>

**ግላዊ ትግበራ**

1. እራሳችሁን ከዮሴፍ ወንድሞች መካከል አንዱ ብታደርጉ ማንን ትመስሉ ነበር? ሮቤልን፣ይሁዳን፣ወይንስ ሌሎቹን በወሰኑት ውሳኔ ከእነሱ ጋር ትስማሙ ነበር? ቁጥር (27) የምትስማሙ ከሆነ ለምን? ካልትስማማችሁ ደግሞ የማትስማሙበት ምክንያት ምንድነው?______________________________________________________

   መልካም ነገር ሊያደርጉ ሚፈልጉ ቡድኖች መካከል ተገኝታችሁ ትክክለኛ ሀሳባቸውን ተቃውማችሁ ታውቃላችሁ እንድትቃወሙ ያደረጋችሁ ምክንያት ምን ነበር ?____________

ሌላውን ሰው በቅን መንገድ መርታችሁ ታውቃላችሁ ታናናሽ ወንድሞቻችሁ ትክክለኛው ነገር ማድረግ ሲያቅታቸው ብትመለከቱ ልትረዷቸው እና ልታቀኗቸው ምን ታቅዳላችሁ ?__________

______________________________________________________________________

ስለዮሴፍ ጠበቃ ሆናችሁ ታውቃላችሁ በጣም የተሰማችሁ ቢሆንም ከዛ በተቃራኒ ወንድሞቻችሁን ምን ልትሏቸው ትችላላችሁ?_____________________________________________

______________________________________________________________________

2. ሮቤል ከሁሉም ታላቅ ስለሆነ ስለትንሹ ወንድሙ ኃላፊነት ያለበት እሱ ነበር።እራሳችሁን አሳልፋችሁ የምትሰጡለት ኃላፊነት ተቀብላችሁ ታውቃላችሁ? ምን ይመስል ነበር?____________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

3. ይሁዳን ልብ ብላችሁታል? ዮሴፍ እንዲወገድ ቢፈልግም እንዲሞት ግን አልፈለገም ነበር።ዮሴፍን ገድለው ደሙ በእጃቸው ቢኖር ምንም እንደማይጠቀሙ ነበር የነገራቸው። እናንት ብትሆኑ በነዚህ በተናደዱ ወንድሞች መካከል ቆማችሁ ይህንን ልትናገሩ ትችሉ ነበር? በዚህ ስፍራ ብትሆኑ ምን ታስቡ ነበር ?_______________________________________

______________________________________________________________________

4. ምን አይነት ባህሪ ያለው ሰው ነው ቅናት ቀጥሎም የነፍስ ገዳይነት ሀሳብ ከፈለቀበት የኃጢአት ባህሪ ተቃራኒ መሄድ የቻለው?_______________________________

______________________________________________________________________

5. ቅናት ህይወቴን መሰቃቅሎት ለሰዎች ፍቅር ፣ ማበረታታት፣ መደገፍ እና መልካም የሆነውን ለነሱ ከመመኘት ይልቅ በክፉ ንግግር፣በሚያፈርሱ ቃላት ፣በተሸቃቀጠ እና በተቀነባበረ ውሸት አእምሮዬን የቂጣ እና የበቀል ወደብ አድርጌ የኖርኩባቸው ጊዜያት መች ነበሩ ?______________________________________________________________

______________________________________________________________________

**ጸሎት፡** ኦ! ጌታ ሆይ በቅናት በተሞላው በገዛ ሀሳቤ ወጥመድ በፍጥነት ተይዠለሁ፣ሌሎች በያዙት ስፍራ ቀንቻለሁ፣በሌሎች ፍቅር፣ግንኙቶች እና ጓደኝነት ፣በስጦታቸው፣በችሎታቸው፣ በፍላጎታቸው እና በሙያቸው ቀንቻለሁ። በራሴ ማንነት እንድደነቅ ፈልጌያለሁ አሳፋሪ እና ከንቱ ሀሳቦች በውስጤ እንዲመላለሱ ፈቅጃለሁ።እራሴንም ከዮሴፍ ወንድሞች የተለየሁ ሰው ሆኜ አላገኘሁትም።ጌታ እየሱስ ሆይ እባክህ ይቅር በለኝ።በህይወቴ ውስጥ እንዲኖር የምፈልገውን ለውጥ በራሴ ማምጣት አልቻልኩም ነገር ግን ሕይወቴን በቅዱሱ መንፈስህ አንድትመራ እና

የሰማዩ አባት ልጅ መሆን እችል ዘንድ እንድታደርገኝ  እራሴን ሙሉ በሙሉ ላንተ ሰጥቻለሁ። አባት ሆይ በተለይ በዚህ የህይወቴ ክፍል ውስጥ ______________________________እንድትረዳኝ እፈልጋለሁ። ካለፈው ህይወቴ የተሸከምኳቸውን  የጥፋተኝነት ስሜቶች አስወግደህ በነፃነት እንድመላለስ ሰላሳረፍከኝ አመሰግንሀለሁ   የሰጠኸኝም ነፃነት ______________________ማድረግ ያስችለኛል።

***ትምህርት፡*** የእነዚህ ወንድማማቾች ድርጊት ያስከተለው ነገር ነበር ፤አባታቸው እጅግ በጣም ተጎዳ ፤ልጁንም ቀሚሱም አወቀው በሀሳቡም ክፉ አውሬ ሰውነቱን ሲገነጣጥለው ታሰበው።በዚህም ምክንያት ያዕቆብ ልብሱን ቀዶ ማቅ ላይ ተቀምጦ ለብዙ ቀናት ለልጁ አለቀሰ።ወንድ እና ሴት ልጆቹ በዙሪያው ሊያፅናኑጽ ተሰበሰቡ ነገር ግን ሊፅናናላቸው አልቻለም።እያለቀሰም  ወደልጄ “ወደሙታን ስፍራ ___________________________ እወርዳለሁ” አለ።(ዘፍጥረት 37፡33-35)

ባለፈው ህይወታችን ሌሎችን የበደልነው በደል ያስከተለውን ችግር ገፊት በቀማሽ መሆናችን አይቀርም።ነገር ግን ባለንበት ሁኔታ ውስጥ  እግዚአብሄር እንደማይረሳን እና እንደማይዘነጋን ማወቅ አለብን። ፍቅር በሆኑት ክንዶቹ ያቅፈናል።እኛም ባለፈው ስህተታቸው ምክንያት በጉዳት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ደግፈን መያዝ ይኖርብናል።

ያዕቆብ አታላይ ነበረ፤ከቤቱ የተሰደደው በማታለል ምክንያት ነበር።አባቱን እና ወንድሞቹን አታሏል።ፈርቶም ከወንድሙ ሸሽቷል።በአጎቱ ቃል የተገበችለትን ሚስት ሳያበኝ በአጎቱ በተደጋጋሚ ተክዷል።አሁን ደግሞ የገዛ ልጆች ዋሹት። ቅናት ፣ምቀኝነት ፣ክህደት እነዚህን የመሳሰሉት በሙሉ የክፉ ስራዎች ናቸው።ነገር ግን በዚህ ሁሉ ትርምስምስ በሆነ  ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሄር ስራውን እየሰራ ነበር።የዮሴፍን ታሪክ ቀጥለን ስንመለከት በመጨረሻ እግዚአብሄርን ባለድል ሆኖ እናገኘዋለን።

# ትምህርት ሁለት

# ጌታ ከዮሴፍ ጋር ነበር

## ዘፍጥረት 39- ስኬታማው

---

**የትምህርት 2 ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 2፡ ዘፍጥረት 39

- ዮሴፍ በጲጢፋራ ቤት
- ጲጢፋራ በዮሴፍ ምክንያት ተባረከ
- ዮሴፍ ፈተና ገጠመው
- ዮሴፍ ኃጢአትን እምቢ አለ

  ዮሴፍ ስለፅድቅ መከራን ተቀበለ

## *መግቢያ*

በክፍል አንድ ትምህርታችን ዮሴፍ በወንድሞቹ አማካኝነት ከምድያማውያን ወደ እማኤላውያን ከዛም ወደ ግብፃውያን እንደተሸጠ ተምረናል፡፡በዚህ የትምህርት ክፍል ደግሞ የዮሴፍ የባርበት ጉዞ በጲጢፋራ ቤት እንደተደመደመ ያሳየናል፡፡ በጲጢፋራ ቤት ስራውና ሀላፊነቱ ምን እንደሆነ ተነግሮታል፡፡ከወንድሞቹ የደረሰበትን መገላታት እንዴት ተቋቋመው ? ከምድያማውያን ጋርስ የነበረውን የምድረበዳ ጉዞ ፣በባእድ ሃገር ባሪያ ሆኖ መኖርን እንዴት ተቋቁሞት ይሆን? ለመሆኑ ይህ ሁሉ ነገር ሲሆን እግዚአብሄር የት ነበረ?

እቅዱ ትንሽ ከበድ ይላል፡፡በጲጢፋራ ቤት ችግር ነበረ፡፡ዮሴፍም ትክክለኛ ላልሆኑ ሁኔታዎች ምንአይነት ምላሽ ሰጥቶ አንደነበር እስቲ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ትክክለኛ ነገር አድርጋችሁ በሀሰት ስትወነጀሉ ያንን ሁኔት እንዴት እና ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ከዮሴፍ ህይወት ተማሩ፡፡ዮሴፍ ከእግዚአብሄር ጋር በነበረው ግንኙነት ላይ ምን እንደተፈጠረ ተመልከቱ ፡፡ትክክለኛ ላልሆነ ፍርድስ የናንተስ ምላሽ ምን መሆን ይኖርበታል? ኃጢአት ለሆኑት ነገሮች የጠሰተው የዮሴፍ ምላሽ እናንተን ምን ያስተምራችኋል?

ነገሮች እየባሱ ሲሄዱ እግዚአብሄር ሆይ እንደ ዚህ አይነት መፈሳዊ ሰው ላይ ይህን አይነት መከራ እንዲደርስበት ትፈቅዳለህ? ዘንግተኸው ይሆን? ዮሴፍስ እንደተዘነጋ ተሰምቶት ይሆን? ታዲያ የተሳካለት ሰው ከሆነ በህይወቱ ውስጥ ያለፉት መከራዎች በሙሉ አስፈላጊ ነበሩ ማለት ነው?

እግዚአብሄር ከዮሴፍ ጋር በመከራ ውስጥ ያደረገውን የጉዞ ታሪክ ስታጠኑ ስለ እግዚአብሄር እና ፤እግዚአብሄር ስለመከራ ያለውን ነገር ልብ በሉ፡፡

## ክፍል 1

***መግቢያ***፡ በዘፍጥረት 37 ውስጥ ክፉ ባህሪያትን፣ ክህደትን ፣የግድያን ሀሳብ በያዕቆብ ቤት ውስጥ ገብተው ተመልክተናል፡፡ከሁሉ አስበልጦ በሚወደው ልጁ ደም የተቀባውን ልብስ ይዞ መፅናናት በሌለበት እጅግ በመረረ ሀዘን ውስጥ የተቀመጠ አባት፤ያዕቆብ ፡፡ በመታለል ልጁ ዮሴፍ በአንድ ክፉ አውሬ እንደተገደለበት አምኗል፡፡ ወንድሞቹም በትንሹን እና አስቸጋሪው ወንድማቸውን ላይ ያደረጉትን ክፉ ስራ የሚሸፍን የፈጠራ ታሪክ አቀነባብረዋል፡፡በተጨማሪም ወንድሞቹ የዮሴፍን ህይወት በበረሀ ለንግድ ይሄዱ ለነበሩት ምድያማውያን (እስማኤላውያን) ነጋዴዎች በመሸጥ ከአደጋ ጠብቀውታል ነገር ግን አባቱ የሚያውቀው ልጁ እንደሞተ ነው፡፡
ዮሴፍ ምን ገጥሞት ይሆን? ያዕቆብ እና ልጆቹን ትተን ዘፍጥረት 39ን እንመልከት፡፡ዘፍጥረት 37፡36 ይህ ሁሉ አሳዛኝ ነገር በያዕቆብ ቤት እየተካሄደ ባለበት ወቅት ምድያማውያኑ (እስማኤላውያኑ) ዮሴፍን ወደግብፅ ወስደው በፈርኦን ቤተ የጥበቃዎች ሀላፊ ባለስልጣን ለሆነው ጲጢፋራ እንደሸጡት ይህ ክፍል ይነግረናል፡፡

**የቤት ስራ፡** ዘፍጥረት 39፡1-6 ያለውን ክፍል እንብቡ፡፡ ቁጥር1 ቃል በቃል ዘፍጥረት 37፡36 ይደግመዋል፡፡

***መልመጃ፡***

1. በቁጥር 2 ላይ ስለዮሴፍ የመንማራቸው የመጀመሪያዎቹ ነገሮች ምድናቸው?

   ሀ.________________________________________

   ለ. ________________________________________

   ሐ. ________________________________________

2. ዮሴፍን እንዲቀበለው የጲጢፋራን ልብ የሳበው ነገር ምን ነበር (ቁጥር 3)?

   ሀ.________________________________________

   ለ. ________________________________________

3. ዮሴፍ በጲጢፋራ ቤት ውስጥ የተሰጠው ሀላፊነት ምን ነበር?

   ሀ.________________________________________

ለ. ____________________________________________________________

4. ከዮሴፍ የተነሳ ግብፃዊው እና የግብፃዊው ቤት ተባረከ (ቁጥር 5) ፡፡ከቁጥር 2-5 ያለውን ክፍል ስለእግዚአብሄር የተነገረ ቃል በመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ በማርከር ምልክት አድርጉበት ፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ላይ የተገለፀው የእግዚአብሄርን የበረከት ውጤት በህዝቡ ላይ እንደገናም የህዝቡ መባረክ ደግሞ ለሌሎች በረከት የመሆኑ ነገር ምን እንድንማር ያደርገናል?____________________________________________________________

____________________________________________________________

5. የቁጥር አምስት መጨረሻ ምን ይነግረናል ?________________________________

____________________________________________________________

6. እግዚአብሄር ቤቱ ውስጥ ያለውን ነገር በመባረኩ ምክያት የዮሴፍ ኃላፊነት ምን ነበር?____________________________________________________________

____________________________________________________________

7. የጲጢፋራ ነፍስ በምን ተይዛ ነበር (ቁጥር 6) ?________________________________

**ክፍል 2**

**ግላዊ ትግበራ፤**የእግዚአብሄር ህዝቦች በእግዚአብሄር በረከት ውስጥ ነው የሚኖሩት፡፡ነገር ግን እግዚአብሄር ህዝቦቹን መባረክ ብቻ ሳይሆን ህዝቦቹን ለሌሎችም በረከት ያደርጋቸዋል፡፡

1. እግዚአብሄር አብርሀምን በዘፍጥረት 12፡2-3 ላይ ምን ነበር ያለው? ____________________

   ____________________________________________________________

2. እግዚአብሄር አብርሀምን በረከት እንደሚሆን እና ለምድር አህዛብ መባረክ ምክንያት እንደሚሆን ተናግሮታል፡፡የምድር ህዝቦች በሙሉ በእርሱ ይባረካሉ፡፡ይህ እውነት በእናንተ ህይት ውስጥ ምን ተግባራዊነት እዳለው ትመልከቱ፡

   ሀ. በዙሪያህ የሚኖሩት እነማን ናቸው? ለምሳሌ ጎረቤቶች፣የስራ ባልደረቦች፣ጓደኞች የተወሰኑትን ግንኙነቶችህን ጥቀስ________________________________

   ____________________________________________________________

   ለ. እስቲ እነሱ ባንተ በኩል እንዴት እንደተባረኩ አስብ፡፡ለምሳሌ ደህንነት እና ጥበቃ፣ታማኝነት እና እውነት፣መልካም ባህሪ እና ፍፁምነት፡፡በዚህ እና በሌሎች ሁኔታዎች ህይወታቸውን በምን መልኩ ባንተ አልፎ ተነክቷል?____________

   ____________________________________________________________

**ማሰላሰል፡** ስለራሳችን እንዲሁም ስለሌሎች ስንል የእግዚአብሄርን ቃል መጠበቅ ይገባለናል፡፡ይህንን ጥናት ስንቀጥል እግዚአብሄር ማን እንደሆነ ፣እኛን እንዴት ሊባርክን እንሚፈልግ፣እደዚሁም በእኛ አልፎ ሌሎቸን ሊባርክ እንደሚፈልግ እንመለከታለን፡፡የተመረጠው የምታሰላስሉት ጥቅስ መዝሙር 1፡1-3 ነው፡፡

1. በቁጥር 1 ላይ ከአካባቢያችን ማስወገድ ያለብን ነገሮች ምንድናቸው?

    ሀ.________________________________________

    ለ. ________________________________________

    ሐ.________________________________________

2. መዝሙረኛው ተድላችን ምን መሆን እንዳለበት ነው የሚነግረን?

    ሀ.________________________________________

    ለ.________________________________________

3. በመጨረሻም በቁጥር 3 ውስጥ የተሰጠን ምስል ምንድነው? ________________________
4. በዚህ ክፍል የተጠቀሰችውን ዛፍ ግለፅ በምን ስፍራ የተተከተለች ነበረች ሁኔታዋስ ምን ይመስል ነበር?________________________________________
5. አስቲ እንደተባረከ የእግዚአብሄር ህዝብ እንደገና አስቡ በእኛ ምክንያት የተባረኩ ሰዎች እነማን ናቸው፡፡በሌላ መልኩ ይህን ጥያቄ ለመጠየቅ በእኛ ቅርንጫፍ ላይ ጎጇቸውን የሰሩ በእኛ ጥላ ስር የተከለሉ እነማን ናቸው? ________________________________________

____________________________________________________________

እነዚህን ጥቅሶች በካርዶቻችሁ ላይ ፃፏቸው በዚህ ቃል ውስጥ እግዚአብሄር እናንተን በውሀ ዳር የተተከላችሁ ፣ህያው እና ጠንካራ፣ለብዙዎች ለተጎዱት ጥላ እንዲሁም መጠጊያ ሌሎች በእናንት ውስጥ ደህንነት እና መፅናትን የሚያበኙባችሁ ሰዎች እንዴት መሆን እንደምትችሉ ያሳያችኂል ፡፡ልምምዳችሁንም በካርዱ ጀርባ ላይ ፃፉት እግዚአብሄር ሌሎችን ለመባረክ ስለመረጣችሁ እግዚአብሄርን አመስግኑት፡፡

**ጸሎት፡** ጲጢፋራን እና ቤተሰቡን በዮሴፍ ምክንያት የባረክ ጌታ ሆይ፡፡የእሱ የሆነውን እቤቱን ፣ ንብረቱን ፣እርሻውን ሁሉ ባረክለት ፡፡ያንተን የተባረከ ህልውና ዮሴፍ በቤቱ ይዞለት ገባ፡፡እባክህ የእኔንም አይኖች ክፍተህ እኔን እንዲሁም ፊፅሞ የማያውቁህ እኳ ቢሆኑ በእኔ ህይወት ተባርከው አሳየኝ፡፡ህይወቴም ለሌሎች በረከት በመሆን ዝንባሌ ይኑረው፤ እኔን በባረክበት ታማኝነትህ ሌሎችንም ባርካቸው፡፡እነዚህ የምፀልይላችንም ሁሉ እውነተኛው የበረከት ምንጭ አንተ መሆንህን ይወቁ፡፡________________________________________

## ክፍል 3

***መግቢያ፡*** በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል የእግዚአብሄር ልጆች በመሆናችን ምክንያት በዚህ ምድር ስንኖር ምንም አይነት ችግር አይገጥመንም ማለት አይደለም፡፡ምናልባት ዘፍጥረት 3 ስናጠና የእግዚአብሄር እቅድ እና የእኛ ምርጫ መካከል ያለውን ፍለሚያ እና ሁልግዜ ነፍሳችንን ክፉ እንደሚከታተላት ተመልክተን ነበር፡፡የዘፍጥረት 39 የመጀመሪያዎቹ ስድስት ቁጥሮች ስለዮሴፍ የምስራች ይነግሩናል በተጨማሪም የዮሴፍ እምነት የሚፈተንበት ግዜ እንደመጣ ይነግሩናል፡፡ስለዚህ ይህንን ጥያቄ እንድንጠይቅ እንገደዳለን በእርግጥ በረከት ማለት ሁል ግዜ አስደሳች እና ጥሩ ስሜት ያለው ነገር ብቻ ነውን?

**የቤት ስራ**፡ዘፍጥረት 39 ፡6-23 ያለውን ክፍል እንብቡ፡፡

***መልመጃ፡***

1. ዮሴፍ በቁጥር 6 ውስጥ በምን መልኩ ነው የተገለፀው?______________________________
2. በ ቁጥር 7 ውስጥ የሚገኙት ቀጣይ ቃላት ምንድናቸው? በጲጢፋራ ሚስት በኩል የመጣው ፈተና ምን የያዘ ነበር?______________________________________________________
3. ቁጥር 8 ዮሴፍ ተቃወማት የተናገረውን ቃል በጥንቃቄ በመመልከት የዮሴፍን መልስ ፃፉ____________________________________________________________________

ተጠያቂነቱ ለማን እንደሆነ ነው የተናገረው?_________________________________________

የቤቱ ጌታ ቤት ውስጥ ባለው ነገር ላይ በሙሉ አምኖ ስልጣን ሰጥቶታል ስለዚህ ቤት ውስጥ ስላለው ስለማንኛውም ነገር ይመለከተዋል፡፡ዮሴፍ የቤቱ ሁለተኛ አዛዥ ነበር፡፡ጌታው ከሚስቱ በቀር ሁልንም ነገር ሰጥቶታል ፡፡ስለዚህ ይህንን ጥያቄ ጠየቀ፡_________________________________

____________________________________________________________________________

4. ዮሴፍ ጤነኛ ወጣት ነበረ ቢሆንም ግን ሌሎች ያለፉበትን ፈተና ተቋቁሞ አለፈ፡፡የጲጢፋራ ሚስት ይህን ስለተረዳች ሁልግዜ ይህንን ግብዣ ታቀርብለት ነበር፡፡መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዮሴፍ በቁጥር 10 ላይ ምን ይላል?____________________________________________________
5. ይህ ክፍል ስለ ጲጢፋራ ሚስት ምን ይነግረናል?_____________________________

**በጥልቀት ማየት ፤** እስቲ ተመሳሳይ ታሪክ ወደሚያወራ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ጥቂት ቆይታ እናድርግ፡፡ንጉስ ሰለሞን የምሳሌ መጽሐፍን ለልጁ ጽፎለታል፡፡በምዕራፍ 6 እና 7 ላይ ከማመንዘር ኃጢአት እንዲጠበቅ ያስጠነቅቀዋል፡፡እናንተ ሙሉውን ክፍል ማጥናት ትችላላችሁ ለዚህ ጥናት ግን እስቲ ሰለሞን ልጁን ከዚህ አይነት ከፋት እንዲጠበቅ ከጋለሞቶች እና ከአመንዝራ ሴቶች እንዲጠበቅ የመከረበትን ጥበብ  አብረን እንመልከት፡፡ ምእራፍ 6፡ 20-35 ያለውን ክፍል በጥንቃቄ አንብቡት፡፡ዮሴፍ ምንአይነት ሁኔታ ውስጥ እንደነበረ አትዘንጉ፡፡

1. ሰለሞን ልጁን የቤተቦቹ ምክር እና ትምህርት አላማ ምን እንደሆነ ነው እየነገረው ያለው?_____
   ____________________________________________
2. በቁጥር 24 ላይ ይህ ትምህርት እሱን ከማን ለመጠበቅ እንደሆነ ነው የሚነግረው?_________
   ____________________________________________
3. ቁጥር 26 ሰለሞን ስለአመንዝራ እና ጋለሞታ ሴቶች ምንድነው የተናገረው?_______________
   ____________________________________________
4. ቁጥር 29-35 ከሌላው ሰው ሚስት ጋር መተኛት የሚያመጣው ጣጣ ምንድነው ብሎ ይናገራል?____________________________________________
   ____________________________________________
   ____________________________________________

ንጉስ ሰለሞን ከልጁ ጋር የነበረው ግንኙነት በጣም ግልፅ ነበረ፡፡የእውነት ቃሎቹም ለእኛ ትምህርቶች ሆነውናል፡፡እነዚህንም ቃሎች እንዲመሩን፣ እንዲናገሩን፣ እንዲቆጣጠሩን በልባችን መያዝ ይኖርብናል፡፡

<u>**ክፍል 4**</u>

**መልመጃ፡** ወደ ዘፍጥረት 39 ፡11 ተመለሱ

1. አንድ ቀን ዮሴፍ ወደ እለት ተእለት ስራው ሲሄድ ምን ገጠመው_______________________

____________________________________________

ከእሷ ጋር እንዲተኛ ትእዛዝ ሰጠቸው፡፡ዮሴፍ ጥሏት ሸሸ ነገር ግን ሲሸሽ ________________ነበር ጥሎ የሸሸው (ቁጥር 12) የጲጢፋራ ሚስትም ይህን እድል ተጠቅማ የውሸት ታሪክ የምትፈጥርበት ምክንያት አገኘች፡፡

ዮሴፍ የሷን ፈቃድ ባለመፈፀሙ ምክንያት ተበሳጭታ እሱን የሚጎዳ የሀሰት ወሬ አዘጋጀች ፡፡ይህ እሷ ያዘጋጀችው የሀሰት ወሬ ምን ነበር ከቁጥር 13-18? __________________________

____________________________________________

2. በቁጥር 19 ላይ ጲጢፋራ ወደ እቤት ሲመጣ ምን ነበር የነገረችው? ____________________

______________________________________________________________________________

የእርሱ ምላሽ ምን ይመስል ነበር?______________________________________________

አልተደነቃችሁም (ምሳሌ 20) ?______________________ ___________________________

3. ጲጢፋራ በዮሴፍ ላይ ምን እርምጃ ወሰደበት?________________________________________

**ገለፃ፤** በዘፍጥረት 39 የመጀመሪያው ቁጥር ውስጥ ዮሴፍ ምን ያህል የተከበር ሰው እንደነበር አንመለከታለን ፡፡በጣም ውብ ፣ሊታመኑት የሚችል፣ግልፅ፣እውነተኛ ፣ታማኝ የሆነ ወጣት ነው፡፡ከጌታው ሚስት የቀረበለትን የዝሙት ግብዣ የሚያመጣበትን መዘዝ በማወቅ ተቃወማት ፡፡አሁን ዮሴፍ እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሯል፡፡በሙሉ ልቡ አምኖ ከዚህ በፊት በቤቱ ሁሉ ላይ የሾመው በዮሴፍ እንደተባረከ ያመነው ጌታው አሁን የሚስቱን ውሸት ሰምቶ ዮሴፍን እስር ቤት ጥሎታል፡፡ዮሴፍ የታሰረው የንጉሱ እስረኞች የሚታሰሩበት ቦታ ስለነበር ምንም አማራጭ የለውም፡፡

ግን ለምን? ዮሴፍን የመሰለ ጥሩ ሰው ላይ እንዲህ አይነት ነገር ለምን ደረሰበት? እግዚአብሄር ወዴት አለ? እግዚአብሄር ከሱ ጋር የሚሆነው ዮሴፍ በሰላም በነበረበት ወቅት ብዙ ሀብታም ሰዎች በዙሪያው በነበሩበት ግዜ ብቻ ነውእንዴ? እደዚህ አይነት ጥሩ ሰው ላይ እንደዚህ አይነት ክፉ ነገር እንዲደርስበት እግዚአብሄር ለምን ፈቀደ? እናንተም እግዚአበሄር የሚሰራው በዚህ መልኩ ከሆነማ በመጀመሪ ከእርሱ ጋር መወያየት ያለብኝ ነገር አለ በላችሁ ሳታስቡ አትቀሩም ፡፡

እስቲ እራሳችሁን ዮሴፍ አድርጋችሁ አስቡ ፡፡በእስርቤት ውስጥ በማህበረሰቡ ውስጥ ክፉ ማንነት ካላቸው ስዎችመሀል ተጥላችሁ አስቡ፡፡በጭንቅላታችሁ ውስጥ የሚመላለሰው ጥያቄ ምንድነው የሚሆነው?አምላክ አለኝ ብላችሁስ እርዳኝ ብላችሁ ወደእርሱ ትጮሀላችሁ? ወንድሞቻችሁ ያደረሱባችሁ አልበቃ ብሎ አሁን ደግሞ ይሄ የባሰ ነገር መጣ፡፡

______________________________________________________________________________

**ጥልቅ ምልከታ፡** ቅን ያልሆነ ፍርድ ተመልክተናል፡፡ እኛ ግን እኛን በሚያንገላቱን ላይከነሱ የባሰ መራራ እንሆንባቸዋለን፡፡በ1 ጴጥሮስ 2፡21-25 ይህንን እኛ “ከፍተኛው ጥሪ” እንለዋለን፡፡እስቲ ይህንን ጥቅስ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ ጴጥሮስ ምሳሌችን የሆነውን እየሱስን አንድንመለከተው ይፍለጋል፡፡

1. ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ክረስቶስን ልትመስሉ ተጠርታችኋል ይለናል “የተጠራችሁለት ለዚህ

ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ______________ እንድትከተሉ _____________ ትቶላችሁ ስለ እናንተ _______ ተቀብሎአልና።"

2. ከዛም ጴጥሮስ ኢሳያስ 53:9 ይጠቅስልናል ።እየሱስ ምንም ኃጢአት አላደረገም ይለናል ።ሲያስቃዩት እና ሲሰድቡት ምን አደረገ ይለናል?________________________________

3. ቁጥር 23 እንዲህ እያለ ይቀጥላል____________________________________ይህን ሲል ምን ማለቱ ነው? እየሱስ ተሸክሞ የነበረው የአባቱን ፈቃድ ነበር።በፍርዱ ትክክል እና ፃድቅ ለሆነው አባቱ እራሱን አሳልፎ ሰጠ።

4. እየሱስ እኛ________________ ኃጢአታችንን በስጋው በመስቀል ላይ ሊሸከም ፈቃደኛ ነበር (ቁጥር 24) __________ ሞተን _________ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋ__________ በእንጨት ላይ ተሸከመ፤" እኔ እና አናንተ እርሱ በሰራልን ስራ ተፈውሰናል።ከአባት ጋር የነበረንን የተበላሸ ግንኙነት አደሰልን።እየሱስ የሰራላቸውን ከመኑ ኃጢአተቸው ከእነሱ ጋር አይኖርም።በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ። እንደ _________ትቅበዘበዙ ነበርና፥ አሁን ግን ወደ__________እና______ተመልሳችኋል።(ቁጥር 25)

**ክፍል 5**

**መልመጃ:** ወደ ዘፍጥረት 39 ምዕራፉ ዮሴፍ በእስር ቤት እያለ ይደመደማል።

1. እንደገና በቁጥር 21 ላይ አምስት ያክል ተመሳሳይ ቃላትን እናገኛለን።እዚህ አምስት ቃላት ምንድናቸው?________________________________________________
2. ቁጥሩ በመቀጠል ዮሴፍ በእስር ቤት እያለ እግዚአብሄር በምን አይነት መልኩ ህልውናውን ይገልጥለት እንደነበር ይነግረናል።___________________________________
3. ቀጥር 23 የዮሴፍ ባህሪ በእስር ቤቱ አዛዥ በመታወቁ ምንክንያት የእስር ቤቱ ኃላፊ ምን አይነት ኃላፊነት ለዮሴፍ ሰጠው?______________________________________
4. የእስር ቤቱ ኃላፊ ዮሴፍ በእርሱ ኃላፊን ስር በመሆኑ በጣም ሳይደሰት አይቀርም ።ቁጥር23 የእስረኞቹ አለቃ _______________________________________
   
   እግዚአብሄር ከዮሴፍ ጋር እንዳለ እና በሚያደርገውም ነገር ሁሉ እንደሚያከናውንለት አውቋል።
5. ጲጢፋራ እና የእስር ቤሩ ኃላፍ በዮሴፍ ህይወት የተመለከቱት ተመሳሳይነት ያላቸው ነገሮች ምንድናቸው (ቀጥር 23)_____________________________________

**ገለፃ:** ዮሴፍ ምን አድርጎ ይሆን በእስርቤቱ ሃላፊ አይን ውስጥ የገባው።እንደ እስረኛ ምን አይነት ነገር ቢያደርግ ነው ።ዮሴፍ የሀሰት ክስ ሰለባ እና ፍርድ የተጣመመበት ሰው ነው።በጣም

በተቆጣው የቀድሞው አስተዳዳሪው ነው ወደእስረቤት የተረወረው፡፡በዚህ እስር ቤት ውስጥ ምን ያክል እንደሚቆይ አላወቀም ምናልባትም እስሩ እድሜ ልክ ሊሆን ይችላል ፡፡መርሳት የሌለብን ነገር ደግሞ ዮሴፍ የሰው ሀገር ሰው ለሀገሩ እንግዳ መሆኑን ነው፡፡የግብፅ ባህል እና ህዝቡ ባጠቃላይ ዮሴፍ በአባቱ ቤት ይኖርበት ከነበረው የዘላንነት (አርብቶ አደርነት) ህይወት በጣም ይለያል ፡፡ግብፃውያን የሰለጠኑ ፣የተማሩ ያደጉ ህዝቦች ናቸው፡፡ፈርኦን ደግሞ  የግብፅ አስተዳዳሪ ነበር፡፡

ከዮሴፍ ጋር ብትታሰሩ ኖሮ ስለዮሴፍ  ምን ትታዘቡ ነበር? ስለእርሱስ ምን ትመሰክሩ ነበር?ሌሎች እንደመሰከሩት እናንተም በርግጥ እግዚአብሄር ከእሱ ጋር ነው ብላችሁ መመስከር ትችሉ ይሆን ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ግላዊ ትግበራ፡**

1. እስቲ ወደ 1ጴጥሮስ 3፡9 ተመለሱ፡፡ዮሴፍ ልንከተለው  የሚገባ ምሳሌ ያለው ሰው ነው፡፡የእግዚአብሄር ሰው እንደሆነ እና የብዙዎችን አይን የማረከ ሰው እንደነበር ይታወቃል፡፡በእሱ ላይ ስልጣን የነበራቸውን ሰዎች አይን እንደማረከ ተመልክተናል፡፡ቁጥር 9 ዮሴፍ ወንድሞቹ ከሸጡት ግዜ አንስቶ የሚኖረው ህይወት ተመሳሳይ ነው አሰስቲ ይህንን ቁጥር በዝርዝር ፃፉት____________________________________________

   __________________________________________________________

2. ዮሴፍ ህይወቱን የሚመለከተው የሌሎችን ህይወት ሊባረክበት በእግዚአብሄር እንደተጠራ ነው፡፡ለሌሎች የሚያሳየው መልካምነት የተመሰረተው እነሱ በሚያደርጉለት መልካም ነገር  ላይ አይደለም፡፡ይኖር የነበረው ልክ እንደ እየሱስ እራሱን ለታመነው እና በፅድቅ ለሚፈርደው አምላክ አሳልፎ በመስጠት ነው፡፡(1ጴጥሮስ 2፡23)፡፡እነዚህ የዮሴፍ ህይወት ተሞክሮ ህይወታችሁን ምን ያህል  ፈተነው?________________________________________

   __________________________________________________________

3. ዝንባሌአችሁ፣ የቃላት አጠቃቀም ምርጫችሁ ፣እንዲሁም በድርጊት የሚገለጠው ሀሳባችሁ በሌሎች ሰዎች ህይወት ውስጥ  ምንያህል ልዩነት ይፈጥራል?__________________________

   __________________________________________________________

4. እራሳችሁን ለሌሎች ሰዎች በረከት አድርጋችሁ እንዳትኖሩ የሚገዳደሯችሁ ነገሮች ምንድናቸው?________________________________________________

**ጸሎት፡** ጌታ ሆይ እንደ ዮሴፍ መሆን እፈልጋለሁ፡፡ጌታሆይ በሌሎች ህይት ለውጥ ማምጣት እፈልጋለሁ፡፡ህይወቴ በሙሉ በአንተ ፍቅር ተሞላ እና በዚህም ምክንያት ሌሎች ያንተን ፍቅር በእኔ ህይወት አይተው ወደአንተ ይሳቡ ዘንድ እፈልጋለሁ ፡፡ አስቸጋሪ እና ክፉ ቀኖች ሲያጋጥሙኝ ከመመማረርና ተስፋ ከመቁረጥ ጠብቀኝ፡፡በእኔ ላይ ስልጣን ኖሯቸው ለሚበድሉኝ መልካም ቃል እናገራቸው ዘንድ በዚህም ውስጥ የአንተን ፍቅር መመልከት ይሆንላቸው ዘንድ አስችለኝ፡፡________________________________________

# ትምህርት ሶስት

# ሚስጥሩ ለእግዚአብሄር ነው

## ዘፍጥረት 40-41

---

**የትምህርት ሶስት ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 3፡ዘፍጥረት 40-41

- የሌሎች ህልም
- ዮሴፍ ህልማቸውን ፈታላቸው
- የፈርኦን ህልም እና ፍቺው
- የዮሴፍ አብይ እቅድ ለግብፅ
- ዮሴፍ በግብፅ ላይ ጌታ ሆነ

## መግቢያ

ዮሴፍ በብዙ መከራዎች ውስጥ አልፏል ነገር ግን እግዚአብሄር ታማኝነቱን አላጓደለበትም፡፡አንድ እግዳ ነገር ተከሰተ፡፡በእስር ቤት ውስጥ ምን አንደተከሰተ እና እግዚአብሄር እንዴት ግብፅን ለመታደግ እንደተጠቀመበት፤ታሪኩን ተከታታሉ፡፡

በዮሴፍ ህይወት ውስጥ ያለፉት ነገሮች በሙሉ በህይወቱ ማለፍ ይገባቸው ከሆነ ያስግገርማል፡፡እግዚአብሄር መከራ እና ስቃዩን ሊያስወግድለት አይችልም ነበር?ታዲያ ለምን ዝም አለው? ነቅታችሁ ዮሴፍ ለመከራው የሰጠውን ምላሽ ተመልከቱ፡፡ባለፈባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ ዝንባሌውን ተመልከቱ፡፡በአስርቤት ውስጥ ባለስልጣናት ለነበሩት ሰዎች የነበረው አመለካከት ተመልከቱ ፡፡አብረውት እስረኛ ለነበሩት የነበረውን አመለካከት እና ክብር ልብ በሉ፡፡ለተሰጠው ኃላፊነት ሌለው ቀርቶ ከርኦን እንኳን ለተሰጠው ኃላፊነት ምን አይነት ዝንባሌ እንዳለው ተመልከቱ፡፡

ዘፀአት 40 እና 41 የታሪኩን ድምዳሜ አይነግሩንም፡፡ግዜ ወስዳችሁ የዮሴፍን ታሪክ በሙሉ በማጥናት በነዚህ ሁሉ ዘመናት እግዚአብሄር ለዮሴፍ ምንያህል ታማኝ እንደነበር ምስክርነታችሁን ስጡ፡፡

## ክፍል 1

***መግቢያ፤*** ትምህርት 2 በጲጢፋራ ሚስት ውሸት የተነሳ ዮሴፍ እስር ቤት እንደተጣለ ተነጋግረን ትምህርት ሁለትን አጠናቀናል፡፡በጌታው ቤት በሁሉ ነገር ላይ እምነት ተጥሎበት በክብር ተሾሞ የነበረ ሰው ነበር፡፡ነገር ግን በተደጋጋሚ የተደረገለትን የዝሙት ግዣ እምቢ ብሎ ሸሸ፡፡እሷም ዋሸች ፤ባሏም የሚስቱን ውሸት አምኖ አሁን ዮሴፍ መቼ እንኳን እንደሚፈታ በማያውቅበት እስር ቤት ውስጥ ተጥሏል፡፡

ዮሴፍ እስር ቤት ይጣል እንጂ እግዚአብሄር አሁንም ለዮሴፍ ታማኝ ነው፡፡መጽሐፍ ቅዱስ ምንም እንኳን ዮሴፍ በእሰር ቤት ቢሆንም እግዚአብሄር ከእሱ ጋር ነበር፡፡እግዚአብሄር ለዮሴፍ መልካምነቱን ያሳየው ነበር በእስርቤቱም ኃላፊ ፊት ሞገስን ሰጥቶት ነበር በዚህም ምክንያት በእስር ቤት ውስጥ ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር፡፡የእስርቤቱም ኃላፊ እግዚአብሄር ከዮሴፍ ጋር እንደነበር እና የሚሰራውን ሁሉ ያከናወንለት እንደነበር አይቷል፡፡

ነገር ግን በእስር ቤት ውስጥ ሆኖ በጣም የተሳካለት ሰው ቢሆን እንኳ ምን ለውጥ ያመጣል፡፡እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር ካለ ዮሴፍን ከእስርቤት አያስፈታውም ነበር?አንድ ሰው ምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ስሜቱ ተመሳሳይ ከሆነ ምንይደረጋል፡፡ስለዚህ እንደዚህ ብለን እንጠይቃለን እግዚአብሄር ካለንበት ሁኔታ ውስጥ ነፃ ያወጣናል ወይንስ ባለንበት ሁኔታ ውስጥ ይመጣልናል?

**የቤት ስራ፤** ታሪኩ ዘፍጥረት 4 እና 41 ላይ ለግዜው ይቆማል፡፡ቀሪዎቹን የምናጠናቸውን ክፍሎች መጨረስ ስላለብን ሁሉንም ተምህርቶች በጥልቀት አንመለከታቸውም፡፡በመልመጀው ያሉት ጥያቄዎች ይህንን ምእራፍ በአግባቡ እንድታጠኑት ይረዳችኋል፡፡ስለዚህ እናንተም አጥኗቸው፣አንብቧቸው፣በማስታወሻ መያዣችሁንም ቀጥሉ ምክንያቱም ለወደፊቱም መጽሐፍ ቅዱስን ስታጠኑ ይጠቅሟችኋል፡፡ዘፍጥረት 40 በማንበብ ጀምሩ፡፡

***መልመጃ:*** ይህ ክፍል ስለሁለት በእስር ላይ ስላሉ ባለስላጣናት የሚተርክ ክፍል ነው፡፡

1. እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው ያጠፉትስ ጥፋት ምንድነው?____________________________

______________________________________________________________________

2. መጨረሻቸውስ ምንድነበር ?______________________________________________

   የእስርቤቱ አዘዥ በማን እንዲጠበቁ ነበር አሳልፎ የሰጣቸው?______________________

3. በቁጥር 5 መሰረት ምን ተፈጠረ?____________________________________________

4. ቁጥር (6-8) ዮሴፍ በንጋታው ጠዋት ምን አስታወቃቸው?________________________

   ምን ጠየወቃቸው?___________________________________________________

   መልሳቸውስ ምን ነበር?_______________________________________________

5. ዮሴፍ የህልሙ ፍቺ ከእግዚአብሄር ዘንድ እንደሆነ አምኗል።ምን ነገራቸው (ቁጥር 8)? ___

   ______________________________________________________________

6. ቁጥር 9-11 የጠጅ አሳለፊው ህልም ምን ነበር? ________________________________

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

7. የዮሴፍ ፍቺስ ምን ነበር ቁጥር12-14?_________________________________________

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

8. በቁጥር 14 ላይ ጠጅ አሳላፊውን ዮሴፍ የጠየቀው ምን ነበር? ______________________

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

9. በተጨማሪ ምን ዮሴፍ ምን ነገራቸው ቁጥር 15?______________________________

   ______________________________________________________________

10. ቁጥር 16-17 እንጀራ አበዛው ምን ህልም አየ?_______________________________

    ______________________________________________________________

11. በቁጥር 18-19 ላይ የዮሴፍ ፍቺ ምን ነበር?___________________________________

    ______________________________________________________________

12. የነበረው ድግስ ምንን አስመልክቶ ነበር ነበርቁጥር 20?____________________________

    ጠጅ አሳላፊለውን ምን ገጠመው ?______________________________________

    እንጀራ አበዛውስ?_______________________________________________

13. ዮሴፍ ህልሙን ሲፈታላቸው ለእያንዳንዱ እንደነገራቸው እንደዛው ሆነባቸው።በቁጥር 23 ላይ የነበረው ችግር ምን ነበር?____________________________________________

<u>ክፍል 2</u>

***መግቢያ*** ፤ አሁንም ዮሴፍ በድ*ጋሚ* ግፍ እየተፈፀመበት ነው ::ጠጅ አሳላፊው በዚህ ሶስት ቀን ውስጥ በሆነለት ነገር በጣም በመደሰቱ ምክንያት ዮሴፍ ለፈረኦን እንዲያቀርብለት የጠየቀውን ሁሉ ሊያስታውሰው አልቻለም።ተስፋቢስ ሆኖ በነበረበት ሁኔታ ውስጥ የምስራች የነገረውን ዮሴፍን እንኳን ለንጉሱ ሊነገርለት ሊያመሰግነው እንኳን አልመጣም ::እናንተስ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ሆናችሁ የረዳችሁን ፤ያበረታታችሁን ሰው የረሳችሁበት ሁኔታ ይኖር ይሆን ?

**የቤት ስራ፡** ዘፍጥረት 41፡1-40 ያለውን አንብቡ።

***መልመጃ*** ፤ እግዚአብሄር አሁንም ለሰዎች በህልም ይናገራል ::.ይህንንም ሁኔታ በዘፍጥረት 37 ዮሴፍ ስለተመለከታቸው ሁለት ህልሞቹ ከቤተሰቦቹ *ጋ*ር ሲነ*ጋ*ገር እንመለከታለን።በምእራፍ 40 ደግሞ ጠጅ አሳላፊው እና እንጀራ አበዛው ህልም ሲያልሙ እንመለከታለን።አሁንም ከሁለት አመት በኋላ ህልሙ ቀጥሎ እመለከታለን።በዚህ ሰአት በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ህልም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።ህልሞቹ በአግባቡ ከተተረጎሙ የባለ ህልሙን የወደፊት እጣ ይወስናሉ።ይህንን ጥናት ስናጠና መርሳት የሌለባችሁ ነገር ብዙ የምስራቅ አገር ነዋሪዎች የአየር ሁኔታቸው የእህል ምርታቸው በሙሉ ከመለኮዊ ጣልቃ ገብነት *ጋ*ር የተያያዙ ናቸው።የረሀቡ ህልም ትንታኔ ፈፅሞ ከዚህ ምድር *ጋ*ር የተያየዘ ጉዳይ አይደለም።

1. ቁጥር 1- 4 በዚህ ግዜ ህልም ያየው ማነው?____________________________________
   ህልሙስ ምን ነበር ?____________________________________________________
   __________________________________________________________________
2. ፈርኦን እንደገና ተኛ ሌላ ህልምም አይቶ ተነሳ ያየው ህልም ምን ነበር ?______________
   __________________________________________________________________
   __________________________________________________________________
3. ቁጥር 8 ላይ ፈርኦን ምን አደረገ ?____________________________________________

ለህልሙ ፍቺ መፈለጉ የጠቀመው ነገር ምን ነበር?____________________________________

**ትምህርት:** በመጨረሻ ጠጅ አሳላፊው በእስርቤት ውስጥ ከመለቀቁ በፊት ስላጋጠመው ነገር አስታወሰ።ለፈርኦንም በእስርቤት ውስጥ አብሮት ታስሮ ስለነበረው የእስረኞቹ አለቃ አገልጋይ ስለሆነው ዕብራዊ ወጣት ነገረው።ፈርኦንም ዮሴፍን ከእስር ቤት አስጠራው።ከእስርቤት ሲያስጠራው ፀጉሩን ተላጭቶ ፣ምናልባትም ገላውን ታጥቦ ፣ልብስ ቀይሮ ነው በንጉሱ ፊት የሚቀርበው።

**መልመጃ:** ከዘፍጥረት 41፡15 ጀምራችሁ አንብቡ

1. ከዮሴፍ የፈለገው ምን ነበር?__________________________________________
2. የዮሴፍስ ምላሽ ምን ነበር(ቁጥር 16)?____________________________________
3. ቁጥር 17-24 ፈርኦን ህልሙም ለዮሴፍ አካፈለው።በቁጥረ 24 ላይ በመጨረሻ ምንድነው ያለው?______________________________________________________
4. ቁጥር 25፡ ዮሴፍ የፈርኦንን ህልም ከመተርጎሙ በፊት ሁለት አስተያየቶችን ተናገረ።

   ሀ. ______________________________________________________

   ለ .________________________________________________
5. ቁጥር 26-27 የህልሙ ፍቺ ምን ነበር? እግዚአብሄር ምን ሊያደርግ ነው?____________

   __________________________________________________________
6. ዮሴፍ ለፈርኦን የህልሙም ፍቺ በራሱ ቃል ነገረው።ለፈርኦን እግዚአብሄር ምን ገለጠለት አለ?______________________________________________________

   __________________________________________________________

   ________________________________________________

**<u>ክፍል 3</u>**

**ትምህርት** ፡ እግዚአብሄር በመላው ግብፅ ሰባት የጥጋብ አመታት ከዛም ቀጥሎ ደግሞ ይህንን የጥጋብ ዘመን የሚያስረሱ ሰባት የረሀብ አመታት እዘጋጅቷል። በቁጥር 32 ላይ እንደተነገረን ደግሞ እግዚአብሄር እነዚህን ህልሞች በሁለት መልኩ የተናገረበት ምክንያት 1. ነገሩ ከእግዚአብሄር ዘንድ የተቆረጠ ስለሆነ እግዚአብሄርም ይህንን እቅዱን ያለጥርጥር ስለሚፈፅም። 2..ይህንን እቅዱን በፍጥነት ስለሚፈፅም።

**መልመጃ:** በእነዚህ ሁለት ቀጣይ ቁጥሮች ውስጥ ዮሴፍ ለፈርኦን ቀጥተኛ መመሪያ ነው የሰጠው።

1. ዮሴፍ እቅዱን ለፈርኦን አቀረበ(ቁጥር 33-36)

   ሀ. ፈርኦን ይህንን ኃላፊነት የሚሰጠው ሰው ባህሪ ምን መምሰል አለበት?____________

   ______________________________________________________

ለ. ፈርኦን ሊሾማቸው የፈለገው ሌሎቹ ሰዎች እነማናው የሚጣቸውስ ስልጣን ምንድነው ቁጥር 34-36?________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

2. ፈርኦንና ባለስልጣናቱ ለዮሴፍ እቅድ ምላሽ የሰጡት እንዴት ነበር?____________________
3. በቁጥር 38 ላይ ያሳሰባቸው ነገር ምን ነበር?______________________________________
4. ቁጥር39 የፈርኦን ውሳኔ ምን  ነበር?____________________________________________
5. ለየትኛው የዮሴፍ ባህሪ  ነበር ፈርኦን  እውቅና የሰጠው?____________________________

_____________________________________________________________________

6. የዮሴፍ ኃላፊነት ምን ነበር?__________________________________________________
7. የሚገዛለት ማነው?________________________________________________________
8. ዮሴፍስ ለማን ይገዛል ?_______________________________________________________

**ገለፃ፡** ወጣቱ ዮሴፍ በአንድ ወቅት ባሪያ እና እንግዳ ሆኖ በመጣበት ሃገር ውስጥ ጥቂት ቆይቶ የሀገሪቱ ሁለተኛ ሰው ሆኗል ።ከፈርኦን በስተቀር ሁሉም ይገዙለታል ።

1. ታዲያ ምን ታስባላችሁ ? ካሳለፋቸው ከእነዛ  አስቸጋሪ አመታት የተነሳ ፈርኦን የሰጠው ይህ ስፍራ ይገባዋል? በቀላሉ ምን ማለት ነው የጨረሻው በረከት የመጀመሪያውን ስቃይ ያስረሳል?________________________________________________________

_________________________________________________________________

2. ጥያቄ መጠየቅ ምን ችግር አለው?____________________________________________

_________________________________________________________________

ምናልባት ከዮሴፍ ጋር መመሳሰል ለእናንተ ላይቸግራችሁ ይችላል ምክንያቱም የሚገባችሁ የስራ እድገት አልፏችሁ ሊሆን ይችላል።ወይንም ደግሞ ከፍተኛ ማእረግ ሊሰጣችሁ ሲገባ ይህም አልፏችሁ ይሆናል።ምናልባት ደግሞ እናንተ የተሻለ ብቃት ኖሯችሁ የስራ እድገት የሚገባው ለእናንተ ሆኖ ሳለ በብቃት ከእናንት ለሚያንስ ሰው በግፍ ተሰጥቶ ይሆናል ።ምናልባት ዮሴፍ በወንድሞቹ እንደተጎዳ  እናንተ ደግሞ በሌሎች ተጎድታችሁ ይሆናል። ቤተሰቦቻችሁ ምንም ዋጋ የሌለው ተራ ህልመኛ አድርገው ቆጥረው እውጥተው ጥለዋችሁ ይሆናል ።ምናልባት ደግሞ ቤተሰብ ውስጥ የማትጠቅሙ እና ዋጋ የሌላችሁ አድርገው ቆጥረዋችሁ ዘመድ ጋ ተጠግታችሁ እንድትኖሩ በገዛ ቤተሰቦቻችሁ ተገፍታችሁ ተጥላችሁ ሊሆን ይችላል።ያለችሁበት ሁኔታ በጣም

ውስብስብ እና አስቸጋሪ ሊሆነን ይችላል፡፡ምናልባት ተማሪዎች ከሆናችሁ የመጨረሻውን ትንሽ ውጤት አግኝታችሁ ይሆናል፡፡ወይ ደግሞ በጣም ብዙ ውለታ የዋላችሁት ሰው ሌላው ቀርቶ ምስጋና እንኳን ነፍጓችሁ ይሆናል፡፡ህይወታችሁን እንኳን ስለሱ አደጋ ላይ የጣላችሁለት ሰው ምንም ስፍራ ላይሰጣችሁ ይችላል፡፡

ይህንን የዮሴፍን ታሪክ ካጠናን በኋላ ግን በህይወታችን ላለንበት ሁኔታ የምንሰጠው ምላሽ የራችንን ድርሻ ይሆናል ፡፡ጲጢፋራም ሆነ የእስርቤቱ አዛዥ ያረጋገጡት አንድ ነገር እግዚአብሄር ከዮሴፍ ጋር መኖሩን ነው፡፡የእግዚአብሄር በረከት በእርሱ ላለይ ነበር የሚሰራውን ሁሉ ያከናውንለት ነበር፡፡ባለፈበት የህይወት ልምዶቹ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሄር ፈርኦን ለሚሰጠው ስፍራ ያዘጋጀው ነበር፡፡በመጀመሪያ በጲጢፋራ ቤት እና አርሻ ላይ ስልጣን እና ኃላፊነት ተሰጠው፡፡ቀጥሎ ደግሞ እስር ቤት ውስጥ ለሚሆነው ነገር ሁሉ ኃላፊነት ተሰጠው፡፡አሁን ደግሞ ለመላው ግብፅ መትረፍ ኃላፊነት ተሰጠው፡፡እዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነን የሚቀጥለው ነገር ማጉረምረም እና ማማረር ነው እንጂ እንደ ዮሴፍ ነገሮችን በብቃት መወጣት ያስቸግራል፡፡በምንሰራው ስራ ውስጥ የእግዚአብሄርን በረከት መመልከት መቻል በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ይህ ለከፍተኛ ጥሪ ያዘጋጀናል፡፡ "ከነገሮች በላይ ሂድ" ልንል አንችላለን ይህ በአብዛኛው ተመሳሳይ ሀሳብ ነው የያዘው ፡፡የተጠራነው ከነገሮች እና ከሁኔታዎች በላይ አልፈን እንድንሄድ እና በነገራችን ሁሉ እግዚአብሄርን እንድናይ አና እንድንታመን በእርሱም ስኬታማ እንድንሆን ነው፡፡

**ግላዊ ትግበራ፡** እስቲ ጊዜ ወስዳችሁ በግል ህይወታችሁ ባሉት ሁኔታዎቸች ላይ ይህንን በተግባር ተለማመዱባቸው፡፡

1. እስቲ የተናቃችሁበትን ዘቅተኛ ግምት ተሰጥቷችሁ የነበረበትን ወቅት አስታውሱ፡፡በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነችሁ ምን አስታወሳችሁ?______________________________
2. ምን ጠብቃችሁ ነበር?________________________________________
3. በትክክል በዛን ወቅት ምን ተፈጠረ?__________________________________
4. ለዛ ሁኔታ የሰጣችሁት ምላሽ ምን ይመስል ነበር?____________________________
5. በተለየ መልኩ በዛ ሁኔታ ውስጥ ምን አደረጋችሁ? ለምን?________________________

   ________________________________________________________
6. ያለፈውን ሁኔታችሁን ስትገልፁ አሁን ላላችሁበት ሁኔታ ምን ተማራችሁበት?________

   ________________________________________________________
7. ይህንን ገለፃ ስታደርጉ ባላችሁበተ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሄርን በየትኛው የህይወታችሁ

ክፍል አብሯችሁ አገኛችሁት?________________________________________________

________________________________________________________________

**ጸሎት፡**ኦ! ጌታ ሆይ እንዳንድ ግዜ በራሴ እውቀት እና ችሎታ ለይ በመደገፌ ይቅር በለኝ፡፡ስልጣን እና ኃይል እንደሚያስፈልገኝ አመንኩ አሁኑኑ እንደሚያስፈልኝ አመንኩ፡፡ዮሴፍ የትህትና ምሳሌ ነው፡፡ጲጢፋራንም ሆነ የእስረኞቹን አለቃ እንደሚገባ አግልግሏል፡፡ለእኔም አገለግላቸው እና እገዛለቸው ዘንድ በስራ ቦታዬ አለቆችን ፣አስተዳዳሪዎችን፣ባለስልጣኖችን በህይወቴ ሰጥተኸኝ ነበር እኔ ግን እንደዮሴፍ አላደረኩም፡፡ዮሴፍ በእርሱ ህይወት እና ከእሱ ህይወት ውጪ ስራ እየሰራህ እንዳለህ አምኖ ነው የኖረው፡፡ከእኔም ጋር እንዳለህ እረዳ ዘንድ አባክህ ልቤን ክፈትልኝ፡፡የምትሰጠኝ ስኬት ሌሎችን ወደአንተ የሚያመጣቸው ይሁን፡፡________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**ክፍል 4**

***መግቢያ፡*** ፈርኦን በግብፅ ለሚፈጠረው ነገር በሙሉ ኃላፊነቱን ዮሴፍ እንዲወስድ መርጦታል፡፡ዘፍጥረት 41፡41-45 ዮሴፍ አዲሱን የሹመት ስራውን እንደጀመረ ይነግረናል፡፡አንዳንዴ በእኛም ጉባኤዎች ውስጥ አንድ ሰው የአገልግሎት ሹመት ሲሰጠው እንደዚህ አይነት ስርአቶች ይፈፀማሉ፡፡ በመጀመሪያ ፓስተሩ ይመረጣል ከዚያም ይሾማል፡፡ከዛም በፓስተሩ አንገት ላይ አንገት ልብስ መሳዩ ባለቀለም ጨርቅ ይደረጋል የዚህም ትርጉሙ ከዚህ በኋላ ይህንን ስራ በሀላፊነት የሚሰራው ይሄ አካል ነው የሚል ነው፡፡ፈርኦንም የዮሴፍን መምረጡን እና መሾሙን እሱም ከህዝቡ ምን እንደሚጠብቅ ለህዝቡ አስታወቀ፡፡

**የቤት ስራ፡** ዘፍጥረት 41፡41-57 ያለውን ክፍል አንብቡ፡፡

***መልመጃ፡***

1. ቁጥር 41፡ ፈርኦን ለዮሴፍ ምን አለው?________________________________
2. ዮሴፍ እንደሁለተኛ ሰው አለባበሱ እንዴት ነበር ?

   ሀ. ________________________________________________

   ለ .________________________________________________

   ሐ .________________________________________________

3. በመጨረሻ በሰረገላ ላይ ሆኖ ሁኔታው ምን ሊመስል እንደሚችል አስቡት፡፡እንዴት የሚገርም ነገር ነው፡፡የዮሴፍ በግብፅ ሁሉ ላይ ከፈርኦን ቀጥሎ ሁለተኛ ሰው መሆኑ በአደባባይ ታወጀ ፡፡ፈርኦን ፈርኦን መሆኑን አወጀ ዮሴፍን ለሱ የሚታዘዝ መሆኑን እንደዚሁ፡፡
4. ለዮሴፍ አዲስ ስም ሰጠው፡፡የተሰጠው አዲስ ስም ማን ነው?____________________
5. ፈርኦን ለዮሴፍ ሚስትም ሰጥቶታል ስሟ ማን ይባላል?_______________________

**ገለፃ** ፡ ዮሴፍ ይህ ሁሉ ነገር ይገባዋል ብላችሁ ታስባላችሁ ይህ ሁሉ ግርግር ለዮሴፍ ይበዛበት ይሆን፡፡ወይንስ ምንያህል ታላቅ ሃላፊነት እንደሰጠው አስቡ፡፡ይህ ሁሉ የፈርኦን የአደባባይ ሽልማት ለህዝቡ የሚስተላልፈው መልእክት ምንድነው? ልክ ፈርኦን ሲያልፍ እጅ እንደሚነሱት እና ክብር እንደሚሰጡት ለዮሴፍም የሚደረግለት ተመሳሳይ ነገር ነው፡፡
ከጥቂት ቀናት በፊት ዮሴፍ እስር ቤት ውስጥ እንደነበረ እና በዚያም ስራውን እያከናነ እንደነበር እና ከቀናት በኋላ በዚህ አይነት ሁኔታ ስናየው ለእግዚአብሄር ታላቅነት ክብር እንሰጣለን፡፡ከቆሻሻ እና ውዳቂ ከሞላበት እስርቤት ስቦ አውጥቶ እንዲህ በክብር ስፍራ ያስቀመጠው እግዚአብሄር ነው፡፡

**ማሰላሰል** ፧ መዝሙር 40፡1-3 ዮሴፍ ስለነበረበት ሁኔታ የሚገልፅ ቢሆንም እናንተም ያለፋችሁበትን ሁኔታ የሚገልፁ ቃላትን ልታገኙ ትችላላችሁ፡፡መዝሙረኛው እግዚአብሄር እንደሚሰማው ተማምኖ በችግሩ ወደ እግዚብሄር ስለጮኸውን ጩኸት ይናገራል፡፡ዮሴፍም ብዙ መከራዎችን ታግሷል ከእስማኤላውያን ጋር ወደግብፅ ያደረገው ጉዞ ፣በእስርቤት ያሳለፈው ግዜ እነዚህን ሁሉ አሳልፏል፡፡ይህ አዲሱ የሹመቱ ቀን ነው፡፡ብዙዎች እግዚአብሄር ያደረገለኝን አይተው እግዚአብሄርን እንዲፈሩ እና እግዚአብሄርን እንዲታመኑት አዲስ ዝማሬን በልቤ ጨመረለኝ፡፡ይህንን ቁጥር በካርዳችሁ ላይ ፃፉት፡፡በተስፋ እና በዓላማ ህይወታችሁን ይሞላ ዘንድ ያገልግላችኋል፡፡የእግዚአብሄርን በህይወታችሁ መኖር ያረጋግጡላችኋል ያፅናኗችኋል፡፡ ጥልቁ ጉድጓድ እንደ እስረኛ ቢይዛችሁ እንኳን እግዚአብሄር ፈፅሞ አይተዋችሁም፡፡

**<u>ክፍል 5</u>**

**መልመጃ፡** ዘፍጥረት 41፡46-57

1. ዮሴፍ በፈርኦን ቤት ማገልገል ሲጀምር እድሜው 30 አመት እንደነበር ቁጥር 46 ይነግረናል፡፡እስቲ ይህን የሙሉነት እድሜ ግፁት፡________________________________
________________________________________

______________________________________________________________

2. ቁጥር 50፡ በዚህ ቁጥር ላይ ዮሴፍ እና አስናት በዚህ በዚህ በሙሉነት እድሜያቸው በሁለት ወንድ ልጆች እንደተባረኩ ይነግረናል የልጆቻቸው ስም?

   ሀ. ____________________________ትርጉሙም_________________________

   ለ.______________________________ትርጉሙም_________________________

3. የበረከት እና የመትርፍረፍ አመት ወይንም አመታት የምግብ ፍላጎትን ከማርካት የዘለለ ያላቸው ትርጉም ምንድነው? ውጥረትን፣ሁለንተናዊ ደህንነትን ፣እና አስተሳሰብን ወዘተ አስቧቸው____________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

4. የተትረፈረፈ የአመት ወይንም የሁለት አመት በረከት በህይወታችሁ ላይ የሚያመጣው ለውጥ ይኖራል?______________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

5. የጥጋብ አመት ሲያልቅ የረሀብ ዘመን ይቀጥላል በቁጥር 54 ላይ ስለግብፅ ምን ተነግሮናል?

______________________________________________________________________

**ትምህርት** ፤ ግብፃውያን ልክ የረሀቡ ጉዳት ሲሰማቸው ዮሴፍ ያዘዛቸውን በሙሉ እንዲፈፅሙ ወደመራቸው ወደፈርኦን መጡ፡፡ልክ የረሀቡ ሃይል እየጨመረ ሲመጣ ጎተራዎቹ ተከፍተው እህል ይሸጥ ጀመር፡፡ትንሽ አስቸጋሪ ነገር ተፈጠረ ያም በቁጥር 57 ላይ የተፃፈው በአጎራባች ያሉ ሀገራት በሙሉ ረሀቡ አዳረሳቸው፡፡በዙሪያው ካሉተ ሃገራትም እህል ያለው ግብፅ ብቻ ነበር፡፡ስለዚህ ከሁሉም ሀገራት ወደ ግብፅ  ዮሴፍጋ እህል ለመሸመት ይመጡ ጀምር፡፡ “በምድር ሁሉ ራብ እጅግ ጸንቶ ነበርና፡፡”

**ገለፃ፡** እሺ አሁን አስተሳባችሁን ተጠቀሙ፡፡ይህንን ረሀብ በግብፅ ላይ ያመጣው ማነው?_____________________________________________________________________

እግዚአብሄር የተሰበረውን የአባት እና የልጆቹን ግንኙነት ለማስቀጠል የተጠቀመበት መንገድ ይሆን? ያዕቆብ እና ልጆቹ በከንአን በታላቅ ረሀብ ውስጥ ናቸው ፡፡ዮሴፍ ደግሞ ከተትረፈረፈው ጎተራ እህል ይሰፍራል፡፡ዮሴፍ አባቱንም ወንድሞቹንም ቤተሰቡን ባጠቃለይ ዘንግቷል፡፡ (ቁጥር 51) በአስቸጋሪ ሁኔታ ወደግብፅ ያመጣው በግብፅም ምድር ፍሬያማ ያደረገው እግዚአብሄር እንደሆነ አሳውቆናል፡፡

በዚህ ስፍራ ላይ ዮሴፍ በግብፅ ምድር ስላሳለፈው መከራ እና ስለፅናቱ የሚነግረን ታሪክ እናገኛለን ወደግብፅ ሲመጣ ለባህሉም ሆነ ለህዝቡ ባእድ ነበር ወደዛ ሀገር መምጣቱንም ማንም

አያውቅም ነበር፡፡ቀጥሎ ደግሞ በአመንዝራ እና በወንጀለኛነት ተከሶ እስር ቤት ገብቷል፡፡ነገር ግን አሁንም እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር እንዳለ ተነግሮናል፡፡ነገር ግን አሁን ፈርኦን ካከበረው አንዲሁም ቤተሰብ መስርቶ ልጆች ከወለደ በኋላ "ይህ ሁሉ የሆነብኝ ምን አጥፍቼ ይሆን" የሚል የልብ ጩኸት ይሰማል ፡፡አሁንም በምድሪቱ ላይ ሁለተኛ አዛዥ ሆኖ ባለበት ስፍራ በሌላ መልኩ ሌላ የልብ ጩኸት ይሰማል፡፡ "ይሁሉ እንዲደረግልኝ እኔ ማነኝ፡፡"

በእነዚህ ሁሉ አመታት እግዚአብሄር ፀጋ ከዮሴፍ ጋር ነበር፡፡ከግብፃውያን አማልክት እጅጉን ከሚለየው የአባቶቹ አምላክ እግዚአብሄር ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው፡፡ይህ አምላክ መሀሪ አምላክ ነው፡፡በፍፁም ትቶት አየውቅም በመንገላታት ውስጥ እያለ አንኳን አልተወውም፡፡

እግዚአብሄር እነዚህን ሁሉ የዮሴፍ አስቸጋሪ የህይወት ጉዞዎች እሱን ለመቅረፅ እና ለመስራት እያወቀም ይሁን ሳያውቅ እግዚአብሄር እሱን ዳግም ከአባቱ ፣ከወንድሞቹ ባጠቃላይ ከቤተሰቦቹ ጋር ለመቀላቀል እያሰለጠነበት ያለው መንገድ ነበር፡፡

**ግላዊ ትግበራ፡**

1. መራራ የሆነ መለየት፤ በጣም ከምትወዷቸው ሰዎች ተለይታችሁ ታውቁ ይሆን? አሁን በተለይ ወደልባችሁ የሚመጣ ሰው አለ?______________________________
2. አሁን ደግማችሁ ከተለያያችሁት ሰው ጋር እደገና ለመገናኘት አሁን የበሰላችሁበት ግዜ እንደሆ ታስባላችሁ?________________________________________

   ____________________________________________________
3. ትናንት ያሳለፋችኋቸው ችግሮች ነገን ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገት አስችለዋችሁ ያውቁ ይሆን?___________________________________________
4. የመረረ መለየትን ካደረጋችሁ በኋላ ያለችሁበትን ሁኔታ በምን መልኩ ለውጦታል?_____

   ____________________________________________________

**ጸሎት፡**በራሳችሁ ቃል በልባችሁ ያለውን ጩኸት ለጌታ አቅርቡለት"ይህ ሁሉ አንዲሆንብኝ ያጠፋሁት ምንድነው"?____________________________________________

________________________________________________

እደገና ልባችሁ በምስጋና ይሞላ እና እግዚአብሄር በፀጋው ስለሰጣችሁ ነፃነት ልባችሁን በምስጋና ወደጌታ አንስታችሁ እንዲህ በሉት "እግዚአብሄር ሆይ ይህ ሁሉ እንዲደረግልኝ እኔ ማነኝ"

## ትምህርት አራት

# ትሹን ወንድማችሁን ወደእኔ አምጡት

### ዘፍጥረት 42 እና 43 -ገዢው

---

**የትምህርት 4 ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 4፡ዘፍጥርት 42 -43

- የያዕቆብ ልጆች ወደግብፅ ተላኩ
- እንደ እንግዳ እና እንደ ሰላይ አቀባበል
- የዮሴፍ ልግስና
- ያልታረመ ጥፋት
- በድጋሚ ወደ ከነአን
- ዮሴፍ እና ቢንያም

## መግቢያ

ረሀቡ የጠናው በግብፅ ብቻ አልነበረም ነገር ግን ያዕቆብ እና ልጆቹ በሚኖሩባት በከነአንም ተመሳሳይ ሁኔታ ነበር፡፡ “በግብፅ ምግብ አለ” የሚለው ቃል በምድር ሁሉ ወጥቷል ፡፡ለያዕቆብ እና ለልጆቹ እንዲሁም ለቤተሰቦቹ በሙሉ ይህ ምን ማለት ይሆን? ዮሴፍ ወንድሞቹን ሲመለከት ምን ተሰምቶት ይሆን ፡፡ለወንወድሞቹ ምን አይነት ፊት እንዲያሳያቸው ትጠብቃላችሁ የእናንተ ወንድሞች ቢሆኑና እናንተን በተመሳሳይ መልኩ በድለዋችሁ ቢሆን ምን ታደርጉ ነበር?

ዮሴፍ ያለ ጥፋቱ ታስሯል፡፡ወንድሞቹ በራሳቸው ጥፋት ምንያህል ህሊናቸው እንደተሰቃየ እና የራሳቸው ህሊና አስረኞች እንደነበሩ ተመልከቱ ፡፡እስቲ መርምራችሁ ድረሱበት በዚህ ሁሉ አመት በአንድነት አስተሳስሮ የያዛቸው ነገር ምን ይመስላችኋል? ከህይወት ሙላት ያጎደላቸው ምንድነው

ዮሴፍ በወንድሞቹ ላይ ጠበቅ ያለ እረምጃ ወስዷል፡፡እስቲ ሁኔታውን ተመልከቱ፡፡ምን ነበር የደመደሙት ፈርኦን ስለዚህ ሁኔታ ቢሰማ ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል? ምግብ ይከለከሉ ይሆን አባታቸው ስለተፈጠረው ነገር እውነታውን ያውቅ ይሆን? በፈፀሙት ወንጀል ምክንያት ይታሰሩ ወይንም ይገደሉ ነበር፡፡

ጥያቄው ለኛም ጥያቄ ሆኖ ይቆያል ፡፡እስቲ አስቡ ባደረግነው ወይንም ባላደረግነው ነገር ለእስር የሚዳርገን ነገር ገጥሞን ያውቅ ይሆን? በአንድነት ያስተሳሰረን ምንድነው ?በህይወታችን ያልተፈታ ጥያቄ ምንድነው? እራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል፡የምኖረው በራሴ የጥፋተኝነት ፣የእፍረት አስርቤት ውስት ምንም የመውጫ አማራጭ እንደሌለ አስቤ በዛውስጥ ተዘግቼ ይሆን ከ? ህይወት መንገድ ላይ የጠፋሁት በዚህ ምክንያት ይሆን እስቲ የዮሴፍን ልብ መርምሩ እና አእምሮን የሚያልፈውን የጌታን ሰላም አስቡ፡፡

**ክፍል 1**

***መግቢያ፡*** ዮሴፍ  ብዙ ተጉዟል ፡፡በአስራ ሰባት አመቱ እራሱን በጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ አገኘው በሰላሳ አመቱ ደግሞ እራሱን የፈርኦኖቹ ምድር የግብፅ ሁለተኛ አዛዥ ሰው ሆኖ አገኘው፡፡ሀገሪቱም  የመጨረሻ ደረጃ ላይ ደርሳለች፡፡ላለፉት ሰባት አመታት የምድሪቱ ጎረተራዎች ሁሉ ሞልተው እስኪትረፈረፉ ድረስ ምርጥ ጥራት ያለው እህል አምርታለች፡፡አሁን ደግሞ ከሰባት አመታት በኋላ ደግሞ የረሀቡ ስሜት በግብፅ እና በአጎራባች ሀገሮች በሙሉ ተዳርሷል፡፡ፈርኦን የዮሴፍን ምክር በመስማቱ ምክንያት እና ህዝቡ ምላሽ በመስጠቱ ለዚህ ክፉ ቀን ተዘጋጅተዋል፡፡ይህም ቃል በምድር ሁሉ ወጥቷል "በግብፅ መግብ አለ!"

አስቲ ይህ ዜና ግብፅን በኢኮኖሚ፣በፖለቲካ ሌላው ቢቀር የምርታማነት አምላካቸውንም በማስተዋወቁ ረገድ ምን ያህል እንደጠቀማቸው ግለፁ ______________________________

________________________________________________________________

**የቤት ስራ ፡** ዘፍጥረት 42 አንብቡ

***መልመጃ፡*** በከነአን የነበረው ሁኔታ በጣም አስከፊ ነበር ያዕቆብ ደግሞ በግብፅ እህል እንዳለ ሰምቷል፡፡

1. በቁጥር 1 እና 2 ያዕቆብ ከልጆቹ ጋር የፈራ ይመስላል፡፡ወንድሞቹ ዮሴፍን ከሸጡት ሃያ አመት አልፎታል፡፡ያደጉ እና እድሜያቸው አባታቸውን የሚጦሩበት እድሜ ላይ ነው ያሉት ፡፡እነሱ ስላደረጉት ሁኔታ ምን ታስባላችሁ?____________________________________

   ____________________________________________________________

2. ያዕቆብ ምን እንዲያደርጉ ነገራቸው?______________________________________
3. ቁጥር 3 ከ__________________በቀር ሁሉም እህል ለመሸመት ወደግብፅ ወረዱ፡፡ለምንድነው እሱ እቤት የቀረው?____________________________________________________
4. ቁጥር 6 በግልፅ ዮሴፍ እንደ አስተዳዳሪነቱ እህል ይሸጥ እንደነበር እንመለከታለን፡፡ወንድሞቹም እንደደረሱ ያገኙት ዮሴፍን ነበር፡፡በመጀመሪያ ያደረጉት ነገር

ምንድነው?____________________________________________________________________

5. ቁጥር 7 ላይ ምን ተነግሮናል?___________________________________________________
   ዮሴፍ አውቋቸዋል ነገር ግን እንዳወቃቸው እንዲያውቁ አልፈለገም። ነገር ግን ምን አደረገ?_______________________________________________________________________
6. ምን ጠየቃቸው?________________________________________________________________
7. ወንዱሞቹ ፈልገው የመጡት ምግብ ለመግዛት እንጂ ከልጅነቱ ጀምሮ ሲጠሉት የነበረውን ተወዳጁን መንድማቸውን አይደለም።ሁኔታዎቹ ተለውጠዋል።ጠረጼዛዎቹ ዞረዋል።ዮሴፍ ምግብ ፍለጋ እንደመጡ አውቋል።በቁጥር 9 ላይ ህልም ለሚለው ቃል የተጠቀሰውን ማጣቀሻ ተመልከቱ ወደ ዘፍጥረት 37 ፡5፣9 እና የዮሴፍን ታሪክ አንብቡት ።
8. ዮሴፍ እንደ እንግዳ ማስተናገዱን ቀጥሏል።በቁጥር 9 ላይ ያቀረበባቸው ክስ ምን ነበር?_____

   __________________________________________________________________________________
9. አስር ሰዎች እና ዮሴፍ ነገር ግን ዮሴፍ አስተዳዳሪ ነበር።ወደ ከነአን ሊወስዱት የሚያስፈልጋቸው እህል አለው።ዮሴፍ የጠየቃቸው ምንድነው?__________________________

   __________________________________________________________________________________
10. ቁጥር 11 እና 13 ስለቤተሰባቸው ምን ነገሩት?________________________________________

    _______________________________________________________________________________
11. ዮሴፍ ፅኑ ሰው ነበር።እነሱንም ሰላዮች ናችሁ እያለ መክሰሱን ቀጥሏል።በቁጥር 15 ላይ ምን አይን ፈተና አዘዛቸው?______________________________________________________
12. ዮሴፍ ለምን ይህንን ፈለገ ዮሴፍ ለማወቅ የፈለገው ነገር ምንድነበር?____________________

    _______________________________________________________________________________
13. ቁጥር 16 እና 17 ዮሴፍ ያዘዛቸው ምን ነበር?________________________________________

    _________________________________________________________________________________

ከፉኛ መፈታተኑን ቀጥሏል።የተናገሩት ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገት ፈልጓል።እቤት ያለው ነገር ልክ እነሱ እንዳሉት መሆኑን ማረጋገጥ ፈልጓል።

## ክፍል 2

**መልመጃው ቀጥሏል፡** በቁጥጥር ስር ከዋሉ ሶስት ቀን ሆኗቸዋል።

1. በእነዚህ ቀናት እነዚህ ወንድማማቾች ስለምን የሚያወሩ ይመስላችኋል ከዚህ በኋላ ከዚያ እንደማይወጡ ያስቡ ይሆን ይህ አስተዳዳሪ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ያለው ጉዳይ ምን

ይሆን እናንተ በዚህ ስፍራ አብራችኋቸው ብትሆኑ ንግግሩ በምን መልኩ የሚካሄድ ይመስላችኋል?____________________________________________

2. ዮሴፍ ትእዛዙን ቀየረ፡፡ሰዎቹ የነገሩት ምንድነው?

ሀ. ቁጥር 18____________________________________________

ለ. ቁጥር 19 ____________________________________________

ሐ. ቁጥር 20____________________________________________

3. ቁጥር 21-22 እነዚህ ወንድሞች እነዚህን አመታት በሙሉ ተሸክመውት የነበረውን የጥፋተኝነት ህመም ይገልፀዋል፡፡አስቲ በራሳችሁ ቃል ተሸክመውት የነበረውን ጥፋተኝነት ግለፁት?________________________________________

____________________________________________

4. ሮቤል እራሱን ንፁህ ሊያደርግ ፈለገ፡፡እንደዚህ አይነቱን ሰው አቶ “ነግሬያችሁ ነበር” እንለዋለን፡፡ነቀፋው ምን ነበር?____________________________________

ይህንን ያለውን ለመጀመሪያ ግዜ የተናገረው ይመስላችኋል?______________________

ክሱ ምን ነበር?____________________________________________

5. በቁጥር 23 ላይ የሚበኘው አስደሳቹ መገለጥ ምንድነው ከዚህ በፊት እንደዚህ አስባችሁት ታውቀቃላችሁ?________________________________________

____________________________________________

6. ለወንድሞቹ ንግግር የዮሴፍ ምላሽ ምን ነበር?______________________________

ስሜቱን ከተቆጣጠረ በኋላ በድጋሚ ምን አዘዛቸው?____________________________

____________________________________________

7. ቁጥር 25 ዮሴፍ ደግ ነበር፡፡እንዴት ነበር ለጋስነቱነ የገለፀው

   1. ________________________________________
   2. ________________________________________እና
   3. ________________________________________::

**ክፍል 3 ፡**

**ገለፃ፡** ዮሴፍ ለወንድሞቹ የማይገባቸውን ነው ያደረገላቸው፡፡እነሱ ሊገድሉት ነው የፈለጉት እሱ ግን ብዙ መልካምነት አሳያቸው፡፡አስቲ ወደ ዘፍጥረት 39፡21 ዮሴፍ በእስር ቤት ውስጥ እያለ፡፡ቁጥሩ እግዚአብሄር ከዮሴፍ ጋር እንደነበረ ይነግረናል ፡፡እግዚብሄር ብዙ መልካምነት አሳየው

ሞገስንም ሰጠው፡፡በዘፍጥረት 42፡25 ላይ ያለውን ክፍል እስቲ ገለፃውን እንመልከት፡፡ስለዮሴፍ ቸርነት አውርተናል፡፡ለወንድሞቹ ደግነት አሳይቷቸዋል፡፡እግዚአብሄር ለዮሴፍ በእነዚህ ሁሉ አመታት ደግነቱን ስላበዛለት እሱም ከእግዚአብሄር የተማረውን ደግነት ለወንድሞቹ በተግባር አሳይቷቸዋል፡፡እግዚአብሄር የዮሴፍን ልብ ለወንድሞቹ እንዳራራላቸው ግልፅ ነው፡፡ዮሴፍ በእነዚህ ጊዜያት በምሬት ሲብሰለሰል አልከረመም ስለዚህም አሁን ከወንድሞቹ ጋር የነበረውን ችግር ፊቶ መልካምነቱን ሊያሳያቸው ፈልጓል፡፡

የዮሴፍን ልግስና እና ደግነት እኛም በህይወታችን መተግበር ይገባናል፡፡ጥፋተኝነት ሌሎች መልካም ነገሮችን እንዳንቀበል ያደርገናል፡፡የጥፋተኝነት ስሜት እራሳችንን ይቅር ካላልን ብቸኛ ያደርገናል፡፡በሌሎች ላይ ያደረግውነን ጥፋት እራሳችንን ይቅር ካላልን ከሌሎች ተለይተን ብቸኛ እንሆናለን፡፡የጥፋተኝነት ስሜት ከእግዚአብሄር እንኳን ሳይቀር ይለየናል፡፡ተፈጥሮአችን አንድን በደል ወዲያውኑ እንድንረሳው የሚያደርገን አይደለም ስለዚህ ከሃጢአት ሁኔታ ውስጥ ልንወጣ አንችልም፡፡እግዚአብሄርን በበደልነው ነገር ጥፋተኛ ነን፡፡በደላችን ለሌሎች ባለን ምላሽ ግልፅ ይሆናል፡፡በጥፋተኝነት ህይወት ውስጥ ስንመላለስ ብዙ ነገሮችን አንዘረፋለን ያም ህይወትን በነፃነት እና በሙላት እንዲሁምለ ከእግዚአብሄር ጋር ያለን የፍቅር ግንኙነት ህይወትን መኖር አንችልም ፡፡

እግዚአብሄር ፍቅሩን ለሁሉም መስጠት ይፈልጋል ፡፡ይህንንም የፍቅር ፀጋ እንልዋለን፡፡ፀጋ ማለት ልክ ዮሴፍ ለወንድሞቹ የማይገባቸውን ደግነት እና ፍቅር እንዳደረገላቸው ለኛም ሊሰጠን የማይገባ የእግዚአብሄር ፍቅር እና መልካምነት ነው፡፡ዮሴፍ ወንድሞቹን እንደሚወዳቸው እንዲረዱት ይፈልግ ነበር፡፡ይቅር ብሏችዋል፡፡እግዚአብሄርም ተሸክመን የምንዞረውን የጥፋተኝነት ህይወት በክርስቶስ እየሱስ ደም እንደተደመሰሰ እንድናውቅ ይፈልጋል፡፡እየሱስ እሱን የበደልነውን በደል እንዲደመሰስልን እና ይቅርታ እንድናገኝ ስለኛ ኃጢአት የሞተልን ነው፡፡የበደኝነት ስሜታችን ካልተወገደ በህይወት መንገዳችን ሁሉ ይከተለናል፡፡ብዙ ግዜ በደላችን እንዳልተደመሰሰ የሚነግረንን ውሸት ተቀብለን የእግዚአብሄር ፍቅር እንደማይገባን እናምናለን፡፡የእግዚአብሄር ግብዣ ግን በክርስቶስ እየሱስ የሰጠንን ነፃነታችንን ተቀብልን በነፃነት እንድንኖር ነው፡፡በኤፌሶን 2፡8-9 ላይ ምን እንደተባልን ግለፁ________________________________________

__________________________________________________________

ፍቅሩ ንፁህ እና ለእኛ ማይገባ ነው፡፡የልጁን እየሱስ ክርስቶስን ህይወት ፣ሞት፣እና ትንሳኤ በማመን የምንቀበለው የእግዚአብሄር ነፃ ስጦታ ነው፡፡የአርሱ ይቅርታ የኛ ነፃ ነታችን ነው፡፡

**የምናሰላስለው፡** በዚሁ ምእራፍ ኤፌሶን 2፡4 ቅዱስ ጳውሎስ እነዚህን ቃላት እንዲህ በሎ

ፅፎልናል፡፡ “ነገር ግን እግዚአብሔር___________ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፥ከወደደን ከትልቅ__________ የተነሣ __________ ፣ __________እንኳ በሆንን ጊዜ ___________ ሰጠን፥ ________ ድናችኊልና፥”

ይህ ክፍል በክርስቶስ እየሱስ ያለውን የእግዚአብሄርን ፍቅር የምስራች ይግረናል፡፡ይህን ክፍል በካርዳችሁ ላይ ፃፉት ልክ ሌሎቹን እንዳደረጋችሁ ይህንን ክፍልም በማሰላሰል የህይወታችሁ ክፍል አድርጉት፡፡የእየእለት ተእለት ህይወታችሁን ስትኖሩ በዚህ አባታችን ከእኛ ጋር ሊካፈል በሚፍልገው እና ከሌሎች ጋር እንድንካፈልው በሚፈልገው የፍቅር ቃል እየታደሳችሁ ፍፁም በመሆናችሁ ሳይሆን ይቅር እንደተባለችሁ ፣እንደታደሳችሁ ፣ነጻ እንደወጣችሁ እና እንደተፈታችሁ ሆናችሁ ኑሩ፡፡

<u>**ክፍል 4**</u>

**ግላዊ ትግበራ**፡የጥፋተኝነትን ስሜት በህይወታን እንዳለ ከተረዳን ከሁለት አቅጣጫ ልናየው ይገባናል፡፡

1. በመጀመሪያ ልክ እንደዮሴፍ በህይወቴ ውስጥ የጎዱኝ ሰዎች አሉ ወይ?__________________ አሁን እግዚአብሄር ታላቅ የሆነ ፍቅሩን እና ደግነቱን እንዴት እለት እለት በላዬ ላይ እንደሚያፈሰው ተረድቻለሁ ፡፡ስለዚህ ልክ እግዚአብሄር እኔን ይቅር ባለበት እና ፍቅሩን በገለፀበት መንገድ እኔም ለእዚህ ሰው ላደርግ ይገባኛል፡፡
   ሀ. ለዚህ ሰው እግዚአብሄር በህይወቴ ውስጥ ያደረገውን ፍቅር እና ደግነት ልገልፅበት የምችለው ጠንካራ ነገር ምንድነው? ____________________________________
   ለ. የእግዚአብሄርን ፍቅር እና ደግነት የማንፀባርቅበት እግዚአብሄር እኔን ሊረዳኝ የሚገባበት የህይወቴ ክፍል የቱ ነው?___________________________________
   ____________________________________________________________

2. የጥፋተኝነትን ስሜት ከወንድሞቻችን ጋር ካለን ግንኙነት አንፃር ነው መመልከት ያለብን ፡፡በውጣችሁ የተሸከማችሁት የበደለኝነት ስሜት አንድን ሰው በንግግር ወይንም በድርጊት የጎዳችሁበት ይሆን ያሰው ማነው?____________________________________________
   ሀ. ያንን ሰው የጎዳችሁበት ነገር ምንድነው?______________________________
   ጥፋትን ማመን ለማንም ሰው ቀላል አይደለም፡፡ልክ ሮቤል እንዳደረገው ጥፋታችንን አሜን ብለን ከመቀበል ይልቅ በሌላው ላይ ማሳበብ እና ማመካኘት ይቀናናል፡፡እነዚህ ለረጅም አመታት የበደለኝነት ስሜታቸውን ተሸክመው የዞሩትን

ወንድሞቸ ተመልከቱ፡፡ያጠፉትን ጥፋት በቶሎ ለመቀበል አልፈለጉም፡፡በዘፍጥረት 42፡21 “እነርሱም እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ፡፡ በእውነት ወንድማችንን በድለናል፥ እኛን በማማጠን ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን አልሰማነውምና ስለዚህ ይህ መከራ መጣብን፡፡”በጣም እያለቀሱ ነበር፡፡ “እንዴት ይህን ነገር አደረግነው?”

ለ. ልክ ጥፋተኝነታችንን ስንረዳ ይህንን ጥያቄ መጠየቅ አለብን “ለምን በጥፋቱ ላይ ተንጠልጥዬ እኖራለውሁ” ይህ ጥያቄ መመለስ አለበት፡፡ይህ የበደልኝነት ስሜት የሚሰማኝ የበከልኩትን ሰው ይቅርታ ስላልጠየኩ ይሆን ?ወይንስ በዚህ የበደለኝነት ስሜት የሚሰማኝ የበደልኩት በደል ይቅር የማይባል ሆኖ ነው? ወይንስ ከበደለኝነት ስሜቴ ጋር ተስማምቼ እየሆኖርኩ ስለሆነ ነው? ለምንድ ነወ ከዚህ የበደለኝነት ስሜት ጋር የምኖረው?______________________________

ሐ. በዚህ የበደለኝነት ስሜቴ ላይ መውሰድ የሚገባኝ እርምጃ ምንድነው? ምክንያቱም እግዚአብሄር ከእንደዚህ አይነቱ የበደለኝነት ስሜት ጋር እንድኖር አይፈልግም ነፃ እና ሙሉ የሆነ ህይወት እንድኖር ነው የሚፈልገው____________________

____________________________________________________________

**ጸሎት፡** ጌታ ሆይ ከበደለኝነት ስሜት ነፃ መውጣቴን ይገፎ በፊትህ እመጣለሁ ፡፡ከዚህ በኋላ ባለፈው በደሌ ምክንያት የሚሰማኝን የበደለኝነት ስሜት ተሸክሜ አልኖርም ነገር ግን ሙሉ አና ነፃ የሆነ ህይወት እኖራለሁ፡፡በእየሱስ ክርስቶስ ሞትእና ትንሳኤ ባለኝ እምነት አሁን ይቅር ተብያለሁ፡፡እሱ ስለእኔ ሞቷል ላንተ ለመኖርም ነፃ ወጥቻለሁ ፡፡እውነተኛ የሆነውን ከፍቅር የሆነውን ደግነትን በተግባር አሳይተሽኛል፡፡እኔም አንተ ያሳየሽኝን ፍቅር እና ደግነት ለሌሎች እንዳሳይ እስችለኝ፡፡በደሌን ስላልቆጠርክብኝ ይቅር ስላልከኝ አመሰግናለሁ፡፡በክርስቶስ እየሱስ በኩል የእኔ ስለሆነው ነፃ የፍቅር ስጦታህ አመሰግናለሁ፡፡____________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

## ክፍል 5

**የቤት ስራ፡** ዘፍጥረት 42፡፡29-38 ያለውን ክፍል አንብቡ “እግዚአብሄር ያደረገብን ይን ነገር ምንድነው?” የሚል ጥያቄ በጭንቅላታቸው ተሞልተው ወደቤታቸው የሚመለሱትን የወንድሞች ንግግር ማሰብ ትችላላችሁ፡፡

**መልመጃ:** የያዕቆብ ልጆች ተመልሰው ወደ እቤት መጥተዋል፡፡ከአባታቸው ጋር የገጠማቸውን ነገር ሲወያዮ ምንያህል እስጨናቂ እንደሚሆንባቸው አስቡ፡፡ምንያህል ግራ እንደተጋቡ አስቡ፡፡

1. በቁጥር 30-40 ላይ ወደ አባታቸው ይዘው ስለመጡት መረጃ ይነግረናል ፡፡ሁሉም ነገር ትክክል ነበር?______________________________________________________
2. በቁጥር 35 አንድ ነገረ ተከሰተ ቁጥር 27 አስታውሱ ከወንድሞች መክካል አንደኛው ቤት እየተመለሱ ባሉበት ወቅት አህያውን ሊመግብ ጆንያውን ሲከፍት እህሉን የገዛበት ገንዘብ ተመልሶለት ውስጡ አገኘው፡፡በቁጥር 35 ላይ ምን ተፈጠረ?________________________

   ገንዘቡን ሲያገኙ ምን ተሰማቸው?________________________________________________
3. ያዕቆብ ለልጆቹ ምን አላቸው?_________________________________________________

   ታዲያ ይህ ምን ማለት ነው ያዕቆብ ለልጆቹ በእውነት ማለት የፈለገው ምንድነው?_______

   ቁጥር 37 ላይ ሮቤክል ተናገረ በዮሴፍ ላይ ስላደረጉት ነገር እና እለአባታቸው ሀዘን እሱ ተጠያቂ እንደሆነ ተናገረ ምን ነበር ያለው?________________________________________

   __________________________________________________________________________
4. የዕቆብ ግትር ነው ምላሹ ምን ነበር?________________________________________________

   __________________________________________________________________________

   የዕቆብ አድልዎው ወደ ሌላኛው የራሄል ልጅ ወደ ቢንያም አንደዞረ ተገልጧል በጥርጣሬ ደረጃ ያዕቆብ እነዚህን አስሩን ልጆቹን ከዚህ በኋላ እንደልጆቹ ላይቆጥራቸው እንደሚችል በቁጥር 1 ላይ ይታያል፡፡በቁጥር 38 ምን እይነት ቃል ነው የተጠቀመው?_______________
5. ቢንያም ምን ያህል ለዚህ ቤተሰብ ከባድ የሀሳብ መከፈል ሆኗል?____________________

   __________________________________________________________________________

**ትምህርት:** ረሀቡ አሁንም ፀንቷል ስለዚህም ያዕቆብ ልጆቹን እንደገና እህል እንዲገዙ ወደግብፅ ላካቸው፡፡ይሁዳም ለያዕቆብ የዛ ሀገር ገዢ ያዘዛቸውን ነገረው፡፡ይሁዳ ቢንያም ከእነሱ ጋር ካልሄደ ጉዟቸው ከንቱ ልፋት እንደሆነ ያውቃል፡፡ያዕቆብ ስለቤተሰቤ እንዲህ አይነት መረጃ ለምን ሰጣችሁ ብሎ ወቀሳቸው፡፡እነሱም የሰጡት መረጃ እንደዚህ አይነት ችግር በላያችው ላይ እንደሚያመጣ እንዳልገመቱ ነገሩት፡፡ይሁዳም ግትር ወደ ሆነው አባቱ ገብቶ ቢንያምን አብሮን እንዲሄድ ፍቀድ አለው፡፡ለዚህም ኃላፊነቱን እኔ እወስዳለሁ አለው፡፡ቢንያም አንድ ነገር ቢሆን ዘመኔን ሁሉ ስለእሱ የምነቀፈው እኔ ልሁን አለ፡፡

**የቤት ስራ፡** ዘፍጥረት 43፡ ያዕቆብ እያመነታ ቢንያምን ከወንድሞቹ ጋር ወደፅ ሄደ፡፡

**መልመጃ፡**

1. ያዕቆብ ከልጆቹ ጋር የላካቸውን ስጦታዎች አስቡ፡፡በቁጥር 12 ላይ ምን ተካቶ ነበር?_____
______________________________________________
2. ያዕቆብ ለልጆቹ ምን ብሎ ፀልዮላቸው ሸኛቸው ቁጥር 14?______________________
______________________________________________
3. ወንድሞቹም ወደግፅ በፍጥነት በመሄድ እራሳቸውን እና ቢንያምን ለዮሴፍ አቀረቡ ቁጥር 16?______________________________________________
______________________________________________
4. ሰዎቹም ወደ ዮሴፍ ቤት ተወሰዱ ቁጥር 18 ምን ይነግረናል ?____________________
5. የሰሩት ጥፋት አእምሮአቸውን ምን ያክንል እንደረበሸው አስቡ ምን ብለው ደመደሙ?______
______________________________________________
6. እነሱም ሀሉም ነገር ሰላም መሆኑን እየነገራቸው ለነበረው ባለአደራ እንዲያማልዳቸው ነሩት ፡፡ብራቸውንም ወሰደ ቁጥር 23 ላይ ምን አላቸው ?________________________
______________________________________________

**ትምህርት ፡** በዚህ ክፍል ወንድሞቹ በየጆንያዎቻቸው ስለተገኘው ብር ንፅህናቸውን እየመሰከሩ እና በድጋሚ እህል ለመሸመት ያላቸውን ፍላጎት እየገለፁ ዘገባው ቀጥሏል፡፡እንዲህ የሚለው ዐረፍተ ነገር “ብሩን እኛ ጆንያውስጥ ማን እንዳደረገው አናውቅም ቁጥር 22” ባለአደራውም ምንም ነገር መፍራት እንደሌለባቸው እያረጋገጠላቸው እንዲህ አላቸው “እርሱም አላቸው፡፡ ሰላም ለእናንተ ይሁን፥ አትፍሩ አምላካችሁና የአባታችሁ አምላክ በዓይበታችሁ የተሰወረ ገንዘብ ሰጣችሁ ብራችሁስ ደርሶኛል፡፡” ሊጠየቅ የሚገባው ጥያቄ “የከፈልነው ገንዘብ በጆንያችን ውስጥ ከተገኘ የገዛነውን እህል ክፍያ የከፈለልን ማነው” ወይንም እኛ ያመጣነው ገንዘብ ለእህል ግዢው ከተከፈለ ሌላ ብር እኛ ጆንያ ውስጥ የጨመረው ማነው

ዘፍጥረት 42፡25 ተመልሰን ስንቃኝ ገንዘነቡን ወደ ጆንያቸው እንዲከተትላቸው እና ለመንገዳቸውም የሚስፈልጋቸው ነገር እንዲሰጣቸው ያዘዘው ዮሴፍ እንደነበር እናስታውሳለን፡፡እዳቸውን ለመክፈል ዮሴፍ ኃላፊነቱን እንደወሰደ ተመልክተናል፡፡ወንድሞቹ የወሰዱትን እህል ከራሱ አካውንት ከፍሏል ፡፡ስለዚህም ከእዳ ነፃ ናቸው፡፡ የሚቀርባቸው ክፍያ የለም፡፡

**ስለእግዚአብሄር ምን እንማራለን፡** የዮሴፍን ታሪክ እያጠናን ባለንበት በዚህ ትምህርት ባጠቃላይ እግዚአብሄር በሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ አብሮት እንደነበረ እና መልካምነቱን እያሳየው እንደነበረ እንዲሁም በሁሉ ፊት ሞገስ ሰጥቶት እንደነበር ተመልክተናል፡፡ በዚህ ታሪክ እንዲሁም ስለ ወንድሞቹ ባጠናንበት ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ለእኛ ጋር ስላለው ግንኙነት ተምረንበታል ፡፡ በተጨማሪም ደግሞ የራሳችንን መንገድ እና ምርጫ በመከተል ከእግዚአብሄር መለየት እንድምንችል ተምረናል፡፡ነገር ግን እርሱ በፍቃዱ የእኛን የኃጢአት እዳ እንደከፈለልን ተመልክተናል ፡፡የኃጢአታችን እዳ የዘላለም ሞት ሲሆን የእግዚአብሄር የፃጋ ስጦታ ግን በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ የሆነው የዘላለም ህይወት ነው፡፡በተመሳሳይ ዮሴፍ የእግዚአብሄርን ታላቅ ፍቅር ምስል ያሳየናል ፡፡ዮሴፍ የወንድሞቹን እዳ ከፈለላቸው፡፡እነሱ ብዙ ነገር አደረጉት እሱ ግን እዳቸውን በሙሉ ከፈለላቸው፡፡ለሁሉም ነግር እርሱ ኃላፊነት ወሰደ፡፡እዳቸውን በሙሉ ከፈለ የበደሉትን ሁሉ ይቅር አላቸው ስለዚህ በዚህ ምክንያት ከእዳ ነፃ የሆነ የነፃነት ኑሮ መኖር ቻሉ፡፡ ከእዳ ነፃ ሆኖ የመኖርን ህይወት ተለማምዳችኇል?ከጥፋተኝነት ስሜት ኑሮ ነፃ የሆነ ኑሮን ተለማምዳችኇል?ከእፍረት ነፃ የሆነ ኑሮስ እንደዚሁ ተለማምዳችሁ ይሆን ከነቀፋስ ህይወታችሁ ንፁህ ነው፡፡የሰማዮ አባታችን የይቅርታን ፀጋ በመቀበል ከእዳ ነፃ የሆነ ኑሮ እንድንኖር ይጋብዘናል፡፡

**መልመጃ፡**(የቀጠለ)

1. ስምኦንን ወደእነሱ አመጡት (ቁጥር 24 ) ለአስተዳዳሪው ከእነሱ ጋር ምግብ እንዲበላ ዝግጅት ተደርጎላታል፡፡ስጦታዎችም ተዘጋጅተዋል፡፡ለእንሰሶቻቸውም መኖ ተዘጋጅተዋል እግራቸውን ታጥበዋል፡፡ዮሴፍም ወደ እቤት ሲመለስ ሁሉም ሰገዱለት እሱም ተቀበላችው፡፡ምን ጠየቃቸው(ቁጥር 27) ?____________________________________________

   ______________________________________________________

   ለሱ ዘርዝር መረጃ አቀረቤ ወድቀውም ሰገዱለት ቁጥር (28)?__________________________

2. ስለቢንያም ጠየቃቸው ብዙ አመታት አልፏል፡፡ያለጥርጥር ታናሽ ወንድሙ መልኩ ይቀየራል ዮሴፍም ለመለየት ተቸግሮ ቢንያም ይህ ይሆን እያለ ሊያስብ ይችላል ፡፡ዮሴፍ የተናገረው ቃል ምን ነበር?____________________________________________________

   የዮሴፍን የተረጋጋ ንግግር ለወንድሞቹ ሲያደርግላቸው በሀሳባችሁ አስቡት፡፡

3. ቁጥር 30 የዮሴፍን ልብ ለወንድሞቹ በተለይም ለእናቱ ልጅ ምን ይመስል እንደነበር ይግልፃል፡፡ስሜቱን መቆጣጠር ስላልቻለ ካለበት ክፍል ወጥቶ የሚያለቅስበት ክፍል ፈለገ፡፡በራሱ ክፍል ውስጥም ሆኖ አለቀሰ፡፡ዮሴፍ በዚህ ሁሉ አመት ውስጥ ያሰቃየው የነበረው በእንባ

የወጣለት ነገር በወንድሞቹም ፊት ባዶ እንዲሆን ያደረገው ምንድነው? ዮሴፍ እና ቢንያም ልጆች ሆነው የነበራቸው ግንኙነት ምን ይመስል ነበር? በጉድጓድ ውስጥ መጣል በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ትልቅ ችግር ፈጥሯል በተለይ ደግሞ በእነዚህ ወንድማማቾች መካከል፡፡

**ጸሎት፡** እንደሚታወቀው ታሪኩ አላለቀም፡፡ትምህርት 5 በዮሴፍ እና በወንድሞቹ መካከል እለተፈጠረው ነገር ይቀጥላል፡፡እግዚአብሄር ይህንን የተበታተነ ቤተሰው እያሰባሰበ እንዳለ እንደዚሁ እኛንም ከምንወዳቸው እና ከተለየናቸው ሰዎች ጋር ያገናኘናል፡፡እስቲ ጌታ ይህን አይነት ፍቅር ከሰዎች ጋር ትከፋፈለሉ ዘንድ እንዲሁም ሰዎች ሁሉ ለዘለአለም የሆነውን ተሀድሶ እንዲያገኙ ለሚፈልገው አምላክ የልባችሁን መሻት ግለፁለት፡፡

# ትምህርት አምስት

# እኔ ዮሴፍ ነኝ

## ዘፍጥረት 43-45- ወንድም

---

**የትምህርት 5 ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት5፡ዘፍጥረት 43-45

- ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋር በላ
- የተዳላለት
- ወንድሞቹ ተያዙ
- ዮሴፍ ከእንደገና በፊት
- የዮሴፍ ማንነት ተገለጠ

## መግቢያ

ዮሴፍ ማንነቱን  የሚገልጥበት ጊዜ መጣ ነገር ግን በአንድ መረጃ ግን መወሰን አለበት፡፡ዮሴፍ ወንድሞቹን በአቤት የቀረውን ትንሹን ወንድማቸውን ቢንያምን ይዘው እንዲመጡ ግድ ያላቸው ለምንድነው? ይህ ልጅ በስጦታና በምግብ በዮሴፍ ፊት ሞገስ ያገኘው ለምንድነው?ለምንድነው ቢንያም ሌሎቹ ወንድሞቹ ባልተስተናገዱበት መንድ ያስተናገደው?ወይንም ለምንድነው ዮሴፍ ሌሎችን ወንድሞችን ቢንያምን ባስተናገደበት መልኩ ያላስተናገዳቸው? ዮሴፍ እራሱን ከመግለጡ በፊት ማወቅ ያስፈለገው ነገር ነበር ይንንም በትምህርት 5 ውስጥ ተመልከቱት፡፡

ዮሴፍ ወንድሞቹን አስቸጋሪ ግዜ እንዲያሳልፉ አድርጓቸዋል፡፡ላደረጉበት ክፋት ምላሽ እየሰጣቸው ይሆን?ዮሴፍ ስለ ይቅርታ ምንድነው ያስተማረን?ይቅርታ ለመቀበል ስለተበደለው በደል ዋጋ መክፈል አለበት ማለት ነው?ለይቅርታ የሚያስፈልገው  ነገር ምንድነው?

ዮሴፍ ወንድሞቹ ያላወቁት አንድ ነገር እንዳለ አምኗል ፡፡ዮሴፍ ስለ አባቶቹ አምላክ ፣ስለ አብርሐም ፣ስለ ይስሃቅ፣ስለያዕቆብ አምላክ ምን እንዳመነ ለህይወታችሁ የሚሆን ትርጉም ፈልጉበት፡፡

## <u>ክፍል 1</u>

***መግቢያ፡*** በመጨረሻም ያዕቆብ ከወንድሞቹ ጋር ወደግፅ እንዲሄድ ፈቀደ፡፡የተለያዮ ስጦታዎችን ለገዢው ይዘው እንደገና በድጋሚ ምግብ ለመግዛት ወደ ግብፅ ሄዱ ፡፡ይህ ስብስብ በጭንቀት ውስጥ ሆኖ ነው የሚጓዘው፡፡ወደ ግብፅ ያደረጉት የአሁኑ ጉዞ እንደከዚህ በፊቱ ብዙም ተስፋ የተሞላ አይደለም፡፡የገዢው ንግግር ጥሩ አልነበረም ፣ለሶስት ቀን እስርቤት አቆይቷቸው ነበር፣እንዲያመጡት ለታዘዙት ወንድማቸው ማስያዣ ሌላ ወንድማቸው በመያዣነት ታስሯል ሁሉም አሁንም ጆንያቸውን ሲከፍቱ እህል የሸመቱበት ገንዘብ አሁንም በጆንያቸው ውስጥ ተመልሶላቸዋል፡፡

በዚህኛው ጉዟቸው ደግሞ በቀጥታ ወደ ገዢው ቤት እንዲሄዱ ነው የተነገራቸው፡፡በዚያም ምሳቸውን በልተዋል፡፡በሀሳባቸውም ውስጥ ዮሴፍን ከብዙ አመት በፊት ባሪያ አድርገው በመሸጣቸው ምክንያት እግዚአብሄር እነሱንም ባሪያ አድርጎ ሊቀጣቸው እንዳሰበ አምነዋል፡፡ነገር ግን ባለአደራው ምንም እንዳይጨነቁ ነግሯቸዋል፡፡ "እርሱም አላቸው፡፡ ሰላም ለእናንተ ይሁን፥ አትፍሩ አምላካችሁና የአባታችሁ አምላክ በዓይበታችሁ የተሰወረ ገንዘብ ሰጣችሁ ብራችሁስ ደርሶኛል፡፡"በመጨረሻም ወንድሞቹ በግብፅ ትተውት ወደመጡት ወንድማቸው ወደ ስምኦን ተመልሰው መጡ፡፡

እግራቸውን ታጥበው ለእንስሶቻቸውም መኖ ተሰጥቶላቸው እነሱም እየተመገቡ ባሉበት ዮሴፍ መጣ፡፡እነሱም ስጦታን አበረከቱለት፡፡ስለአባታቸው እና ትንሹን ወንድማቸወን ቢንያምን ይዘው መምጣታቸውን እያረጋገጠ ጠየቃቸው፡፡ዮሴፍም ታናሹን ወንድሙም ሲመለከተው ስሜቱን መቆጣጠር አቃተው፡፡ወዲያውም የሚያለቅስበት ስፍራ ፈልጎ ወጣ፡፡ትረካችን ያቆመው ምግብ

ወደሚመገቡበት ስፍራ ተመልሶ ሲመጣ ነው።

**የቤት ስራ፡** ምእራፍ 43 አንብቡ

**መልመጃ፡** የሴፍም እራሱን ካረጋጋ በኂላ ምግብ እንዲቀርብ አዘዘ

1. በቁጥር 32 መሰረት አቀማመጣቸው እንዴት ነበር ?
   ሀ. ዮሴፍ የተቀመጠው የት ነበር?________________________________________
   ለ. ወንድሞቹ የት ተቀመጡ?___________________________________________
   ሐ. ግብፃውያኑስ የት ሆነው ነበር የሚመገቡት?______________________________
2. ለምንድነው አቀማመጣቸው በዚህ መልኩ የሆነው? ___________________________
3. ለምን ነበር ዮሴፍ ከግብፃውያኑ ጋር የተቀመጠው? የዘፍጥረት 41፡12 ማጠቃለያ ምንድነው?______________________________________________________________

______________________________________________________________________

4. በቁጥር 33 ላይ ስላለው አቀማመጥ ምን ተነግሮናል ?_____________________________

_________________________________________________________________________

5. የወንድሞቹ ምላሽ ምን ይመስል ነበር?_______________________________________
6. ምግቡ ቀርቦ ሲበላ ደስ የሚያሰኘው ምኑ ነበር?_________________________________
7. ለቢንያም የተሰጠው ድርሻ ምን ያክል ነገር ?____________________________________
8. በቁጥር 34 መሰረት ሁሉም ጥሩ ግዜ አሳልፈዋል “እነርሱም_________ ከእርሱም ጋር ________________አላቸው።”

**<u>ክፍል 2</u>**

**ገለፃ፡** በዚህ ጥቂት ቁጥር ውስጥ ያለውን ታሪክ ለመረዳት ጥቂት ነጥቦችን ማየት አለብን ።እስቲ አነዚህን ከግንዛቤውስጥ አስገብታችኂል?

1. ለምንደነው ማንነቱን ዮሴፍ ያለነገራቸው? ፊቱን ወደ ታናሽ ወንድሙ ቢንያም መልሷል።አስራ ሁለቱም ወንድማማቾች በአንድ ክፍል ውስጥ ናቸው ያሉት ነገር ግን ለምንድነው ማንነቱን ከወንድሞቹ መሸሸግ የፈለገው?
2. አቀማመጣቸው ይህን ይመስል ነበር።በመጀመሪ ሶስት የመመገቢያ ስፍራዎች ነበሩ።ዮሴፍ ፣ወንድሞቹ፣ እና ግብፃውያን።ለግብፃውያኑ ከዕብራውያኑ ጋር መመገብ ደስተኛ እንደማያደርጋቸው ተነግሮናል። ይህ የምግብ አቀራረንብ የዋናው የምግብ አቀራረብ አይነት

አልነበረም ፡፡ዮሴፍ እየበላ የነበረው ብቻውን ይሆን?

3. ግብፃውያኑ እንዴት በእድሜያቸው ከፋፍለው አስቀመጧቸው ?እንዴት አወቋቸው?ወንደማማቾቹ ተደንቀዋል፡፡
4. ወንድማማቾቹ ምግባቸው ከአስተዳዳሪው ጋር አንድ እንደነበር ልብ ብለው ይሆን?ምግቡ የተወሰደላቸው ከግብፃውያኑ ሳይሆን ከዮሴፍ ጠረጴዛ ላይ ነው ያንን ልብ ብለው ይሆን ?ሁሉም እየተመገቡ የነበሩት አንድ አይነት ምግብ ይሆን?ስለዚህ ግድ የሚላቸው ይሆን?ያ ለነሱ ትርጉም ያለው ነገር ይሆን ?
5. ዮሴፍ ለታናሽ ወንድሙ በግልፅ ከሌሎቹ በተለየ ብዙ ምግብ እንዲወስድ ሲያደርገው ሌሎች ምንም አይነት ስሜት አልተፈጠረባቸውም ያለምንም ሰውጥ መብላት መጠጣታቸውን ቀጠሉ፡፡ሁሉም ከያዙት አምስት እጥፍ ድርሻ እንዲያነሳ ሲያደርግ ማንም በዚህ ላይ አስተያየት አልሰጠም አልተረበሹምም፡፡

**የቤት ስራ፡** ዘፍጥረት 44 አንብቡ

***መልመጃ፡*** *ታሪኩ በሌላ ክስተት ቀጥሏል*

1. ቁጥር 1-2፡ የሴፍ ባለአደራውን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?____________________________

____________________________________________________________________________

2. በማለዳው ወመድማማቾቹ ወደ ከነአን ጉዟቸውን ጀመሩ፡፡ዮሴፍ ለቤቱ አዛዥ ቀጥሎ ምን እንዲያደርግ ነገረው?____________________________________________________

____________________________________________________________________________

3. የቤቱም አዛዥ ተከታትሎ ዮሴፍ እንዳዘዘው አደረገ፡፡ለዚህ ክስ ምላሻቸው ምን ነበር?________

____________________________________________________________________________

ለምን ?ለምን ?ለምን? አሁን ደግሞ ምን አጠፋን?ጭንቀታቸውን ተመለከታችሁ?እኛ ይህን ያክል ፀንተን ይሆን? በቁጥር 7 ላይ ያለውን ለምን የሚለውን ቃል አስምሩበት፡፡

4. በቁጥር 9 ላይ ምልጃቸው ምን ነበር?___________________________________________

____________________________________________________________________________

የቤቱ አዛዥ የብሩ ፅዋ የተገኘበት ማንኛውም ሰው ባሪያ ይሆናል ብሎ ተስማማ፡፡

5. ቁጥር 10፡13 ስለዚህ አንድ በአንድ ጆንያቸውን ያስፈትሹ ጀመር፡፡ፅዋው ማንጋ ተገኘ?_____

____________________________________________________________________________

## ክፍል3

**ትምህርት፡** በዘፍጥረት 44፡13 ላይ ፅዋው በቢንያም ጆንያ ውስይ ሲገኝ ስለተፈጠረው ነገር እንዲህ በማለት ይነግረናል። ወንድሞቹ ልብሳቸውን ቀደዱ።ልብስን መቅድ ጥልቅ የሆነ ኀዘን ወይንም ፀፀት መግለጫ ነው።በቁጥር 13 ላይ የተጠ ቀሰውን ማጣቀሻ ተመልከቱ።በዚህ ስፍራ ልብሱን የቀደደው ማነው የነበረበትስ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር ዘፍጥረት 37፡29____________

________________________________________________________________

በዘፍጥረት ያለው ስለዮሴፍ የተፃፈው ዘገባ በሌላ ግዜ ስለ ዮሴፍ ስየተፃፈውን ሲነግረን “ ልብሱን ቀደደ ”ይለናል በዚህስ ስፍራ ልብሱን የቀደደው ማነው ዘፍጥረት 37፡ 34?_________________

________________________________________________________________

**መልመጃ፡** ወንድማማቾቹ በጣም ተረብሸዋል።ቢንያምን ፈፅሞ በግብፅ ትተውት አይመለሱም ። ስለዚህ እንደገና አስተዳዳሪውን ሊማፀኑ ወደግብፅ ተመለሱ።ዘፍጥረት 44፡14 እንደሚያሳየን ዮሴፍ በቤቱ ተቀምጦ ይጠብቃቸው ነበር።

1. ከወንድማማቾቹ መካከል መሪ ወጥቷል ፣ከፈለጋችሁም አፈጉባኤ ልትሉት ትችላላችሁ ያሰው ማነው (ቁጥር 16)?________________ለምንድ ነው እሱ ከመካከላቸው የመሪነቱን ስፍራ የያዘው?ሊያደርግ ያለው ነገር ምንድነው?ዘፍጥረት 43፡8-10 ተመልከቱ___________________

________________________________________________________________

2. ልክ ዮሴፍ ጋ እንደደረሱ ሁሉም መሬት ላይ ወደቁ።በፊቱ በመስገድ በመካከላቸው ማን ታላቅ እንደሆነ አወጁ።ስለዚህም ዮሴፍ ክሱን ያሰማ ጀመር።በጣም ፈተናቸው።ምን እንዳደረጉ እየመረመራቸው እንደሆነ አላወቁምን?እንዴት ቢደፍሩ ነው በዚህ አይነት ስነምግባር ከግብፅ መሪ ፊት ሊሄዱ የሚሞክሩት ?ለምንድነው ዮሴፍ በግፍ ወንድሞቹን የሚያነገላታቸው?___________

________________________________________________________________

ያጠፉት ጥፋት አለእንዴ?_____________________________________________

3. እንደገና የተሸከሙት የጥፋተኝነት ስሜት ይፈርድባቸው ጀመር።ያለፈው ማንነታቸው መልሶ ያዛቸው።ነገር ግን አሁን ስላሉበት ነው።የምንኖርበት ዛሬ ትናንት ባደረግነው ይበላሻል። በቁጥር 16 መሰረት መደምደሚያው ምንድነው?_____________________________________

4. ይሁዳ ያጠፉት ሁሉም እንደሆኑና ሁሉም ባሪዎች ሆነው በግብፅ እንዲቀሩ ጠየቀ ።ነገር ግን ዮሴፍ ያንን እንደማያደርግ ተናገረ።ጥፋተኛው ብቻ ነው እዚህ መቅረት ያለበት እሱም ደግሞ_____________________________ነው።አሁንም በድጋሚ ይሁዳ ሁሉንም ወክሎ

ተናገረ።ይሁዳ ከገዢው ጋር ይነጋገር የነበረው ነገር ምን ነበር?

ሀ. ቀጥር 20-21________________________________

ለ.ቁጥር 21-40________________________________

ሐ. ቁጥር 25-26________________________________

መ. ቁጥር 26-29 ________________________________

ይሁዳ ሁሉንም ነገር አጠቃሎታል ።በግብፅ ለመጀመሪያ ግዜ ከመጡበት ግዜ ጀምሮ ያለውን ነገር ገለፀለት።

5. በመቀጠልም ቢንያምን በግብፅ ትተውት ቢሄዱ ሊፈጠር የሚችለውን ነገር ነገረው።ቁጥር 32 ሌላ ምን ጨምሮ ገለፀለት? ማነው በሕይወት ያለው?ቢንያም ወደ እቤት ካልተመለሰ የዛ ሰው ህይወት መጨረሻ ምን እንደሚሆን ተናገረ?________________________________

________________________________

6. ይሁዳ በቁጥር 33-34 ላይ ስለምን ነበር የሚማፀነው?________________________________

________________________________

## <u>ክፍል 4</u>

**ገለፃ፡** እስከአሁን ዮሴፍ ትክክለኛ ማንነቱን አልገለጠላቸውም ።ነገር ግን ያኔ አብረው በጎች ሲጠብቁ ከነበረበት ግዜ የተለወጠ ነገር ይኖር እንደሆን ይጠይቀው ነበር።በዛን ግዜ ዮሴፍ ለተባለው ለያዕቆብ ተወዳጅ ልጅ አባቱ ለሱ ካለው ፍቅር የተነሳ ወንድሞቹ ሊገድሉት ቢፈልጉም ሀሳባቸውን ቀይረው ለነጋዴዎች ሸጡት።የዮሴፍንም ልብስ በደም በመንከር አባታቸውን አታለሉት።ልጁ ምን ሆኖ እንደሞተ እንዲገምት ለያዕቆብ ተተውለት ወጡ።

**መልመጃ፡** ነገሮች ተለውጠው ይሆን?ዮሴፍ ምን ተረዳ?ለእያንዳንዱ ጥያቄ በጥቅስ የተደገፈ ምላሽ ስጡ

1. እርስ በእርሳቸው እንዴት ነበር የሚቀባበሉት?________________________________
2. ስለቤተሰቦቻቸው ምን ወሬ ይዘው መጡ?________________________________
3. ስለቢንያም እንዴት ነበር የሚናገሩት ?________________________________
4. አባታቸው ቢንያምን ይወደው ነበር?________________________________
5. ወንድማማቾቹ ለአባታቸው ያላቸው ነገር ምን ይመስል ነበር?________________________________
6. የልባቸው ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?________________________________
7. በዮሴፍ ላይ ስላደረጉት ነገር እራሳቸው ወደምን አይነት ሁኔታ መጡ?________________________________

**ገለፃ:** ይህንን ታሪክ ስትከልሱት እና ጥያቄዎችን ስትመልሱ ምን ታስባላችሁ?ነገሮች ተለውጠዋል?እንደ ትልቅ ለውጥ የምታዩት ነገር ምንድነው?____________________________

______________________________________________________________

**ግላዊ ትግበራ:** አዎ የእነዚን ወንድማማቾች ነገር ተለውጧል፡፡ጊዜ እና ብስለት በህይወታችን ውስጥ ትልቅ ለውጥ ያመጣሉ፡፡

1. በህይወታችሁ ውስጥ ባህሪያችሁን ፣ማንነታችሁን፣እሴቶቻችሁን፣እንዲሁም ግንኙነታችሁን የተመለከተ መልካም ለውጥ በህይወታችሁ አይታችኋል?እስቲ ለይዋቸው፡፡ይህ ሁሉ ሆኖ ለወጥ በህይወታችሁ ባታዩ ምን ይሰማችኋል?እነዚህ ለውጦች ምን ምን ናቸው?__________________

______________________________________________________________

2. በጓደኞቻችሁ፣በወዳጆቻችሁ፣ወይንም አብሮአደጎቻችሁ ህይወት ውስጥ ያያችኋቸው አዎንታዊ ለውጦች ምንድናቸው?ልክ እግዚአብሄር በእኛ ህይወት ወስጥ ስራ እየሰራ እንዳለ እንዲሁም ደግሞ በሌሎች ህይወት ውስጥ እየሰራ ነው፡፡አስቲ ግዜ ወስዳችሁ እነዚህን ለውጦች ተከታተሏቸው፡፡______________________________________________

______________________________________________________________

3. እስቲ ያንን በለውጥ ላያ ያለን ወይንም ያለችን ሰው የምታበረታቱበትን ነገር አስቡ፡፡_______

______________________________________________________________

**ማሰላሰል:** የማበረታቻ ቃላት እግዚአብሄር በእኛ ህይወት ውስጥ እየሰራ አንደሆነ ለሌሎች የምናሳይበት መንገድ ነው፡፡ቅዱስ ጳውሎስ "በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና፤" ይለናል፡፡ እስቲ ግዜ ወስዳችሁ ፊሊጵስዮስን በቃላችሁ አሰላስሉት፡፡በካርዳችሁ ላይም ፃፉት፡፡በዚህ ሳምንት በዚህ ቃል መሰረት እግዚአብሄር በህይወታችሁ እየሰራ እንዳለ ተመልከቱ፡፡

**መልመጃ:** እነዚህ ወንድማማቾች ምንም እንኳን ግዜው ቢያልፍም እነዚህ ወንድማማቾች በተፈጠረው ነገር የበቀል ወይንም የጥላቻ ነገር የለባቸውም ይልቁኑም የፀፀት ነገር እንጂ ይህ ደግሞ በጣም የሚያስደስት ነገር ነው፡፡ስላለፈው ስህተታቸው ይፀፀቱ ነበር፡፡የጥፋተኝነት ስሜት ጥፋቱ ይቅር ካልተባለ በቀር እረፍት አይሰጥም ፡፡አስቲ ዘፍጥረት 42-44 ያለውን ክፍል ተመልከቱት፡፡ጥፋታቸውን የሚገልጡትን ቃላት ፃፏቸው፡፡

| ማጣቀሻ | ጥፋታቸውን የሚገልፁ ቃላት |
|---|---|
| 1. ዘፍጥረት 42፡21-22 | 1. ________________________________________ |
| | ________________________________________ |
| 2. ዘፍጥረት 42፡28 | 2.________________________________________ |
| | ________________________________________ |
| 3. ዘፍጥረት 44፡16 | 3. ________________________________________ |
| | ________________________________________ |

መስማት ያለባቸውን ነገር መስማት ያለባቸው በደል ካደረሱበት ሰው ነው ነገር ግን ይህ ሁል ጊዜ ላይሆን ይችላል።ዮሴፍ የት እንዳለ ማንም ያውቃል?ወንድሞቹ ሁሉ ያሚያውቁት ዮሴፍ እንደሞተ ነው?

**ጸሎት፡** ጌታ ሆይ ጥፋተኝነት ሊሸከሙት የሚከብድ ነገር ነው።አንዳንዴ እንደበደልን እንኳን ሳይታወቀን  እራሳችንን በደለን እንገኛለን።ለሌሎች ሳንጠነቀቅ በቸልተኝነት የምንናገረው ነገር ብዙዎችን ጎድቷል በሌሎች ደግሞ በማንነታቸው በመቅናት ሌሎችን ደግሞ ባላቸው ነገር በመመቅኘት በድላናል ።ባንተ ተፈጥረን አና ተወደን  ሳለን እንተን በድለንህል ጌታሆይ እራሳችንን ላይ በምናደርገው እንዲሁም ሌሎች ላይ በምናደርገው ነገር ።በድርጊታችነ ፣በንግግራችን፣ አንተን በበድልንበት ነገር ጌታ ሆይ ይቅር በለን።ዛሬ ጌታሆይ በራሴላይ ስለሰራሁት ኃጢአት ይቅር በለኝ፡

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ጓደኞቼን በበደልኩበት፣ቤተሰቦቼን እንዲሁም ሌሎችን በበደልኩበት ነገር ሁሉ ይቅር በለኝ

____________________________________________________________

የራሴን ፈቃድ በማድረግ እንዲሁም የአንተን ፈቃድ በመቃወም አንተን ክፉኛ በበደልኩበት በደል ሁሉ ይቅር በለኝ፡________________________________________________

____________________________________________________________

እንተ በእኔ ህይወት ወስጥ በስራ ላይ እንዳለህ ስላስረዳኸኝ አመሰግናለሁ።እኔ በለውጥ ላይ ያለሁ ያንተስራ ነኝ።አንተ አትተወኝም በእኔ የጀመርከውን ስራ ትፈፅማለህ________________________

____________________________________________________________

**ክፍል 5**

የቤት ስራ፡ ዘፍጥረት 45፡1-15 ያለውን ክፍል  አንብቡ።

**መልመጃ፡** ዮሴፍ ከዚህ በኃላ ሊይዘው አልቻለም።ይሁዳ በአባቱ ምትክ ሆኖ ስለቢንያም

ማለደ ።ዮሴፈን በከንአን ያለው የቤተሰቡ የህይወት ሁኔታ እንደተለወጠ አወቀ።

1. በእስር ውስጥ የነበረውን ዮሴፍ ሊፈታው ነው።በቁጥር 1 ላይ ያሉት ትእዛዛት ምንድናቸው?_______________________________________________.

2. አሁን ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋር ብቻውን ነው ያለው።የግብፅ ገዢ ከእነሱጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ብቻውን ሲሆን እዚህ ወንድማማቾች ምን አስበው ይሆን ?ግብፃውያን እንዲሁም የፈርኦን ቤተሰቦች እስኪሰሙት ድመፁን ከፍ አድርጎ እራሱን መቆጣጠር እስኪያቅተው ድረስ ሲያለቅስ።እናንተ ከወንድሞቹ እንዱን ሆናችሁ በዛ ብትገኙ ምን ይሰማችሁ ነበር?የቤቱ ተቆጣጣሪ ወይንም ፈርኦን እራሱን ብርሆኑ ምን ይሰማችኋል?____________

ዮሴፍ እስካሁን እራሱን አልገለጠላቸውም ።ምንም ነገር አልተነገራቸውም።እውነታው በጣም ያለቅስ ስለነበር ሊነግራቸው አልቻለም።

3. በቁጥር 3 ላይ በቀላሉ ዮሴፍ ምን ነበር ያላቸው?______________________________

4. በቀጥታ የጠየቃቸው ምን ነበር?__________________________________________

5. የወንድሞቹ ምላሽ ምን ነበር?___________________________________________

6. ዮሴፍ እንደገና ማን እንደሆነ ነገራቸው።ያፅናቸውም ጀመር።በቁጥር 5 ላይ ምን አላቸው___

---

________________________________________________________________________

ዮሴፍ እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር እዳለ አውቋል።አሁን እንኳን በዚህ የመገለጥ ግዜ ነገራቸው።___

________________________________________________________________________

ቀሪ አምስት የረሀብ አመታት እንደሚቀሩ እና እግዚአብሄር በዚህ ምክንያት እንዳመጣው እንደሚያምን ነገራቸው።_____________________________________________

እርሱ እራሱን እግዚአብሄር ቅሬታን ሊያተርፍ ታለቅ የሆነ ማዳንን ሊያድንበት እግዚአብሄር እየመራው እንደሆነ ተረድቷል።

7. እግዚአብሄር ስህተቶቹን እና ሁኔታዎችን በመጠቀም ለታለቅ ነፃ ማወጣት እንደተጠቀመበት አምኗል።ዮሴፍ ያደረጉበትን ከፋት የበደሉትን በደል እንዲሁም ከነጋዴዎች ጋር ወደግብፅ መምጣቱን እግዚአብሄር ለበጎ ለውጦ እንደተጠቀመበት አምኗል።በቁጥር 8 ላይ በነዚህ ሁሉ አመታት ግብፅ ውስጥ እግዚአብሄር ምን እንዳደረገ ይነግረናል ።

1. ________________________________

2. ________________________________

3. ________________________________

**ገለፃ፡** እንዴት አይነት ድራማዊ ትእይንት ነው?ወንድሞቹ ወደእቤት ተመለሱ፡፡ በግብፅ ከፈርኦን ጎን ለጎን ኃይል ያለው እንዲገደሉ ወይንም እንዲለቀቁ ማድረግ የሚችለው ወንድማቸው ነው፡፡እንደማንኛውም አይነት ወንድም አይደለም ነገር ግን የምድሪቱ ገዢ ነው፡፡ዮሴፍ እዛ ስፍራ ላይ ለመቀመጡ ምንም ድርሻ የለውም ፡፡የሚያውቀው አንድ ነገር ግን እግዚአብሄር በስራ ላይ መሆኑን ነው፡፡ይህን ሁሉ ያደረገው እግዚአብሄር ብቻ ነው፡፡በወንድሞቹ መካከል የተፈጠረውን አስቀያሚ ነገር ህዝብን ነፃ ማውጫ መንገድ አድርጎ የተጠቀመው እግዚአብሄር ነው፡፡ይህ ነፃ መውጣት የጠቀመው ግብፅን ብቻ አይደለም ነር ግን በግብፅ ዙሪያ ያሉትን ሃገራት ነው፡፡

ስለዚህ እናንተ በግብፅ የነበረውን ሁኔታ ለመዘገብ የተገኛችሁ ጋዜጠኞች ናችሁ፡፡ይህ ገዢ ከአስራ አንዱ ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ሲተው ማንባቱን የሰማችሁት ከግብፃውያን ነው፡፡እናንተ ታሪኩን ዘጋቢዎች ናችሁ እንበል፡፡እግዲን ቃለ መጠይቅ ብታደርጉ ማንን ነው ቀድማችሁ ቃለመጠይቅ የምታደርጉለት?ለምን?ምንድነው ልትጠይቁት የምትፈልጉት?____________________________

____________________________________________________________________

ይህ ሰብአዊ ታሪክ ዮሴፍ የሚባል እግዚአብሄር ሰዎችን ለማዳን ያዘጋጀው ሰው በፈታው ህልም ምክንያት ለሰባት አመታት የሚሆን ምግብ እንዲከማች እቅድ ያስወጣ ነው?ወይንስ ይህ ታሪክ ሌላ ጠቀሜታ አለው?ለምንድነው ይህንን ልዩ ታሪክ አንድትዘግቡ አለቃችሁ ወደግብፅ የላካችሁ?ይህንን የህዝቦችን ህይወት የነካውን ዘገባ ስተዘግቡ እና ቃለመጠይቅ ስታደርጉ ጠቀሜታ ያለውን እና ጎልቶ የታያችሁ ነገር ምንድነው?____________________________________

____________________________________________________________________

**ማሰላሰል፡** ሶስተ ግዜ ዮሴፍ የተናገረው ነገር ይህንን ነው "እግዚአብሄር ላከኝ______________________________________________________________

____________________________________________________________________

"መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉታሪኮቸን ስታነቡ በተለያዮ ስፍራዎች ላይ እግዚአብሄር ሰዎች ሲልክ ታያላችሁ፡፡ይህ ታሪክ ሊታለፍ የማይችል ቃል የያዘ ጥቅስ ይገኝበታል እሱም ዘፍጥረት 50፡20___________________________________________________________

____________________________________________________________________

ይህንን ቁጥር ለማሰላሰል ከምትይዟቸው ቁጥሮች ጋር አብራችሁ ይዛችሁ አሰላስሉት፡፡ምንም እንኳን ሀሳቦቻችን ፣ድርጊቶቻችን፣ንፁህ ባይሆኑ እንኳን አግዚአብሄር ለመልካም ቀይሮ ሀዝብን የሚጠቅም ነገር ሊያደርገው አንደሚችል ይህ ክፍል ያስታውሰናል፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ለምታልፉ ለእናንተ በሮሜ 8፡28 ላይ የሚገኘውን መልእክት ይሰጣችኋል፡፡፡ጥፋተኝነት ህይወታችንን ይበላዋል እግዚአብሄር በህይወታቸን ያሉት ሁኔታዎች ለክፉ ቢመስሉም እንኳን

በክርስቶስ እየሱስ  እግዚአብሄርን ለሚወዱት ነገርን ሁሉ ለበጎ ሊለውጥ ይህንንም ሊለውጥ ሊያንቀሳቅሰን እና ሊያሳስበን ይወዳል፡፡

**ጸሎት፡** ስለማይገለፀው ፍቅሩ እግዚአብሄርን  አወድሱት አመስግኑትም፡፡ህይወታችን የሱን ክብር እና ግርማ እንዲገልፁ ይፈልጋል፡፡_______________________________________________

_______________________________________________________________

# ትምህርት ስድስት

# አባቴን ወደ እዚህ አምጡት

## ዘፍጥረት 45፣46፣50 -ልጁ

---

**ቅኝት ትምህርት ስድስት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 6፡ ዘፍጥረት 45፣46፣50

- ወንድማማቾቹ ወደያዕቆብ ተመለሱ
- የደስታ ቀን
- ያዕቆብ ንብረቱነ ሽክፎ ከነአንን ለቆ ተጓዘ
- ቀል ተጠብቋል
- አባት እና ልክ እንደገና ተገናኙ
- ይቅርታ ፍርኀትን አስወገደ

## መግቢያ

የዮሴፍ ታሪክ አባቱን ወደግፅ እንዲያመጡ በማስገደድ ይቀጥላል ሆኖም ግን በመጨረሻ አባት እና ልጅ ተገናኙ! ሁሉም ነገር መሆን እንዳለበት ሆነ፡፡አባትም ለአብርሐም ፣ለይስሀቅ ፣ለያዕቆብ ተስፋ ከተሰጠችው  ምድር ለቆ ከቤተሰቦች ጋር በአንድነት ሆነ፡፡አባቱ እና አያቱ ከተቀበሩበት ምድር ለቆ ሄደ፡፡ አሁን ልጁ የሀገሪቱ ሁለተኛ ገዢ ወደሆነበት ምድር ሄደ፡፡

ያዕቆብ እድሜው  ገፍቷል ፡፡ከመሞቱ በፊትም እያንዳንዱን ልጆቹን መባረክ አለበት የመጨረሻውንም  ጥያቄ ይጠይቃል፡፡መቀበር የሚፍለገው አብርሀም ለቀብር ማስፈፀሚያ በከነአን በገዛው ዋሻ ውስጥ ነው፡፡ግብፅ የተስፋይቱ ምድር እንዳልሆነች እና የሚቀበረውም እዛ እንዳልሆነ ያውቃል፡፡

ነገር ግን ያዕቆብ ሞቶ በከነአን ከተቀበረ እንደገና በወንድማማቾቹ መካከል ያለው ግንኙነት አደጋ ላይ የመውደቁ ፍርሀት በወንድማማቾቹ ልብ ውስጥ አለ፡፡ወንድማማቾቹ የዮሴፍ ይቅርታ የሚዘልቀው ያዕቆብ በህይወት እስካለ ግዜ ድረስ እንደሆነ እና ያዕቆብ ሲሞት ዮሴፍ ላደረጉበት እያንዳንዱ ነገር እንደሚበቀላቸው አስበው ነበር፡፡ነገር ግን ይህንን ፍርሀታቸውን የሚያስወግድ ይቅርታ ሆነ ፡፡ምክንያቱም ይቅርታ ፍርሀትን ያስወግዳል፡፡

## ክፍል 1

**መግቢያ፡** በመጨረሻ ዮሴፍ እና ወንድሞቹ ተቀላቀሉ፡፡ ቀጥሎ ምን ተፈጠረ?ዮሴፍ ያዩትን እና የሰሙትን በሙሉ ለአባታቸው እንዲነግሩት ነገራቸው፡፡አባቱ በግብፅ ያለውን ከፍኛ ቦታ እንዲያውቅ ፈልጓል፡፡የረሀቡ ግዜ ለአምስት አመታት ስለሚዘልቅ አባታቸውን ወደግብፅ አምጥተውት የረሀቡ ግዜ እስኪያልቅ ድረስ በጌሴም እንዲቀሙጠ ነገራቸው፡፡

ወንድሞቹም ከእርሱ ጋር ግዜ አሳለፉ ያለጥርጥርም ያለፈው በደላቸው እንደተደመሰሰ አረጋገጡ፡፡ዮሴፍም ሌሎችን ለማዳን እግዚአብሄር አስቀድሞ እንደላከው አውቋል፡፡ወደዚህ ምድር የላከው እና በምድሪቱም ላይ የሾመው እግዚአብሄር እንደሆነ አምኗል፡፡ስለዚህም ይቅር ብሏቸዋል፡፡በቤተሰቡ ሁሉ ላይ ቸርነቱን አድርጎላቸዋል፡፡የሚኖሩበትንም በጎቻቸውን እና ከብቶቻቸውን የሚያሰማሩበትም ምድር ሰጥቷቸዋል፡፡ባሉበት ምድር ሆነው በረሀብ እንዲጎዱ አልፈለገም ፈጥነው ካሉበት ስፍራ እንዲመጡ አደረገ፡፡ከመሄዳቸውም በፊት ተቃቀፉ ፣ተሳሳሙ፣ሁሉም ተላቀሱ፡፡

ፈርኦንም እራሱ በመገኘት በምድሪቱ ላይ እንዲኖሩ እና የምድሪቱንም የሰባ በረከት እንዲካፈሉ ጠየቃቸው፡፡ዮሴፍ ቃል የገባላቸውን ነገር ፈርኦንም አፀናላቸው፡፡በተጨማሪም ቤተሰቡን ለማጓጓዝ የሚጠቅሟቸውን ሰረገላ እንዲሁም የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንዲወስዱ ፈቀደላቸው፡፡በግብፅ ያለው ማንኛውም መልካም ነገር የእነሱሠ እንደሆነም አረጋገጠላቸው፡፡

**የቤት ስራ፡** ዘፍትረት 45፡16-28 ያለውን ክፍል አንብቡ፡፡

1. ወንድማማቾቹ ከቤት ተልከው ወጡ፡፡እንደገና ጭነታቸውን ጭነው ተነሱ፡፡ዮሴፍ ምን ነበር የሰጣቸው (ቁጥር 21፣22)?________________________________________
2. አሁንም በድጋሚ ለቢንያም መልካም ተደረገለት (ዘፍጥረት 43፡ 34 እንዲሁም 44፡2) በቁጥር 22 ላይ ምን ሰጠው? ________________________________________
3. ለአባታቸውስ ምን ላከ (ቁጥር 23)?________________________________________
4. በግብፅ ያለውን ምርጥ ነገር አስይዞ ዮሴፍ ወንድሞቹን ሰደዳቸው፡፡ወንድሞቹን ለመጨረሻ የላካቸው መልእክት ምን ነበር ቁጥር 24?________________________________________
   ለምን ነበር እንደዛ ያላቸው?________________________________________

**ትምህርት፡** የዮሴፍ የመጨረሻው አስተያየት የሆነው የስንብት ቃል “ደህና ሁኑ በመንገድ እርስ በርሳችሁ አትጣሉ።”ነገር ግን የሰው ተፈጥሮ ሌላውን የሚነቅፍበት ነገር ይፈልጋል።ምክንያቱም ሰው መርካት የሚችለው እና በኅሀሊና የሚኖረው ከጥፋተኝነት ስሜት ነፃ ሲሆን ብቻ ነው።በመጀመሪያው ጉዟቸው ከግብፅ ሲመለሱ ምን እየተነጋገሩ እንደነበር አስታውሱ።ይህ ጭንቀት ለምን እንደመጣባቸው ሲነጋገሩ ሮቤል ያለውን ነገር አስታውሱ ዘፍጥረት 42፡21-22። “ቀድሞውኑ ነግሬያችሁ ነበር” የሚል ነበር።” እኔ አይደለሁም ይህ የእኔ ጥፋት አይደለም የሚለው አባባል የሁላችንም ችግር ነው።መነቃቀፍ ልክ በአየር ላይ ከአንዱ ሰው ወደሌለው እንደሚነጥር ኳስ ነው።ከእኔ አርቅልኝ ይህ የሌላ ሰው ጥፋት ነው።እሱ ነው! እሷ ነች!

**የአመለካከት ጥያቄ፡**

1. ወንድማማቾቹ ይቅር ተባብለው ይሆን? የእናንተ አመለካከት ምንድነው?______________

________________________________________________________________

2. እራሳቸውንስ ይቅር ብለዋል? ስለዚህስ ምን ታስባላችሁ?__________________________

________________________________________________________________

<u>**ክፍል 2**</u>

**ግላዊ ገለፃ፡** ነቀፌታ ወደእናንተ ሲመጣ እንዴት ነው የምታስተናግዱት?ሁላችንም የየራሳችንን ችግር መናዘዝ እና ነቀፌታችንን መቀበል መልመድ ይኖርብናል።

1. በፍፁም ጥፋቴን መቀብል አልፈልግም
2. የሰራሁትን ትፋት ተከትሎ የሚመጣውን ማንኛውም ነገር ለመቀብል ፈቃደኛ አይደለሁም
3. እኔ ነፃ ልሁን ጥፋተኝነቱን እናንተ ተሸከሙ።
4. አንተ ከነገሩ ጋር ስትታገል ባይህ ምንም አያስጨንቀኝም ምክንያቱም ጥፋቱ ያንተነው።
5. ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍልህ እራስህ ብቻህን ተጋፈጠው
6. አንተ ካደረከው ጋር ሳነፃፅረው የእኔ ጥፋት ሚዛን አይደፋም
7. በርግጥ ምን እንዳጠፋሁ እንኳን አላውቅም
8. ጥፋትን ለመቀበል ወይንም ላለመቀበል የምትተቀሚቸውን ቃላቶች ቀጥላችሁ ሙሏቸው____

________________________________________________________________

ጥፋቴን የማልቀበል እና ነቀፌታዬን የማልወስድ ከሆነ በህይወቴ ውስጥ ምንም ለውጥ አይመጣም።ጥፋቴን አምኜ ስናዘዝ እግዚአብሄር ይቅር ሊለኝ እና ከበደሌ ሊያነፃኝ እና ማንኛውም ከእግዚአብሄር ያልሆነውን ነገር ከህይወቴ ሊያስወግድ በጉጉት ይጠብቃል ።የምታሰላስሉትን ጥቅስ አስታውሱ እስቲ ቃሉን በድጋሚ ፃፉት 1 ዮሐንስ 1፡8-10 ________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

**ጸሎት** ፡ ጌታሆይ ጥፋቴን ለመቀበል በጣም እንደተቸገርኩ የገዛ ጥፋቴን ነቀፌታ ለመቀበል አንዳቃተኝ አሁን ማመን እፈልጋለሁ።እኔ እንደ ሮቤል ነኝ።ላለሁበት ችግር ተጠያቂው እኔው መሆኔን እያወቅሁ ነገር ግን ችግሬን ላለመቀበል ዙሪያ ጥምጥም መሄድ ይቀናኛል።ሁልግዜ ጥፋቴን እና የጥፋቴን ውጤት መቀበል ይቸግረኛል።ሌላው ቀርቶ ከሁሉ በላይ ለጥፋቴ እንኳን ምህረት እንደሚያስፈልገኝ መቀበል ያቅተኛል።ነቀፌታዮን መቀበል እንደውርደት እቆጥረዋለሁ።ነገር ግን ጌታ ሆይ በደለኛ ነኝ አጥፍቻለሁ።ኃጢአቴን መናዘዝ እፈልጋለሁ።ያንተን የይቅርታ ቃል መስማት እፈልጋለሁ። ሽክም ከሆነብኝ የጥፋተኝነት ስሜት ነፃ ሊያወጣኝ እና ሊያድነኝ የሚችለው ህይወቴንም በተስተካከለ መልኩ መምራት የሚስችለኝ ያንተ የይቅርታ ቃል ነው።በልጅህ በእየሱስ ክርስቶስ ከእስራቱ ተፈትቻለሁ። ስለወደድከኝ እና ነፃ ስላወጣኸኝ አመሰግናለሁ።______________________________________________________

________________________________________________________________________

_______________________________________________________________

**አመለካከት፡** አስራ አንዱም ወንድማማቾች ወደ አባታቸው ቤት ወደ ከነአን እየተጓዙ ነው።እስቲ ይህ ስብስብ የነበረበትን ሁኔታ አስቡት።ያለጥርጥር ሁሉም የራሱ የሆነ አስተሳሰብ እና አመለካከት ይኖረዋል ።እንደዚህ የሚሉ አስተያቶችም ከአንዳንዶቹ ሊሰማ ይችላል "እንዴት አይነት እውሮች ነበርን" ሌላው ደግሞ "እኔ በጣም ደስ ብሎኛል እናንተ አባታችን እንደገና ደስ ሊለው ነው?" ብትፈልጉ እናሲዝ አባታችን ይህን ጉድ አያምነንም "።

**መልመጃ፡** የአባታቸውን ደስታ ለመገለፅ ያስቸግራል።

1. ልጆቹ የነገሩትን ነገር ያዕቆብ እንዴት ነበር የተቀበላቸው ቁጥር (25-28)?_____________

ሀ. ምን ነገሩት (ቀጥር 25)?______________________________________

ለ. የያዕቆብ ምላሽ ምን ነበር?______________________________________

ሐ. አለማመኑን ወደ ማመን የቀየረለት ምን ነበር መንፈሱን ያነቃቃው ምን ነበር?________

መ. በቁጥር 28 ላይ ምን አላቸው?______________________________________

**ክፍል 3**

**የቤት ስራ፡** ዘፍትረት 46፡1-7 46፡26-27 ያለውን ክፍል አንብቡ፡፡

**መልመጃ፡** እንዴት ያለ የደስታ ቀን ነው!

1. ያዕቆብ (እስራኤል) ልቡ አሁን በህይወት እዳለ ያወቀውን ልጁን ለማግኘት እንደጓጓ በከነአን ካለችው ከኬብሮንን ተነስቷል በምንገዱም በቤርሳቤህ አልፏል ፡፡በዛም ለአባቶቹ አምላክ ለእግዚአብሄር መስዋእትን አቅርቧል፡፡ ያዕቆብን ከነአንን ለቆ እንዳይወጣ ችግር የፈረጠረበት ነገር ምንድነው? ____________________________________________________

______________________________________________________________

እግዚአብሄር ለአብርሐም ፣ለይስሀቅ፣እንዲሁም ለያዕቆብ ተስፋ ስለገባላቸው ነገር የምታውታውሱት ነገር ምንድነው፡፡

2. ቁጥር 2-4 እግዚአብሄር ወደ እስራኤል የመጣው በ________________________________

ሀ. ጠራው______________________________________________________

ለ. ምላሹ ምን ነበር?____________________________________________

ሐ. እግዚአብሄር እራሱን ለያእቆብ ያስተዋወቀው እንዴት ነበር________________________

መ. እግዚአብሄርም ለያዕቆብ ወደግብፅ መሄድ እንዳይፈራ ነገረው በዛም የተስፋ ቃል ሰጠው፡፡

1. ________________________________________________
2. ________________________________________________
3. ________________________________________________
4. ________________________________________________

**አመለካከት፡** በዚህ አጭር ግዜ ብዙ ነገር ተከናወነ፡፡ያዕቆብ የዮሴፍን በህይወት መኖር እንዳመነ ወዲያውኑ በፍጥነት ለመጓዝ እንዲያስችላቸው ዕቃዎቻቸውን መጫን ጀመሩ፡፡በዚህ ሁሉ ውክቢያ መካከል ለያዕቆብ በጉዞው እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡ለእሱ እና ለአባቶቹ የገባለትን የተስፋ ቃል እግዚአብሄር እንዴት ነው የሚፈፅምለት፡፡እግዚአብሄር አብሮት መኖር እና እንደገባለት የተስፋ ቃል ህዝብ ሊያደርገው ይገባል፡፡ዘሮቹም ወደተስፋይቱ ምድር

ይመስሳሉ አሁን ግን ወደሞት ከመሄዱ በፊት ዮሴፍን ማየት አለበት፡፡

1. ያዕቆብ በማለዳ ተነስቶ ሁሉም ጉዞውን ለመጀመር በዙሪያው ተከማችቶ ባለበት ሰአት በያዕቆብ ልብ ውስጥ ምን አይነት ሀሳብ ያለ ይመስላችኋል?እንደገና የአባቶቹ አምላክ ወደእሱ መጣ ሌሎች ግዜያቶች ነበሩ________________________________________________

ሀ. በዘፍጥረት 28፡10 እና በተከታዮ ቁጥር ላይ የነበረው ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?_______________________________________________________

_______________________________________________________

ለ. ኤሳውን ከማግኘቱ አንድ ቀን ሰደም ብሎ የነበረውን ሌሊት አስታውሱ፡፡በዛ ሌሊት ምን ነበር የረፈጠረው (ዘፍጥረት፡ 32፡22) እና ተከታዮ ቁጥር_______________

_______________________________________________________

2. የከነአንን ምድር ለቆ መሄድ ለያዕቆብ ቀላል ነገር አይደለም፡፡የሚወዳት ሚስቱ ራሄል ፣አባቱ ይስሀቅ እና ርብቃ የተቀበሩበትን ስፍራ ነው ጥሎ የሚሄደው፡፡ጥሎት የሚሄደውን ይህንን ስፍራ ከዚህ በኋላ በፍፁም ሊያየው አይችልም፡፡ስፍራውን ለቆ ወደሌላ ወደማያውቀው ሀገር ነው አዲስ እና አስገራሚ ጉዞ የሚያደርገው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ በጭንቀት እና በጥርጥር የተሞላ ማንነት ይታያል፡፡በቁጥር 4 ላይ እግዚአብሄር ያዕቆብ እንዲያስታውሰው የፈለገው ነገር ምን ነበር?_______________________

_______________________________________________________

3. ለያዕቆብ እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር ለመሆኑ ምን ያለ ምልከት ነበር ?እናንተስ በህይወታችሁ ውስጥ በየትኛውም ስፍራ ስትንቀሳቀሱ እግዚአብሄር ከእናንተ ጋር መኖሩን በምን ታውቃላችሁ ?የምታውቁበት መንገድ አለ?______________________________________

_______________________________________________________

<u>**ክፍል 4.**</u>

**ማሰላሰል** ፡ ለያዕቆብ እግዚአብሄር ከእርሱ ጋረ መኖሩን በማወቁ በታላቅ መፅናናት እና እርግጠኝነት ነበረ፡፡ለእኔ እና ለእናንተም የእግዚአብሄር ከእኛ ጋርመሆን ልክ ለያዕቆብ እደሆነለት በእርሱ መገኘት መፅናናት ይሆንልናል ፡፡በመዝሙር 139፡7-10 መዝሙረኛው ዳዊት እንዲህ አይነት ጥያቄ ይጠይቃል "ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ ከፊትንስ ወዴት እሸሻለሁ?" ምንም ያህል ርቀን ብንሄድ እግዚአብሄር ከእኛ ጋር ይኖራል፡፡ቃሉ ይህንነ ይነግረናል፡፡ይህም ደግሞ እውነት ነው፡፡በድጋሚ ይህንን ጥቅስ በካርዳችሁ ላይ ፃፉበት በካርዱ ጀርባ ላይም የትም ቦታ ብትሄዱ

እግዚአብሄር  በእዛ እንደሚኖር  የሚያስታውሳችሁ ማስታወሻ ፃፉበት፡፡

**ግላዊ ትግበራ፡**

1. በሁሉ ስፍራ እግዚአብሄር ከእናንተ ጋር መሆኑን ስታስቡ ምን አይነት መፅናናት ወደውስጣችሁ መጣ?________________________________________

________________________________________

2. የእግዚአብሄር ከእናንተ ጋር መሆን እየተሰማችሁ ነገር ግን በዛ ስፍራ መሆናችሁ ደስተኛ የማያደርጋችሁ ስፍራ ይኖር ይሆን?________________________________________

________________________________________

3. አንዳንድ ስፍራዎች ስትሄዱ የእግዚአብሄር መገኘት በደንብ ይሰማችኋል፡፡ይህ ስፍራ ምናልባት የተራራ ጫፍ ወይንም ሆስፒታል ውስት ሊሆን ይችላል፡፡እግዚአብሄር በዛ እንዳለ እየተሰማችሁ የምትሄዱበት ስፍራ የትኛው ነው?________________________________________

________________________________________

**ጸሎት፡** እስቲ የራሳችሁን ጸሎት ፃፉት እናንተ በዚያ ስትገኙ እግዚአብሄር በዚያ እንዳለ ስለሚሰማችሁ ስፍራ እና መገኘቱ ስለማይሰማችሁ ስፍራ እስቲ ለጌታ አካፍሉት፡፡የእግዚአብሄር አብሮአቸሁ መገኘት ምቾት ስላልሰጧችሁ ስፍራዎች እስቲ በጌታ ፊት ተናዘዙ፡፡የትም ብትሄዱ ምንም እይነት ስራ እየራችሁም ቢሆን እግዚአብሄር ከእናንተ ጋር ስላለ ደስ ይበላችሁ፡፡የመገኘቱ አውነት በእናንተ ማንነት ላይ የተመሰረት አይደለም ነገር ግን ግሩም በሆነው ፍቅሩ ለይ ነው፡፡________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

**ትምህርት፡** መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ከከነአን እየወጣ ያለ ተጓዥ ስብስብ ምን እንደሚመስል እንድናስተውል ይፈልጋል፡፡ብዙ ነጥቦችን መመልከት ይቻላል፡፡

1. እስከዚህ ግዜ ድረስ የአብርሐም ቤተሰቦች በቁጥር ጥቂት ነበሩ፡፡መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅስልን አብርሐምን ፣ሳራን፣ይስሰቅን፣ ከዛም የይስሀቅ ሚስት ርብቃን ፣ያዕቆብ እና ኤሳውን ብቻ ነበር፡፡የያዕቆብ ቤተሰብ አባላት በግብፅ ቀድሞውኑ ካለው ከዮሴፍ በስተቀር አስራ አንዱ ብቻ እንደነበሩ ነው፡፡ታሪኩን ስንቀጥል የተስፋው ፍፃሜ የሆነውን የያዕቆብን

ዘር እናያለን፡፡

2. እግዚአብሄር ለህዝቡ ያለው ተስፋ የሚፈፀመው በቀጥታ ብቻ አይደለም፡፡አብርሐም ወደ ከነአን መጣ በዛም የተስፋውን ቃል ተቀበለ፡፡ብዙ ህዝብ እንደሚሆንም የተስፋ ቃል አገኘ፡፡ከዛም ሳራ መካን እንደነበረች እንመለከታለን፡፡አሁን ደግሞ ከነአን የያዕቆብ ቤተሰብ ንብረት እንደሆነች እንመለከታለን፡፡ከዚህ ስፍራ እየለቀቁ ያሉት በረሀቡ ምክንያት እንደሆነ እንመለከታለን፡፡እስቲ ህይወታችሁን ተመልከቱ ፡፡ህይወት ነጭ እና ጥቁር ሆና አይታችኋት ታውቃላችሁ ?ነገሮች ሁልግዜ እንዳቀድናቸው አይሄዱልንም ፡፡ ግቦች ፣እቅዶች ፣ውጥኖች ልናደርጋቸው የምንፈልጋቸው ነገሮች ይኖራሉ የእዚህን ውጥኖቻችንን ፍፃሜ ላይ ለመድረስ ብዙ ውጣውረዶችን ማለፍ ይኖርብናል፡፡እናንተስ በእንደዚህ አይነት መልኩ አቅዳችሁ በእቅዳችሁ መሰረት ነገሮች ሳይሄዱ ቀርተው ያውቃሉ?____________________________

____________________________________________________________________

3. የተጓዦቹ ቁጥር በዝቷል አንድነት የጓዙት ከ 70 በላይ ይሆናሉ፡፡ይህ ቀላል አይደለም ፡፡ከፈርኦን የተሰጧቸው ሰረገሎች ዕቃዎቻቸውን ለማጓጓዝ በጣም ጠቅመዋቸዋል፡፡ይህ እግዚአብሄር የገባውን የተስፋ ቃል እንደሚፈፅም የሚያሳይን ምሳሌ ነው፡፡

4. በአንድነት የጓዝን ቤተሰብ ምሳሌም ይሆኑልናል፡፡የያእቆብ ልጆች፣እና የልጅልጆች ሁሉም በአንድነት ይጓዙ ነበር፡፡ይህ የያዕቆብ በአንድነት የሚጓዝ ቤተሰብ የእኛንም ቤተሰብ እንድናስብ ያደርገናል፡፡የብዛት ጉዳይ ሰይሆን በአንድነት መያያዙ ነው ትርጉም ያለው፡፡ማንም ወደኋላ አይቀርም፡፡ሁሉም ብግብፅ ለሚጀመረው አዲስ ህይወት ተዘጋጅቷል፡፡አንድነታቸው ለቤተሰቡ ትልቅ ጥንካሬ ሰጥቷቸዋል፡፡ቁጥር 8-27 በዚህ ጉዞ ውስጥ የተካተቱትን በሙሉ ዘርዝራቸውን ይገልፅልናል፡፡

**ገለፃ፡** የዚህን ተጓዥ ቤተሰብ ስንመለከት በአይነ ህሊናችን እግዚአብሄር ለአብርሐም ሰይስሀቅ እነደገናም ለያዕቆብ የገባውን የተስፋ ቃል እንዴት እንደሚጠብቅ ያስታውሰናል፡፡እስቲ በሀሳባችሁ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ተጓዙ ትንንሾቹን ተሸክመው፣አንዱ አንዱን እያበረታ የደከመውን ሙቀቱ ያደከመውን እያገዘ ፡፡ደግሞ መንድማማቾቹ በአዲሱ ምድር ስለሚኖሩት አዲስ ህይወት እየተነጋገሩ ሲሄዱ አሰባችኋቸው፡፡እናንተ የቴሌቪዥን ካሜራማን ብትሆኑና ይህንን ጉዞ እየተከታተላችሁ የምትዘግቡ ቢሆን አብዛኛውን ግዜያችሁን የምታሳልፉት ከማን ጋር ይሆናለ?ለምን?

____________________________________________________________

**ክፍል 5**

**የቤት ስራ፡** ዘፍጥረት 46፡28-30 ያለውን ክፍል አንብቡ።

***መልመጃ፡*** ተጓዦቹ ወደግብፅ እየደረሱ ነው።

1. ያዕቆብ ይሁዳን ላከው።ምን እዲያደርግ ነበር የላከው(ቁጥር 28) ?____________________

2. ጌሴም አካባቢ ደርሰዋል።እስቲ በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ ባለው አንዱ ካርታ ላይ የጌሴምን ምድር አመልከቱ ።ምን ያህል እንደተጓዙ ፃፉ ።አስታውሱ ቤርሳቤህ አካባቢ ነገር እግዚአብሄር ለያዕቆብ በራዕይ የተገለጠለት።ከቤርሳቤህ እስከ ጌሴም________________ኪሎሜትር ይሆናል፡

3. ዮሴፍ ሰረገላውን አዘጋጅቶ እየተጠባበቀ ነው የአባቱን መቅረበረ ሲሰማ _______________

4. ምንኛ የተባረካ ቅልቅል ነው።እስቲ በቁጥር 29 ላይ የነበረውን የአባት እና የልጅ ስሜት ግለፁት?______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

5. የዕቆብ የሚፈልገው ከዮሴፍ ጋር እንደገና መኖርን ነው።ልቡ እረክቷል።ከዚህ በኋላ ልጁ በምን አይነት ሞት እንደሞተ ማሰብ አከተመ።እግዚአብሄር በቸርነቱ በቤተሰቡ ላይ ፈውስ አምጥቷል።ያዕቆብ እና ዮሴፍ እንደገና ተቃቀፉ።

**ግላዊ ትግበራ፡** ያዕቆብ የገጠመው ችግር መለያየት ብቻ አልነበረም ነገር ግን ከዛም የለፈ ነበር።የልጁን በህይወት መኖር አለመኖር እንኳእርግጠኛ አልነበረም።በዚህም ዘመን በብዙ የዜና አውታሮች ልጆች ቤተሰቦቻቸው ታፍነው መወሰዳቸውን እንዲሁም ከቤተሰቦቻቸው የመጥፋታቸውን ዜና በየእለቱ እንሰማለን።ወታደሮችም ግዳጃቸውን ለመወጣት ወደሌላ ሀገር በመሄድ ለብዙ ግዜያት ከቤተሰቦቻቸው እና ከወዳጆቻቸው ተለይተው ይቆያሉ ።የዚህ አይነት ተመሳሳይ ነገር ገጥሟችሁ ያውቃል? ከመለያየት ይልቅ የሚከብደው የተለያችሁት ሰው ያለበትን ሁኔታ ማለትም ክፉ ወይንም ደግ ነገር ሳይሰሙ መቅረት ነው።

1. እስቲ እንደዚህ አይነት ችግር የገጠማችሁ እናንተ ብትሆኑ የገጠማችሁን ይህንን ሁኔታ መግለፅ ትችላላችሁ______________________________________________

2. እንደዚህ አይነት ገጥሟችሁ የምታውቁ ከሆነ ሁኔታው በሰላም ተጠናቀቀ ?ተጠናቆ ከሆነ ስሜቱ ምን ይመስል ነበር?ተጨማሪ የምትነግሩን ነገር ይኖር ይሆን?_________________

   ______________________________________________________________

3. እንደዚህ አይነት ነገር እናንተን የገጠማችሁ ነገር ላይሆን ይችላል ነገር ግን እናንት የምታውቁት እንዚህ አይነት አሳዛኝ ታሪክ ያለው የሚወደውን አጥቶ የሚሰቃይ ሰው ታውቁ

ይሆን ?፧እንደዚህ ላዘነ እና ለተጎዳ ሰው የሚኖራችሁ ማፅናኛ ምድነው?_______________

_________________________________________________________________

4. ልክ ያዕቆብ ልጁን አቅፎ እንዳለቀሰ አናንተንም በተመሳሳይ መልክ ሊያገኟችሁ ለሚፈልጉ ሰዎች እንዲያገኟችሁ ምን አይነት መንገድ ትፈጥሩላቸዋላችሁ?______________________

_________________________________________________________________

5. የጥፋተኝነት ስሜት እና ኃጢአት ከሰዎች ፊት ካሸሻችሁ ይህንን ሁኔታ ለመወጥ ምን አውነታ አለ?_____________________________________________________

_________________________________________________________________

6. የእናንተ ድርሻ ምንድነው?________________________________________

እግዚአብሄር መለኮታዊ በሆኑ አጆቹ ሊያቅፈን ይገልጋል ፡፡እንደገና ከእርሱ ጋር ወዳለው ቤተሰባዊ ግንኙነት ሊመልሰን ይፈልጋል እሱ የእኛ አባት እና ፈጣሪ ነው፡፡ልክ እንደ ልጅ ወደ እቤቱ እስክንመለስ ያለማቋረጥ ይመለከተናል፡፡የራሳችንን መንገድ መርጠን እንደነበርንና እንደተሳሳትን በእግዚአብሄር ፊት ማመን አለብን ፡፡በምንኖርበት ዓለም ውስጥ የሱን ባህሪ ልናንፀባርቅ ሲገባን ያንን ማድረግ እንዳልቻልን በእርሱ ፊት መናዘዝ አለብን፡፡ነገር ግን ካለንብት ስፍራ ወጥተን ወደሱ እስክንመጣ ድር ፍቅር እጆቹን ዘርግቶ ይጠብቀናል፡፡አግዚአብሄር እንደልጅ ከጠፋንበት ስፍራ ተመልሰን ወደእቅፉ ስንገባ በደስታ በእንባ እንደሚቀበለን ታውቃላችሁ?

**ጸሎት፡** አባት ሆይ አንተ ፈጥረህኛል ፡፡ላንተ በህይወቴ እንድሆንልህ የምትፈልገው ነግር አለ፡፡የፈጠርከኝ አንተን ለፍጥረት ሁሉ እንዳንፀባርቅ ነው፡፡የአንተን ምህረት በህይወቴ እንዳሳይ ከሰጠኸኝ ነገር አንዱ ነፃ ምርጫዬ ነው፡፡እባክህ ደስታ እና ሰላምን እንዲሁም ባንተ ያለውን ፍፁም ነፃነት እንዳገኝ እርዳኝ፡፡በምህረትህ እና በፍቅርህ ስለተመለከትከኝ አመሰግንሀለሁ፡፡አዳኝ እና ጌታ በሆነው በልጅህ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል ካንተ ጋር አንድ እንዳደረከኝ አባክህ ወደራስህ አስጠጋኝ በእቅፍህም ያዘኝ፡፡________________________________________________

_________________________________________________________________

______________________________________________________

**በጥልቀት መመልከት፡** መጽሀፍ ቅዱስ ስለዚህ ቤተሰብ በተቀሩት የዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፎች ውስጥ መናገሩን ይቀጥላል ፡፡ታሪኩ በጣም አስደሳች እና ተጨማሪ መረጃዎችን የሚሰጠን ነው፡፡ለሚቀጥለው ጥናት የሚከተሉትን ዝርዝሮች ተመልከቷቸው፡፡

- ዘፍጥረት 46፡3 -በጌሴም መስፈር

- ዘፍጥረት 47፡9- ፈርኦን ፊት በቀረበ ግዜ የያዕቆብ እድሜ
- ዘፍጥረት 47 ፡13 የረሀቡ ጉዳት እና ዮሴፍ ግብፃውያንን እንዴት እንደረዳቸው
- ዘፍጥረት 47፡26 ከአምስቱ እጅ አንዱ ለፈርኦን የሚለው የዮሴፍ ህግ
- ዘፍጥረት 47፡27 የያዕቆብ ሞት ቀረበ
- ዘፍጥረት 48፡የዮሴፍ ልጆች በያዕቆብ ተባረኩ
- ዘፍጥረት 49 ያዕቆብ ከመሞቱ በፊት ልጆቹ በሙሉ የሚገባቸውን በረከት ተቀበሉ
- ዘፍጥረት 49፡29 ያዕቆብ ሞተ
- ዘፍጥረት 50፡1-14 ዮሴፍ እና ወንድሞቹ አባታቸውን በከነአን ቀበሩ
- ዘፍጥረት 50፡22 የዮሴፍ ሞት

## <u>ክፍል 6</u>

***መግቢያ*** ፡ ዘፍጥረት 50፡15-51 ያለውን ታሪክ ሳናጠቃልል የዮሴፍን ታሪክ አንደመድምም፡፡እነዚህ ቁጥሮች ለእኛ እና ለወንደሞቹ የምስራች የያዘ ነው፡፡አባታቸው ሲሞት የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍ ይበቀለናል ብለው አሰቡ፡፡ምክንነያቱም በምድሪቱ ላይ ታለቅ መሪ ሆኖ አይተውታል፡፡ሁሉም ለሱ ይገዛ እና ይታዘዝ ነበር፡፡አንዲት ትእዛእ ቢያተላልፍ ሁሉም በአንድ ግዜ ሊታሰሩ እና ሊገደሉ ይችላሉ፡፡ስለዚን እነዚህ ወንድማማቾች በአባታቸው በያዕቆብ ሞት ምክንያት ህይወታቸው አደጋ ላይ እንደወደቀ አስበዋል፡፡ያዕቆብ በሰላም እና በደህንነት የሚኖሩበትን ሁኔታ እንዳመቻቸላቸው አምነው ነበር ነገር ግን ያዕቆብ ሞተ፡፡

**የቤት ስራ፡**

**መልመጃ፡**

1. ይህ ቁጥር ሰለ ወንድማማቾቹ ምን ያስረዳናል?________________________________
2. በቁጥር አስራ 15 ፍታቻቸው ምን ነበር?____________________________________
3. እንደገና ክፋት አስቀያሚ ገፅታውን ይዞ ተነሳ፡፡ለዮሴፍ አባታቸው ምን እንዳለ ነገሩት?_____

______________________________________________________________________

4. ይህ ቁጥር ስለዮሴፍ ምን ይነግረናል?_________________________________________
5. እንደገና መጥተው ይቅርታ ጠየቁት፡፡ይህ ነገር ዮሴፍን አስቆጣው፡፡እስካሁን ፍቅሩ አልገባቸውም? የሱ ፍቅር ከእነሱ ጥፋት እደሚበልጥ አልተረዱም?እሱ ምን አላቸው?__________

______________________________________________________________________

ፍቅር ፍርሀትን ያስወግዳል ፡፡እንዳይፈሩ ነገራቸው፡፡እነሱን እና ልጆቻቸውን እንደሚጠብቅ ቃል ገባላቸው፡፡በመጨረሻም ፍቅሩን እና ደግነቱን በመልካም ቃል በመናገር አረጋገጠላቸው፡፡የየቅርታ ስራ ተጠናቀቀ፡፡

**ግላዊ ትግበራ፡** እናንተስ የጥፋተኝነትን ስሜት ይዛችሁ ለመጓዝ ትመርጣላችሁ?የወንድሞቹ የጥፋተኝነት ስሜት ዮሴፍን አበሳጨው፡፡ስለእነሱ አነባ፡፡ይቅር እንዳለች እና እንደሚወዳቸው እንዲረዱ ያደረጋቸው ነገር ምንድ ነው?ህይወታቸውን በነፃነት እንዲኖሩ ፍፁም ላልተፈጠረ ነገር ባሪያ እንዳይሆኑ ነገራቸው፡፡

እስከ ዛሬ ከእናንተ ህይወት ያልተወገደ የጥፋተኝነት ስሜት ምንድነው?እራሳችሁን ይቅር ማለት ያቃታችሁ ነገር ምንድነው?እራሳችንን ይቅር ማለት ምርጫው የእኛ ሲሆን እግዚአብሄር ደግሞ ያግዘናል፡፡እግዚአብሄር ከእርሱም ይቅርታን እንድንቀበል፣ሌሎችም ይቅር እንዲሉን እግዚአብሄር ይረዳናል ፡፡ከእርሱ የምንቀበለው ይቅርታ በነፃ ነው፡፡በራሳችን ኃይል ይቅርታን መቀበል አንችልም ነገር ግን በእርሱ ኃይል ይቅርታ የእኛ ይናል ፣የግላችን ይሆናል፣ያለመከልከል መቀበል እንችላለን ፡፡መጽሐፍ ቅዱሳችነ በያዕቆብ 5፡16 ላይ እርስ በእርሳችን ኃጢአታችንን እንድንናዘዝ ይነግረናል ፡፡ኑዛዜ ይቅርታ የመቀበያ አንዱ ከፍል ነው፡፡በኑዛዜ ኃጢአት መገለጥ ይጀምራል ይቅርታም ወደውስጣችን መግባት ይጀምራል ፡፡መናዘዝ ፈውስ ያደርጋል፡፡እርስ በእርሳችነ ስንናዘዝም የተሰበሩ ግንኙነቶች ይፈወሳሉ ፡፡ኑዛዜ ማለት አንዱ ሰው ከሌላው ይበልጣል ማለት አይደለም፡፡ እንዳችን ለአንዳችን ስንናዘዝ ሁላችንም ደካሞች እንደሆንን እናውቃለን፡፡መናዘዝ ታላቅ ሆነ ፍቅር በህይወታችን እንዲፈስ ያደርገናል ፡፡

**ጸሎት፡** ጌታ ሆይ ለኃጢአታችን ሁሉ  የይቅርታን የምስራች አወጅክልን ፡፡ከዚህ በኋላ ይህንን መርዘኛ የሆነ የጥፋተኝነት ስሜት ከህይወታችን መለየት የማይፈልገውን የጥፋተኝነት ስሜት ተሸክመን መዞር  አያስፈልገንም፡፡ጌታሆይ ከፍቅርህ የሆነው ይቅርታ እንድቀበል ስላስታጠከኝ አመሰግንሀለሁ፡፡ይቅርታ በህይወቴ ስላመጣው ነፃነት አመሰግንሀለሁ፡፡ከእየሱስ ክርስቶስ የተነሳ እንደ ልጅህ፤ እንደ  ንጉስ ልጅ እንድመላለስ ስላደረከኝ አመሰግናለሁ፡፡በሉቃስ ወንጌል ላይ "ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል፡፡ ተብሎ የተፃፈውን ቃልህን አምናለሁ፡፡እኔም በአንተ ይቅር እንደተባልኩ ሌሎችን ይቅር የምልበት እድል ስጠኝ፡፡ሌሎችንም በነፃነት እና መይቅርታ ይመላለሱ ዘንድ እርዳቸው፡፡

ክለሳ

# ነፃነታችን የሆነው የእግዚአብሄር ይቅርታ

## ክለሳ

የዚህ ለዩ መልመጃ አላማ የብሉይ ኪዳን ታሪኮችን በማወቅ በአግባቡ እንድታድጉ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።የዚን ምዕራፍ  ተቀዳሚ ገፀ ባህሪ ያዕቆብ እና ልጆቹ ናቸው።አብዛኞቹ የተቀመጡት ባላቸው በስፍራቸው ነው። አንዳንዶቹን ገፀባህሪያትእስቲ እንደገና በክለሳ መልክ ተመልከቷቸው የምታስታውሷቻን ነገሮች ደግሞ በማስታወሻችሁ ላይ ያዟቸው።

| ማጣቀሻ | ገፀ ባህሪያት | የማስታውሳቸው ነገሮች …… |
| --- | --- | --- |
| ዘፍጥረት 37:21-23; 42:22 | | |
| ዘፍጥረት 37:26; 43:8-9 | | |
| ዘፍጥረት 39:1 | | |
| ዘፍጥረት 39:7 | | |
| ዘፍጥረት 39:21 | | |
| ዘፍጥረት 40:2 | | |
| | | |

| | | |
|---|---|---|
| **ዘፍጥረት** 40:2 | | |
| **ዘፍጥረት** 42:24 | | |
| **ዘፍጥረት** 43:29 | | |

ጊዜ ወስዳችሁ የዬሴፍ የሀገሪቱ ሁለተኛ ሰው ለመሆን ወደግብፅ ምድር ያደረገውን ጉዞ ማስታወሻ ፃፉ

1. ዘፍጥረት 37
   ሀ. ______________________________
   ለ. ______________________________
   ሐ. ______________________________
2. ዘፍጥረት 39
   ሀ. ______________________________
   ለ. ______________________________
3. ዘፍጥረት 40
   ሀ. ______________________________
   ለ. ______________________________
4. ዘፍጥረት 41
   ሀ. ______________________________
   ለ. ______________________________
   ሐ. ______________________________
5. ዘፍጥረት 42-44
   ሀ. ______________________________
   ለ. ______________________________
6. ዘፍጥረት 45
   ሀ. ______________________________
   ለ. ______________________________

ይህንን ክፍል ስጣታት በመፅሀፍ ቅዱሳችሁ ላይ ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ስፍራዎች እንደገና አጥኗቸው፡፡ከእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ደግሞ ለ21ኛው ክፍለዘመን ሰው ያላቸውን መልእክት በመፈለግ ለህይወታችሁ ጥቅም ያገኛችሁባቸውን ጥቅሶች ተመልከቷቸው፡፡

______________________________

______________________________

______________________________

ከዮሴፍ  ታሪክ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የእናንተን ታሪክ የት ጋ አገኛችሁ?

ከዮሴፍ ጋር ፊትለፊት መገናኘት ብትችሉ እና ካሳለፋቸው አስቸጋሪ ወቅቶች እንዲያካፍላችሁ የምትጠይቁት  የትኛውን ነው?

“እግዚአብሄር ከእኔ ጋር ነው።” እስቲ ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ እግዚአብሄር ከእናንተ ጋር የነበረበትን ጊዜ አስታውሱ ።በዚህ አጋጣሚ እግዚአብሄር አብሯችሁ በመሆን ስላከናወነላችሁ ነገር አመስግኑት፤ በሌሎች ፊትም ሞገስን ስለሰጣችሁ አመስግኑት።